በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት (ከ1968-2004 ዓ.ም) የአማርኛ ቋንቋ

መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

በ

እምሻው ማሞ

ሰኔ 2005

አዲስ አበባ

ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት (ከ1968-2004 ዓ.ም) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

እምሻው ማሞ

ሰኔ፣ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት (ከ1968-2004 ዓ.ም) የአማርኛ ቋንቋ

መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

በ

እምሻው ማሞ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም	ፊርማ	ቀን
ፀጋዬን አሰግሪ		27/10/05
የፈታኝ ስም	**ፊርማ**	
1. ዶ/ር ገዛኸኝ		27/10/05
2. ፕ/ር ኃይሉ		22/10/05

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ.ጥ.ተ.
በተ መ ሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምስጋና

የመጀመሪያው የፈጣሪ ነው። "ኪያከ እግዚኦ ንሴብሃከ ወንዌድሰከ"!

ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ ሳዘጋጅ ፡- የጥናቱ ርዕስ ተስተካክሎ እንዲጸድቅ ከማድረግ ጀምሮ አቅጣጫ በመጠቆም ፣ስህተቶቼን በማረምና በማቃናት ሙያዊ ድጋፋቸውን ለለገሱኝ መምህሬ እና አማካሪዬ ዶ/ር ጌታሁን አማረ እግዜር ይስጥልኝ።

የትምህርት እድል የሰጠኝን የአርባምንጭ ትምህርት ኮሌጅና ለጥናቴ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት ላመሰግን እወዳለሁ።

ቤተ መጻሕፍታችሁን እንድጠቀም የተባበራችሁኝን የዳግማዊ ምኒልክ የመሰናዶ ትምህርት ቤትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዘክር ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

እዚህ ደረጃ እንድደርስ ያላችሁን ሁሉ ላደረጋችሁልኝ ወላጆቼ፡- አባቴ ማሞ በለጠ እና እናቴ ይረፉ ደነቀ ረጅም እድሜ እና ጤና ፈጣሪ ይስጥልኝ። ልፋታችሁ ወኔ ሀዘናችሁ ስንቄ ሆኖ እዚህ አድርሶኛልና።

ልጅ ማሳደግን ከመንግሥት ሥራ ጋር ደርበሽ ከባዱንና መራራውን የኑሮ ስንክሳር ለብቻሽ በመቋቋም ያለሃሳብና ጭንቀት እንድማር ዋጋ ለከፈልሽዉ ባለቤቴ የኔነሽ አበበ ገ/ሃና ከሚስትነትም በላይ ባለዉለታዬ ነሽ! እወድሻለሁ።

ልጆቼ የአብ ስራ ድንቅ እና ጎዙናን እምሻዉ ለትዕግስታችሁ ሠላም እላለሁ። የመቼ ነዉ ምትመጣዉ አሳዛኝ ጥያቄያችሁ መልስ በማግኘቱ ደስ ብሎኛል።

በወሳኙ ሰዓት ጽሁፌን በማረም ለተባበርሽኝ አስቴር ገመዳ እና ዉድ ጊዜያችሁን ሰዉታችሁ ከጎኔ በመሆን ለረዳችሁኝ ጓደኞቼ አሸብር አለማየሁና ወንድማገኝ አደም መልካሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ።

መታሰቢያነቷ

በህይወት መንገድ ላይ...

እረፍታችሁ ሸንፈትን ላስተማረች

ትዝታዬ ብትሆኑም

ሁሌም ለምወዳችሁ

ወንድሞቼ

ዘገዬና ፍስሃ ማሞ

ትሁንልኝ::

ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

ምስጋና.....i

ማውጫ.....ii

የሰንጠረዥ ማውጫ.....vi

ሙዳዬ ቃላት.....vii

አህጽሮተ ጥናት.....viii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ.....1

1.1. የጥናቱ ዳራ.....1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.....3

1.3. የጥናቱ ዓላማ.....7

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ.....8

1.5. የጥናቱ ወሰን.....9

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት.....10

2.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት፣ ሥነ ትምህርታዊ ጠቀሜታ እና አይነት.....10

2.1.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት.....10

2.1.2. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሥነ-ትምህርታዊ ጠቀሜታ.....11

2.1.3. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አይነት.....12

2.1.3.1. ጥንታዊ (መዋቅራዊ) የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት.....13

2.1.3.2. ዘመናዊ ወይም ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት.....14

2.2. የሰዋስው ምንነት.....15

2.2.1. የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ምንነት፣ ይዘቶች ባህሪያትና ትኩረት.....17

2.2.1.1 የስነ ትምህርታዊ ምንነት.....17

2.2.1.2 የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች ባህሪያት.....18

2.2.1.3. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘት ትኩረት.....19

2.3. የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት እና ይዘቶች አቀራረብ.....21

2.3.1 የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት 21
2.3.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ 24
2.3.2.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ 25
2.3.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ 27
2.3.2.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ 28
2.3.2.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ 29
2.3.2.5. ጥምረታዊ አቀራረብ 31
2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 33
ምዕራፍ ሶስት
የጥናቱ ዘዴ 37
3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጭ 37
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ 37
3.3 የመማሪያ መፃህፍትና የክፍል ደረጃ አመራረጥ 38
3.4 የጥናቱ ዘመን አመራረጥ 38
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ 39
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ትንተና 40
4.1 ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ ፍት መጻሕፍት ሰዋስውን በተመለከተ ያላቸው አቋም 41
4.2. ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች 42
4.2.1 በ1968 ዓ.ም. በታተሙት መፃህፍት ውስጥ 44
4.2.2 በ1972/3 ዓ.ም. ተሻሽለው በታተሙት መፃህፍት ውስጥ 45
4.2.2 በ1984 ዓ.ም በታተሙት መፃሕፍት ውስጥ 46
4.2.4 በ1991/2 ዓ.ም በታተሙት መፃህፍት ውስጥ 49
4.2.5 በ1997 ዓ.ም በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ 51
4.2.6 በ2004 ዓ.ም በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ 53
4.3. ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ 55
4.3.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ 55

4.3.1.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1968 ዓ.ም 55

4.3.1.2 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም 58

4.3.1.3 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1984 ዓ.ም 59

4.3.1.4. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም 59

4.3.1.5. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1997 ዓ.ም 61

4.3.1.6 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ2004 ዓ.ም 64

4.3.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩትና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ 66

4.3.2.1.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1968 ዓ.ም 66

4.3.2.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም 68

4.3.2.3 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1984 ዓ.ም 70

4.3.2.4 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም 73

4.3.2.5 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1997 ዓ.ም 74

4.3.2.6 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ2004 ዓ.ም 76

4.3.3 ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም በነበሩትና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ 78

4.3.3.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1968 ዓ.ም 79

4.3.3.2 ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም 80

4.3.3.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1984 ዓ.ም 81

4.3.3.4 ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም 83

4.3.3.5 ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1997 ዓ.ም 85

4.3.3.6 ውጤት ተኮር አቀራረብ በ2004 ዓ.ም 86

4.3.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ 88

4.3.4.1. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1968 ዓ.ም 88

4.3.4.2 ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም 90

4.3.4.3 ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1984 ዓ.ም 91

4.3.4.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም 94

4.3.4.5. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1997 ዓ.ም 96

4.3.4.6. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ2004 ዓ.ም 97

4.3.5 ጥምረታዊ አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ 99

4.3.5.1 ጥምረታዊ አቀራረብ በ1968 ዓ.ም 100

4.3.5.2 ጥምረታዊ አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም 101

4.3.5.3 ጥምረታዊ አቀራረብ በ1984 ዓ.ም 101

4.3.5.4 ጥምረታዊ አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም 103

4.3.5.5 ጥምረታዊ አቀራረብ በ1997 ዓ.ም 106

4.3.5.6 ጥምረታዊ አቀራረብ በ2004 ዓ.ም 109

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት 112

5.1 ማጠቃለያ 112

5.2 አስተያየት 119

ዋቢ ጽሁፎች 122

የሰንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

ሠንጠረዥ 1 ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሠዋስው ትምህርት ረገድ በጊዜ ሂደት የቀረቡ ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ----------42

ሠንጠረዥ-2 በ1997 ዓ.ም በታተመዉ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ----------63

ሠንጠረዥ-3 በ1997 ዓ.ም በታተመዉ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ----------64

ሠንጠረዥ-4 በ2004 ዓ.ም በታተመዉ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ----------65

ሠንጠረዥ-5 በ2004 ዓ.ም በታተመዉ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ----------66

ሠንጠረዥ-6 በ1972/3 ዓ.ም በታተመዉ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ----------70

መዳዬ ቃላት

1. ሂደታዊ አቀራረብ	process approach
2. መዋቅራዊ ሥነልሳን	Structural Linguistics
3. መደበኛ ሰዋስው	Formal Grammar
4. ማጣቀሻ ሰዋስው	Referential Grammar
5. ሰዋስዋዊ ፍቺ	Grammatical meaning
6. ስነ ልቦናዊ ሥነልሳን	Psychological Linguistics
7. ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው	Pedagogical Grammar
8. አዛዥ ሰዋስው	Prescriptive Grammar
9. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር	Deductive
10.ውጤት ተኮር አቀራረብ	Product Approach
11.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ	Inductive
12.ድረጃ	Grading
13.ገላጭ ሰዋስው	Descriptive Grammar
14.ጥምረታዊ አቀራረብ	Integrative Approach

አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከመቼ ጀምሮ ቀርበው እንደነበረ መፈተሸና ከሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የማቅረቢያ መርሆዎች አንፃር እንዴት እንደቀረቡ በመመርመር በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥና መሻሻል ወይም አለመሻሻል መገምገም ነበር። ጥናቱ ባነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ የተለያዩ ምሁራን ያቀረቧቸውን ንድፋ ሃሳባዊ መርሆዎች መሠረት በማድረግ በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ረገድ መነሳት ያለባቸውን ነጥቦች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በማሰባሰብ ለማቅረብ ሞክሯል። ጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የተጠቀማቸው ሠነዶች፤ በተጠቀሰው ዘመን ቀርበው የነበሩትን የተተኳሪዎቹ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት ሲሆኑ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች "ሥነ ድምጽ፣ ሥነ ምዕላድ፣ ሥነ ሐረግ፣ አረፍተ ነገርና ሥነ ፍቺ" ከተመደቡ በኋላ ከመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ተለይተው እንዲወጡ ተደርገዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በምዕራፍ ሁለት ከተጠቀሱት የማቅረቢያ መስፈርቶች አንፃር በገላጭ ስልት ተተንትነዋል። በጥናቱ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተውም፣ ሥነ ድምጽን በተመለከተ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ አልቀረበም። ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መፃህፍት ውስጥ ግን መገኘቱ ታውቋል። ሥነ ምዕላድ፣ ሥነ ሐረግ፣ አረፍተ ነገርና ሥነ ፍቺን በተመለከተ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በአገባባቸው ላይ በማተኮር ቅርፃዊ ገጽታቸው ችላ ተብሎ የቀረበ ሲሆን ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ግን ከአገባብና ፍቺ በተጨማሪ ለሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ቅርፃዊ አወቃቀርና አጠቃቀም ጭምር ትኩረት ተሰጥቷቸው የቀረቡ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል። የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ በተመለከተም በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የተለያየ ገጽታ የታየባቸው ሲሆኑ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያሳዩትን ለውጥ በተመለከተ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እያሳዩ በመምጣት የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሱ ቢሆንም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አመጣጥኖ ከማቅረብ አንጻር አሁንም ቢሆን መጻህፍቱ ሙሉ በሙሉ ከችግሩ ያልጸዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። በተተኳሪዎቹ ክፍሎች ቀጣይ የመጻህፍቱ ዝግጅት ወቅት እስካሁን ከታዩት የአቀራረብ ክፍተቶች ተነስቶ የተሻሉ መጻህፍት መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው በመጠቆም እና አስተያየት በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ ተማሪዎች ሥርዓት ባለው መንገድ በቋንቋው እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው። ይኸው ጉዳይ በየመማሪያ መፃሕፍቱ የመግቢያ ክፍል በሚከተለው መልኩ ተብራርቶ እናገኛዋለን። ለአብነትም በ2004 ዓ.ም በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ላይ "የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ማጎልበት፤ እንዲሁም የሰዋስውና የስነ-ፅሁፍን መሰረታዊ ፅውቀቶች ማዳበር መሆናቸው ይታወቃል።" በሚል መልኩ ሰፍሮ እናገኘዋለን። በመሆኑም እተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ ይቻል ዘንድ በውስጣቸው የክህሎት፣ የሥነ ልሣንና የሥነ ጽሁፍ ይዘትነት ያላቸውን የትምህርት ግብአቶች በአግባቡ የያዙ፣ በወጉ የተደራጁና ብቃት ያላቸውን የቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ማሰናዳትና በአግባቡ ማደራጀት እንደሚያስፈልግ Brown (1994) ይገልፃሉ።

ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች ሥርዓት ባለው መንገድ በቋንቋ መገልገል ይችሉ ዘንድ በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ከሚካተቱት የክሂልና የሥነ ፅሁፍ ይዘቶች በተጨማሪ የሰዋስው ትምህርትም አንዱ መሆኑን ነው። ይህም ሰዋስው የቋንቋ ትምህርት የትኩረት አቅጣጫ አንድ መስክ መሆኑን ያስገነዝበናል።

በርግጥ እንደ Bygate et.al, (1994) ገለፃ የሰዋስው ትምህርት ዘርፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሥፍራ በተመለከተ ከአፍ መፍቻ ወይም ከሁለተኛ ወይም ከውጪ ቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ በትምህርትነት መሰጠት "አለበት /የለበትም" በሚል ረገድ ብዙ ክርክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት በሁለተኛ ወይም በውጪ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ አብይ ጉዳይ ሆኖ ከመገኘት ያገደው ነገር የለም።

ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትኩረት በተሠጠበት በ20ኛው መቶ ክፍለ-ዘመንም ቢሆን በተለይም እስከ 1980ዎቹ ድረስ የሰዋስው ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ማዕከላዊ ጉዳይ ሊሆን መቻሉን Mitchell (1994)፣ Rutherford (1987)፣ እና Tonkyn (1994) ይጠቁማሉ።

ይህም የሆነው ያለምክንያት አይደለም። የሰዋስው ትምህርት ለአጠቃላዩ የቋንቋ ትምህርት ጉልህ ሚና ስላለው እንጂ። ባየ (1987) ይህንኑ ጉዳይ፣ የቋንቋን ትምህርት በተመለከተ በርግጠኝነት መናገር ከምንችልባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ "የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከነ ሥርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ እውቀት ያለው መሆኑን ነው" በማለት የሥነ ልሣን ትምህርት የክሂል ትምህርትን ያህል የሚያስፈልግ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

ጌታሁን (1989) በበኩላቸው የሰዋስው ትምህርት ዘመናዊ እሳቤ ህግጋትን የማወቅና ያለማወቅ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን ከዚያ ባሻገር ያለውንና ለተግባቦታዊ ተግባር የሚሰጠውን ፋይዳ ከግንዛቤ ያስገባ መሆን እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተው ይገልፃሉ።

Palmer (1984) እንዲሁ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋስዋዊ እውቀት ላይ የተመሠረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። በማለት ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቦታ አስረግጠው ይናገራሉ።

ከእነዚህ ምሁራን አባባል የምንረዳው የስዋስው ትምህርት ተማሪዎች ላቅ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ እንዲኖራቸው፣ ትክክለኛውን የቋንቋ ትንታኔ እንዲያውቁ፣ በአጠቃቀም ወቅትም ስህተት ሲፈጠር ሥህተቱ የምን እንደሆነ ከመናገር በተጨማሪ እርማት ለመስጠት እንዲችሉ ጭምር የሚያበቃ የእውቀት ባለቤት የሚያደርግ መሆኑን ነው። ይህም ማለት ተማሪዎቹ የቋንቋውን ቅርጽ ከአገልግሎት፣ ከፍቺና ከጠቃቀም ጋር አጣምረው በመማር ተገቢ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን አፍልቀው እንዲጽፉና እንዲናገሩ የሚያስችል የትምህርት ዘርፍ ነው።

በመሆኑም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ተካተው መቅረብ ይገባቸዋል ስንል ከላይ የተዘረዘሩትን ማለትም የሰዋስው ትምህርት ለአጠቃላዩ የቋንቋ ትምህርት የሚያበረክተውን ጉልህ አስተዋጽኦ ታሳቢ በማድረግ ነው።

የስዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እንደ አንድ የትምህርት ይዘት መቅረብ ይኖርባቸዋል ሲባልም በአቀራረብ ረገድ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሲዋቀሩ ከክሂሎችም ጋር ሆነ ከቋንቋው የእውቅት ዘርፎች ጋር ጥብቅ ትስስር ሊኖራቸው ይገባል።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩት እና አሁንም ግልጋሎት እየሰጡ ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማረያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የማቅረቢያ መርሆዎች አንፃር እንዴት እንደቀረቡ በመመርመርና በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥ በመፈተሽ ላይ ነው።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለዚህ ጥናት በአነሳሽ ምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል የመጀመሪያው "የመማሪያ መፃህፍት ዝግጅት በአንድ ጊዜ የሚጠናቀቅ ተግባር አይደለም" የሚለው የምሁራን እይታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እስከ አሁን ድረስ በተተኳሪዎቹ መፃህፍት ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያልዳሰሷቸውን ጉዳዮችና ዘመናት ጭምር ለማየት መፈለግ ነው። በዋናነት ግን በተጠቀሰው ዘመን ተዘጋጅተው አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በጊዜ ሂደት ያሳየውን ለውጥ ለመገምገም መሻት ነው።

በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ ከላይ አጠቃላይ በሆነ መልኩ የተጠቀሱትን ሃሣቦች ዘርዘር አድርገን እንቃኛለን።

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሚገመገሙባቸው በበርካታ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደነ Dubin እና Olshtain (1986)፣ Stern (1992) እና Cunningsworth (1995) ገለፃ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በጥንቃቄ የተመረጡና በወጉ የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለማቅረብ ይችሉ ዘንድ በዝግጅት ወቅት የተለያዩ ሥነ-ልሣናዊ፣ ሥነ-ትምህርታዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ሃሣቦችን መሠረት ማድረግ ያለባቸው መሆናቸውን በመጠቆም በዝግጅት ወቅትም ይሁን ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ በተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸውና በሚገኙ ምላሾችም ሊሻሻሉ እንደሚገባቸው ይገልፃሉ።

Donough and Show (1995) በበኩላቸው ግምገማ የሚያስፈልገው ሥራ ላይ ያሉ መፃህፍትን ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ለመለየት ሲሆን አዲስ የሚዘጋጁትን መፃህፍት ደግሞ ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ ነው ይላሉ።

Grant (1987)ም እንዲሁ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የተካተቱባቸውን የመማሪያ መፃህፍት ትኩረት ሰጥቶ የመመርመርን ተገቢነት ሲያስረዱ በምክንያትነት ያቀረቡት ሃሣብ "ምንም አይነት ችግር የሌለባቸው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን አዘጋጅቶ ማቅረብ አይቻልምና ነው" የሚል ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን አባባል የምንረዳው የመማሪያ መፃህፍት ዝግጅት በአንድ ጊዜ የሚያበቃ ተግባር ያለመሆኑን ነው። በየጊዜው እየተገመገሙና እየተፈተሹ ጠንካራ ጎናቸው የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትና ደካማ ጎናቸው ደግሞ የሚስተካከልበት ሁኔታ መፈጠር ያለበት መሆኑን ነው።

ይህንን ሃሣብ መሠረት በማድረግ ወደ ሀገራችን የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መፃህፍት ስንመጣ፣ ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረበት ከ1900 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ ድረስ የሰዋስው ትምህርት ይሰጥ የነበረው ከሌሎች የክሂልና የእውቀት ዘርፎች ጋር ተቀናጅቶ ሳይሆን ለብቻው "በጥሬ ወይም በደረቅ የሰዋስው ትምህርትነት" እንደነበረ በ1968 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት መግቢያ ላይ በሚከተለው መልኩ ሠፍሮ እናገኘዋለን።

> *በመጀመሪያ ሰዋስው ከቋንቋው የወጣ ሥርዓትና ደንብ እንደ መሆኑ መጠን ለብቻው ታይቶ እንደ አንድ ክፍለ ትምህርት መሰጠት አልነበረበትም። እንደ አንድ ክፍለ ትምህርት ቢሰጥም እንኳን፣ በተቻለ መጠን ተግባራዊ ከሆነ ይዘታ ጋር በመጣመር ሳይደጋገም፣ በቃል ትምህርት ላይ ሳይመሰረትና በፈተና ላይ ብቻ ሳያተኩር ማቅረቡ የተሻለ ሲሆን ባለፈው ስርዓተ ትምህርት ግን ለዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ይቀርብ ነበር (ገጽ 1)።*

አባባሉ የሚነግረን ሰዋስው ከተጠቀሰው ጊዜ በፊት ሲቀርብ የነበረው እንደ አንድ ክፍለ ትምህርት ለብቻው መሆኑንና ይህም አቀራረብ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ነው። በምትኩም መሰጠት ያለበት ተግባራዊ ከሆነ ይዘት ጋር በመጣመር መሆን እንዳለበት

ያስገነዝበናል። በመሆኑም መፃህፍቱ የተዘጋጁት በዚሁ መርህ በመሆኑ የሰዋስው ትምህርት ከቋንቋው የክሂልና የእውቀት ዘርፎች ጋር ተቀናጅቶ በተማሪው የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ መቅረብ የጀመረው ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ ነው ማለት ነው።

በ1944 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀውን የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-12ኛ) ሥርዓተ ትምህርትን መሠረት አድርገው በ1968 ዓ.ም የታተሙት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉት የስርዓተ ትምህርትና የመርሃ ትምህርት ለውጦች እስከ አሁን (2005 ዓ.ም) ድረስ አራት ጊዜ እንደ አዲስ የተዘጋጁ ሲሆኑ ሁለት ጊዜ ደግሞ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቶቹ የሥርዓት ለውጥን ተከትሎ በመጣው የቋንቋ ፖሊሲ ለውጥ እና በተከታታይ በተደረጉ የመርሐ ትምህርት መሻሻል ናቸው።

የመጀመሪያዎቹ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በ1968 ከታተሙ በኋላ በ1972/73 ዓ.ም ማሻሻያ የተደረገባቸው ሲሆኑ የአገልግሎት ዘመናቸውም በ1984 ዓ.ም በተዘጋጁት መፃህፍት እስከተተኩበት ድረስ የዘለቀ ነበር። በዚህ ወቅት እንደ አዲስ የተዘጋጁት የመማሪያ መፃህፍት በተራቸው እስከ 1990/91 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ በ1991/92 ዓ.ም ለታተሙት የመማሪያ መፃህፍት ቦታቸውን ለቅቀዋል። በወቅቱ የተዘጋጁት የመማሪያ መፃህፍትም በ1997 ዓ.ም ማሻሻያ ከተደረገባቸው በኋላ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሲሆኑ በመጨረሻም በ2004 ዓ.ም በተዘጋጁት ሌሎች አዳዲስ መፃህፍት ተተክተዋል። ለውጡና መሻሻሉም እዚሁ ላይ የሚያበቃ ሳይሆን በጊዜ ሂደት እንደሚቀጥል ይታመናል።

ይሁን እንጂ በእነዚህ በተለያዩ ጊዜያን ተዘጋጅተው አግልግሎት ሲሰጡ በነበሩት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የቋንቋው የክሂልና የእውቀት ዘርፎች ጋር ተቀናጅተው ሲቀርቡ የነበሩ ቢሆንም የዚህ ጥናት አቅራቢ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸውን በተመለከተ በተጠቀሱት ጊዜያት ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ያሳዩት ለውጥ ምን መልክ እንደነበረው የሚጠቁም መረጃ አላገኘም።

ይህ ማለት ግን የሰዋስው ትምህርት በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ምን ገጽታ እንደነበረው የሚያመለክቱ ጥናቶች ከቶውኑ የሉም ማለት አይደለም፤ እንዲያውም በርካታ ናቸው። ከእነዚህ መካከል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ሥር ከ1987 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የቀረቡት የሰለሞን (1987)፣ ይግለጡ (1988)፣ አስካለ (1992)፣ ኪዳን (1993)፣ ዮሐንስ (1993)፣ እንደገና (1994)፣ ሁሉባንተ (1994)፣ ውድ አዲስ (1994)፣ ካሣሁን (1995) እና ስሜ (1996) ሥራዎች ተጠቃሾች ናቸው።

ከእነዚህ የመመረቂያ ጥናቶች መካከል ከዮሀንስ፣ አስካለ፣ ይግለጡና ሰለሞን ስራዎች በስተቀር ሌሎቹ በአንደኛ ደረጃ የመማሪያ መፃህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ፍተሻ ላይ ያተኮሩ ናቸው። የጥናት ሥራዎቹም አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለሆነና ላልሆነ ተማሪዎች፣ በየክልሎቹ በተዘጋጁ የአማርኛ፣ የኦሮሚኛና የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ምን ገጽታ እንደነበረው የፈተሹ ሲሆኑ ትኩረታቸውም የነበረው በአንድ ወቅት ተዘጋጅቶ/ተው/ ሥራ ላይ በነበረ/-ኡ/ የመማሪያ መፅሐፍ/-ኦች/ ላይ ሲሆን የሰዋስው ትምህርት ይዘቱን ከአደረጃጀትና አመራረጥ አንፃር እንጂ ከአቀራረብ መርሆዎች አኳያ የዳሰሱ አልነበሩም። በተጨማሪም የጥናት አካሄዳቸውም የንጽጽር ሥልትን የተከተለ አልነበረም።

በሁለተኛ ደረጃ የመማሪያ መፃህፍት ላይ የተሠሩት የዮሐንስ፣ ይግ*ለጡ፣ አስካለና ሰለሞን ሥራዎችም ቢሆኑ ምንም እንኳን የትኩረት ነጥባቸው በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በመገምገም ላይ ቢሆንም እንደ መጀመሪያዎቹ ሁሉ እነዚህም "አቀራረብን" ወደ ጎን የተው ነበሩ። በተጨማሪም ጥናቶቹ በተተኳሪው የመማሪያ መጽሀፍ ላይ ከማተኮር በዘለለ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው አቀራረብና አደረጃጀት አንፃር በጊዜ ሂደት (ከ1968-2004 ዓ.ም ድረስ] ሥላሳዩት ለውጥ ያሉት ነገር ካለመኖሩም ሌለ የንጽጽር መንፈስም የማይታይባቸው ነበሩ።

በሌላ በኩል በትምህርት ክፍሉ ለሁለተኛ ዲግሪ (MA) ማሟያነት ከተሰሩት ጥናቶች መካከል የተስፋዬ (1993)፣ ሐዋዝ (2000)፣ የስሌማን (2003) እና ኢያሱ (2003) ጥናቶች ተጠቃሾች ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህም ሥራዎች ቢሆኑ በአንድ ወይም በሁለት የመማሪያ ክፍል መፃህፍት ላይ በማተኮር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት የመረመሩ እንጂ በተለያዩ ጊዜያት የታተሙ መማሪያ መፃህፍትን መሠረት በማድረግ ወጥነት ባለው መልኩ የሰዋስው ትምህርት ይዘት በጊዜ ሂደት በተተኳሪዎቹ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሳየውን ለውጥ የፈተሹ አልነበሩም።

በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ የመማሪያ መፃህፍት የሚገመገሙበትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግና በመስኩ የተደረጉትን ጥናቶች በመፈተሽ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከክሂልና ከእውቀት ዘርፎች ጋር ተጣምረው በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ መቅረብ ከጀመሩበት ከ1968 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ (2004 ዓ.ም ድረስ) ሥራ ላይ በነበሩት እና ባሉት መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ያሳየው ለውጥ ምን እንደሚመስል በንጽጽር መልክ ለመቃኘት በመፈለጉ ጥናቱን በዚህ ርዕስ ላይ ለማድረግ ወስኗል። በመሆኑም ጥናቱ ለተጠቀሰው የክፍል ደረጃ መማሪያ ይሆናሉ ተብለው በተዘጋጁት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ፦

- በሰዋስው ትምህርት ረገድ ምን ምን ይዘቶች ተካትተው ቀረቡ?
- ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ አቀራረባቸው ምን ይመስላል?
- በጊዜ ሂደት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ ከአቀራረብ አንፃር ምን ለውጥ ታይቶባቸዋል?
- ምን አይነት ጥንካሬና ድክመት ታየባቸው? እና
- በተጠኑ መጻሕፍት የታዩት ድክመቶች በቀጣዩ መጻሕፍት ውስጥ መወገድ አለመወገዳቸውም ጭምር ለመፈተሽ ይጥራል።

1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ በነበሩት እና አሁንም ግልጋሎት እየሰጡ ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ

መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በመገምገም ያሳየውን ለውጥ መፈተሽ ነው።

ንዑሳን ዓላማዎች፡- ጥናቱ ከላይ በተጠቀሰው ዋና ዓላማ ሥር የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት።

- በሰዋስው ትምህርት ረገድ ከተጠቀሱት ጊዜያት አንፃር ምን ምን ይዘቶች እንደቀረቡ መፈተሽ፣
- የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ያሳዩት የአቀራረብ ለውጥ ካለ እንዴት እንደቀረበና ምን እንደሚመስል መመርመር፣
- ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከሰዋስው የትምህርት ይዘት ማቅረቢያ መርሆዎች አንፃር በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥ መገምገም እና
- በተጠቀሰው ዘመን የተዘጋጁትን መማሪያ መፃህፍት ከሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ አንፃር የታየባቸውን ደካማና ጠንካራ ጎኖች መቃኘት የሚሉ ናቸው።

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው ጠንካራ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በሚቀርቡ መማሪያ መፃህፍት ላይ በየጊዜው ፍተሻ ማድረግ ጠቀሜታ እንዳለውም የመስኩ ባለሙያዎች ይመክራሉ። ምክንያቱም በሁሉም መልኩ ፍጹም እና እንከን የለሽ የሆነ የመማሪያ መጻህፍ ማዘጋጀት አይቻልምና። በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ከሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው። እንደሌሎች የትምህርት ይዘቶች የሰዋስውን ትምህርት አቀራረብ መገምገምም ተገቢ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል

- በተጠቀሱት ጊዜያት በተዘጋጁት የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ፈትሾ ምን ገጽታ እንደነበረው በመጠቆም በመስኩ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል።

- የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ በተተኳሪዎቹ መፃህፍት ውስጥ በጊዜ ሂደት ያሳየውን ለውጥ በማመልከት በቀጣይ ለሚዘጋጁ የመማሪያ መፃህፍት ዝግጅት የመነሻ ሃሣብ ይሠጣል።
- በሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ረገድ በተተኳሪዎቹ መፃህፍት ውስጥ የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን በማሳየት ጠንካራ ጎኖቻቸው ተጠናክረው የሚቀጥሉበትን ደካማ ጎኖቻቸው ደግሞ የሚሻሻሉበትን አቅጣጫ ያመላክታል።
- በተመሳሳይ ርዕስ ጉዳይ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አካላት እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ሥራ ላይ በነበሩትና ባሉት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው መርሆዎች አንፃር በመገምገም ላይ ነው። በመሆኑም በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥ በማነፃፀር በታላሚዎቹ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

ይህ ክፍል በዋናነት በሦስት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ቅኝት የሚድረግበት ነው። የመጀመሪያው፣ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ክፍልም የሰዋስው ምንነትና ተያያዥ ጉዳዮች የሚዳሰሱበት ይሆናል። ሦስተኛውና የመጨመረሻው ክፍል ደግሞ በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ዝርዝር ሀሳብ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በማሰባሰብ የሚቀርብበት ነው።

2.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት፣ ሥነ ትምህርታዊ ጠቀሜታ እና አይነት

2.1.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት

ለቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት መነሻ የሚሆነው የቋንቋ ትምህርቱ አጠቃላይ አላማ ነው። በመሆኑም በመማሪያ መፃህፍቱ የተባለውን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በሥርዓተ ትምህርቱና በመርሀ ትምህርቱ ዝግጅትና አደረጃጀት ወቅት የሚካተቱ ይዘቶችን የያዙ መተግበሪያ ሠነዶች መሆን ይገባቸዋል።

Grant (1987:8) የመማሪያ መፃህፍትን ምንነት በምስያ ዘይቤ ስልት እንደሚከተለው ገልፀውታል። አንድ ሠው ወደ ማያውቀው አካባቢ ተጉዞ ለመድረስ መረጃ ወይም መመሪያ የሚሆነው የጉዞ ካርታ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፤ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትም ተማሪውን ወደ ተፈላጊው ዓላማ ለማድረስ የሚያስችሉ አስተማማኝ መሣሪያዎች ወይም ለተማሪዎቹ የሚያስፈልጉ የትምህርት ካርታዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ። አክለውም፤ እነዚሁ የመማሪያ መፃህፍት የተደራጁ፣ የተመጠኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለተማሪዎች የሚያቀርቡ መሣሪያዎች መሆን እንደሚገባቸውና ይህንንም በማድረግ ሂደት የተማሪዎቹን አካባቢያዊ እና ዳራዊ እውቀት መያዝ እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባሉ።

በሌላ በኩል Hutchinson and Torres (1994:315-317) እና Sheldon (1987:1-3) የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከአንድ የትምህርት ተቋም እስከ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ድረስ ያለውን የቋንቋ ትምህርት ሂደት፤ ምን ገጽታ ሊኖረው እንደሚገባ ምላሽ ለመስጠት፤ በትምህርት ፖሊሲው፣ በሥርዓተ ትምህርቱና በመርሐ ትምህርቱ የተቀረጹ ይዘቶችን በማጣጣም፣ ሙያው ባላቸው ኤክስፐርቶች የሚዘጋጁ፣ ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ መምታት ዋና መሣሪያ በመሆን የሚያገለግሉ ሠነዶች መሆናቸውን ይናገራሉ።

ምሁራኑ ካቀረቧቸው ሙያዊ ብያኔዎች የምንረዳው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተማሪውን ዳራ፣ እድሜና ፍላጎት፣ እንደዚሁም የአካባቢውን ሁኔታ እና ወዘተ... ታሣቢ በማድረግ የትምህርት ዓላማን ለማስፈፀም የሚዘጋጁ መሣሪያዎች መሆናቸውን ነው። መፃህፍቱ ይህንን ለማድረግ ያስችላቸው ዘንድም መመሥረት የሚኖርባቸው በቋንቋ ትምህርቱ ፍልስፍና፣ ፖሊሲና ዓላማ ላይ ሲሆን የሥርዓተ ትምህርቱንና የመርሐ ትምህርቱን ዝግጅት ተከትለው የሚሠናዱ ሠነዶች መሆናቸውን ነው።

2.1.2. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሥነ-ትምህርታዊ ጠቀሜታ

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የመማር ማስተማር ሂደቱን በማቀላጠፍ ረገድ ላቅ ያለ ጠቀሜታ እንዳላቸው በባሙያዎቹ ይታመናል። በተለይም እንደነ Richards and Rodgers (1986:25-26) እና Sheldon (1987:78) አይነቶቹ የመስኩ ጠበብቶች ተገቢ የሆነ ጥንቃቄና ትኩረት ባልተለየው መንገድ የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጫወቱት ሚና የጎላ መሆኑን ያስረዳሉ። በእነሱ እምነት የህብረተሰቡን የእድገት ደረጃ፣ ወግና ባህል፣ እምነት፣ አስተሳሰብና ፍላጎት፣ እንደዚሁም የትምህርት ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለተማሪው፣ ለመምህሩና በአጠቃላይ ለትምህርት ሂደቱ ስኬታማነት አስፈላጊነታቸው አሌ የማይባል መሆኑን በአጽንኦት ይናገራሉ።

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመጠቀሙን አስፈላጊነት ሲገልጹም፣ "ተማሪዎቹ በጽሁፍ መልክ የቀረቡ መለማመጃዎችን፣ ሣጥቦችን፣ እውነታዎችን ለመረዳትና ለማጎልበት የሚያግዟቸው ሰነዶች ናቸው" ይላሉ። ይህን አባባላቸውን በምክንያት ሲያስደግፉም በመምህር በቃል የሚተላለፍ ትምህርት

ከሽምደዳ ስለማያልፍ ቶሎ ይረሳል፤ በጽሁፍ የሠፈረ ትምህርት ግን ለማንበብ አመቺ ነው፤ ማለትም በእውነታዎች ላይ ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤን ለማዳበርና ግላዊ ግምገማ በማድረግ አመለካከትን ለማስፋት ከቃል ይልቅ በጽሁፍ የቀረበ ትምህርት ተመራጭ ነው። በመሆኑም የመማሪያ መፃህፍት ተማሪው መማር የሚገባውን ይዘት በጊዜው እና በተገቢ የማስተማር ዘዴ፣ ለመማር በሚያስችል መንገድ ሥለሚያቀርቡለት ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ መምህራን የሚማሩ የተለያዩ ተማሪዎች በአንድ አይነት የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ስለሚጠቀሙ ተመሳሳይ ትምህርት እንዲያገኙ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ለመምህራኑም ቢሆን ጊዜና ጉልበታቸውን በመቆጠብ ነገሮችን አቅደው እንዲንቀሳቀሱ ያግዟቸዋልና ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው።

2.1.3. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አይነት

Sheldon (1987:1-3) እና Cunningsworth (1984:2) የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት እንደተማሪው ፍላጎትና እንደትምህርቱ አላማ የሚዘጋጁ በመሆናቸው አይነታቸውን አስመልክቶ ይህ ነው ብሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ቢሆንም የተለመዱትና በሠፊው የሚታወቁት የመማሪያ መፃህፍት አይነቶች ግን ሁለት መሆናቸውን ይናገራሉ። እነርሱም "ጥንታዊ እና ተግባቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት ናቸው" ይሉናል።

Grant (1987:12) በበኩላቸው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አይነቶችን በተመለከተ ከሚከተሉት ሥነ ዘዴ፣ ትኩረት ከሚሰጡበት የቋንቋ ትምህርት አይነት፣ ከተተኳሪዎቹ ተማሪዎች ማንነት አንፃር ልዩነት እንዳላቸው በመግለጽ፤ ሠፋ ባለመልኩ ግን ሥርዓታዊ ወይም መዋቅር ተኮርና ተግባቦታዊ በማለት በሁለት መክፈል እንደሚቻል ጠቁመዋል።

Dawson (1984:137-140) ግን ከላይ በተጠቀሱት ምሁራን የተገለጹትን መሥፈርቶች መሠረት በማድረግ ግን ደግሞ ለየት ባለ የአመዳደብ ስልት መዋቅራዊ፣ ሁነታዊና አገልግሎታዊ በማለት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን በሦስት ጎራዎች መክፈል እንደሚቻል አስገንዝበዋል።

ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን የመማሪያ መፃህፍት አይነቶችን በሁለት ወይም በሦስት ለመክፈል በመመደቢያ መስፈርትነት የተጠቀሟቸውን ጽንሰ ሃሣቦች ወይም የመማሪያ መፃህፍቱን ባህሪያት መሠረት በማድረግ፤ ሥርዓታዊ፣ መዋቅር ተኮርና ጥንታዊ የተባሉትን በአንድ በኩል፤ ተግባቦት ተኮር፣ ሁነታዊ እና አገልግሎታዊ የተባሉትን ደግሞ በሌላ በኩል በመመደብ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን አጠቃላይ በሆነ መልኩ በሁለት ብቻ መክፈል ይቻላል። ምክንያቱም በተጠቃሾቹ ምሁራን መካከል፣ በመማሪያ መፃህፍት አይነቶች አከፋፋል ላይ የተስተዋለው ልዩነት የስያሜ እንጂ የጽንሰ ሃሣብ ልዩነት ባለመሆኑ ነው። በመሆኑም ከዚህ ቀጥለን አባባለችንን ግልጽ የሚያደርግልንን የሁለቱን ምድቦች የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ባህሪያት በዝርዝር እንመለከታለን።

2.1.3.1. ጥንታዊ (መዋቅራዊ) የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት

እነዚህ የመማሪያ መፃህፍት አይነቶች ዋነኛ ትኩረታቸው በቋንቋው መዋቅር ወይም ሥርዓት ላይ ሲሆን ዓላማቸውም "ተማሪዎች የቋንቋውን መዋቅር ካጠኑ፣ በቋንቋው መገልገል ይችላሉ" የሚለውን ሃሳብ የሚያንፀባርቁ ናቸው። እነዚህ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አይነቶች በጥንቃቄ የተመረጡ፣ በታቀደ ሁኔታ በቅደም ተከተል የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን የሚያቀርቡ ናቸው። በመፃህፍቱ ውስጥ የሚገኙ ምዕራፎች፣ ይዘቶች ፣ ወዘተ ሰዋስዋዊ እውቀትን ለማስገንዘብ ዓላማ ያደረጉ እና መፃህፍቱም ለቋንቋው ቅርጽ ወይም ሰዋስው ከፍተኛ ሽፋን ወይም ትኩረት ሲሰጡ ይታያሉ።

እነዚህ የመማሪያ መፃህፍት ተለይተው ከሚታወቁባቸው ባህሪያት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው።

- ቋንቋ ተግቦታዊ ይዘት ይልቅ በቋንቋው ቅርጽ ላይ ማተኮር፣
- በንባብና በጽህፈት ክሂሎች ላይ ብቻ በመመስረት ሌሎች ክሂሎችን መዘንጋት፣
- የአፍ መፍቻ ቋንቋን እንጂ ታላሚውን ቋንቋ ለመጠቀም አለመሞከር፣
- የቋንቋ አጠቃቀም ተክክለኛነት አስፈላጊ ነው ብሎ ማመን፣
- ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው ቁርኝነት የላላ መሆን፣
- በፈተና ነክ ይዘቶች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ለመምህሩ ሥራ ቀላልና ተወዳጅ መሆን ናቸው (Grant 1987:13)።

2.1.3.2. ዘመናዊ ወይም ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት

ዘመናዊ ወይም ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሚባሉት ደግሞ ትኩረታቸው በዋናነት የጥንታዊ የመማሪያ መፃህፍት ድክመቶችን በመቅረፍ ተማሪው በቋንቋው እንዲግባባ ማድረግ ነው። ይህም ማለት መፃህፍቱ ተማሪው በእውናዊ ህይወቱ ውስጥ የሚገለገልበትን የቋንቋ አጠቃቀም የሚያለማምዱ ሲሆኑ ከታላሚው ቋንቋ ቅርጽ ይልቅ ለታላሚው ቋንቋ ተግባቦታዊ ግልጋሎት ትኩረት የሚሠጡ ናቸው። በባህሪያቸውም፡-

- ተማሪው በማህበራዊ ህይወቱ ውስጥ በቋንቋው መግባባት ይችል ዘንድ በክሂሎች መካከል ተመጣጣኝ ይዞታ እንዲኖር ያደርጋሉ፣
- ተማሪው በጥንድና በቡድን እንዲሠራ ያበረታታሉ፣
- በቋንቋ አጠቃቀም ብቃት እንጂ በትክክለኛነት ላይ አያተኩሩም፣
- የትምህርቱን ዓላማ በዝርዝር ለመግለጽ ይጥራሉ፣
- ይዘታቸው ኑባሬያዊነት ያለውና የእውኑ ዓለም ነፀብራቅ ነው የሚሉ ናቸው Grant (1987፡ 118-119) በማለት ይገልፃሉ።

ከዚህ በላይ የሁለቱን የመማሪያ መፃህፍት አይነቶች ምንነት እና መለያ ባህሪያት ምን እንደሚመስል ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመሆኑም ከቀረበው ገለፃ መረዳት የሚቻለው በሁለቱ የቋንቋ መማሪየ መፃህፍት መካከል ልዩነት መኖሩን ነው። ልዩነቱ ጥንታዊያኑ ወይም መዋቅራዊያኑ የመማሪያ መፃህፍት አይነቶቹ የቋንቋውን ተግባቦታዊ ተግባር ችል ብለው ተማሪው የቋንቋውን ቅርጽና ሰዋስዋዊ ህጉን ብቻ እንዲያጠና የሚያደርጉ ሲሆኑ ዘመናዊያኑ ወይም ተግባቦታዊያኑ የመማሪያ መፃህፍት ደግሞ ለቋንቋው መዋቅራዊ ቅርጽ እና ህግ ብዙም ትኩረት ሳይሠጡ በተግባቦት ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸውን ነው።

ይሁን እንጂ አንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ጥሩ መፅሐፍ ነው የሚባለው መፅሐፉ የቋንቋ ክሂሎችን ሥነ-ጽሁፍንና ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አመጣጥኖ ከተማሪው ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር በሚስማማ መልኩ የሚያቀርብ ሲሆን ነው። ይህም ማለት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ይዘቶች የክሂልንም ሆነ የሥርዓት እውቀትን አመጣጥነው የያዙ መሆን ይገባቸዋል ማለት ነው።

ስለ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ይህን ያህል ካልን ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስለ ሰዋስውና ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ምንነትና ተያያዥ ጉዳዮችም የምንለው ይኖረናል።

2.2. የሰዋስው ምንነት

የሰዋስውን ምንነት አስመልክቶ የመስኩ ባለሙያዎች በተለያየ መንገድ ብያኔ ሲሰጡ ቆይተዋል። በጊዜ ሂደት የተሰጡት ብያኔዎችም እንደ ባለሙያዎቹ እይታ ልዩነት ይታይባቸዋል። ባለሙያዎቹ ስለሰዋስው ጽንሰ ሃሣብ ያላቸው አመለካከት በመለያየቱ ምክንያት ወጥ የሆነና ቁጥር ያለ ብያኔ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን Stern (1983፡131) ሰዋስውን "አወዛጋቢ ቃል ነው" በማለት ሲገልጹት ጌታሁን (1989፡iv) ደግሞ የቃሉ ትርጉም "ጽንስ ሃሣባዊ አሻሚነት" እንዳለው ያስገነዝባሉ።

ይሁን እንጂ የጽንሰ ሃሣቡ የቱንም ያህል "አሻሚ" እና "አወዛጋቢ" መሆን ባለሙያዎቹ የተለያዩ ብያኔዎችን ከመሰንዘር ወደ ኃላ እንዲሉ አላደረጋቸውም። በዚህም መሠረት በብዙሃኑ ምሁራን ብያኔ ውስጥ ማለት ይቻላል፣ "የቋንቋ ሥርዓተ ጥናት" የሚለው ሀረግ የብያኔዎቻቸው የጋራ መዳረሻ ይመስላል።

Brown (1994:45) የምሁራኑን የግንዛቤ ልዩነት እና የብያኔያቸውን ማዕከላዊ የማጠንጠኛ ነጥብ በተመለከተ፣ ሰዋስው የቋንቋ ሥርዓት መሆኑን በመጠቆም ሥርዓቱ መሠረት በሚያደርጋቸው ተዋቃሪዎች ረገድ ግን ልዩነት መኖሩን፣ በዚህም መሠረት ብዙዎቹ ብያኔዎች አረፍተ ነገርን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ይናገራሉ። ይቀጥሉናም "ሰዋስው የቃላትን የቅንጅት ስርዓት የሚመለከት፣ በአረፍተ ነገር ደረጃ የሚታይና የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሠረት ያደረገ ቅደም ተከተላዊ የቃላት አገባብ መሆኑን" እንደሚስማሙበት ይገልፃሉ።

ከቀረበው ገለፃ የምንረዳው ሰዋስው የቋንቋ ሥርዓተ ጥናት መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ቢሆንም ሥርዓቱ የሚያተኩረው በየትኞቹ የቋንቋው ተዋቃሪ አካላት [ድምጽ፣ ምዕላድ፣ ቃል፣ ሀረግ፣ ዐ.ነገር] ላይ መሆን እንዳለበት፣ በእነዚህ ተዋቃሪ አካላት ላይ ሲያተኩርም የተዋቃሪ አካላቱን ቅርጽ፣ አገባብና አጠቃቀምን ማካተት አለማካተቱ እና መሠል ጉዳዮች የልዩነታቸው ምክንያቶች መሆናቸውን ነው።

ከዚህ ቀጥለን በሰዋስው ምንነት ዙሪያ ከቀረቡት ብያኔዎች መካከል ለማሳያ ያህል ብቻ የተወሰኑትን ለመመልከት እንሞክራለን።

Stern (1993:131), Harmer (1987:1) Ur (1996:32) Larsen Freeman (1991), Brown (1994:94-95) ባየ (2000:8) እና ጌታሁን (1989) ሰዋስው የአንድን ቋንቋ የአገባበብ ሥርዓት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ሲሆን፣ ይህም የአገባብ ሥርዓት የንግግር ድምጾች ምዕላድን ወይም ቃላትን ለመመስረት ከሚፈጥሩት ቅንጅት እስከ ሀረግና አረፍተ ነገር ምስረታ ድረስ የሚዘልቅ የአገባብ ሥርዓት መሆኑን በድምሩ ያስገነዝባሉ።

ካላይ ከተጠቀሱት ምሁራን መካከል ባየ (2000) እና Brown (1994) ሰዋስው አንድን ቋንቋ ከድምጽ አሰካክ እስከ ሀረግ ምስረታ ሥርዓቱ ድረስ የሚያጠና ነው ሲባል፣ ሥርዓቱ መሠረት የሚያደርገው "የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት ወይም ተናጋሪዎቹ የለመዱትና በአጠቃቀም ወቅት ትክክል ወይም ስህተት ለማለት የሚያስችላቸውን ነው" በማለት የሰዋስው ትኩረት በቋንቋው ቅርጽ ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃቀሙም ላይ መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ ጌታሁን (1989) እና Larsen Freeman (1991) ደግሞ ሰዋስው ከሥነ ድምጽ እስከ አረፍተ ነገር መዋቅር ድረስ ያለውን የቋንቋ ሥርዓት ያጠናል ሲባል ከቋንቋ ላዕላይ ቅርጽ በተጨማሪ በተናጋሪው አዕምሮ ውስጥ ያለውንና የቋንቋ እውቀት ጭምር እንሚያካትት ያስገነዝባሉ። ይህም ማለት ሰዋስው በጠባቡ ሲታይ "የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ጥናት" የሚያመለክት ሲሆን በሰፊው ሲታይ ግን "ቋንቋን ለመጠቀም የሚያስችል ውስጣዊ ችሎታ"ን ጭምር መሆኑን ይገልፃሉ።

በተለይም እንደ ጌታሁን (1989) ገለፃ ሰዋስው ያጠናዋል የተባለው መስክ አንድም በተናጋሪው አዕምሮ ውስጥ ያለውንና የግለሰቡን ቋንቋዊ እውቀት (ግለሰባዊ ችሎታ) ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን አዕምሯዊ እውቀት ተጠቅሞ ችሎታውን በተግባራዊ ግልጋሎት ላይ የሚያውልበትን "ተተግባሪ ሥርዓት" የሚያመለክት መሆኑን ነው።

እንደ Stern (1993), Ur (1996) እና Harmer (1987) ደግሞ ቃላት እንዴት ራሳቸውን ወደ ተለያየ ቅርጽና ይዘት በመለወጥ እና በመቀናጀት ዓረፍተ ነገር የሚመሠርቱበትን ሥርዓት የሚያሳይ፣ ወይም ይህንን የቃላት አቀነጃጀት ህግ የምናጠናበት የቋንቋ የጥናት ክፍል መሆኑን ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ ምሁራኑ ካቀረቧቸው ግላጼዎች መረዳት የምንችለው በአንድ በኩል፣ ሰዋስው የቋንቋ መዋቅር ጥናት መሆኑን ነው። የድምፅ፣ ቀለም፣ ምዕላድ፣ ቃል፣ ሀረግና አረፍተ ነገር። እነዚህ ተዋቃሪ አካላት የአንድ ቋንቋ መገንቢያ ንጥረ ነገሮች ናቸው። የተዋቃሪ አካላቱ መከሠቻ ቅርጸች መዋቅሩ በወኪልነት የቆመለትን እሳቤ (ትርጉም ወይም ፍቺ) ተሻካሚ ናቸው። ቅርጽ፣ ፍቺን ለመሸከም የሚያስችል አቅም የሚኖረው ቅርጹን ያስገኙት ተዋቃሪ አካላት የሚገዙበት አንድ አይነት የአቀነባበር ሥርዓት ሲኖራቸው መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን፣

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከቅርጽ እና ፍቺ ውህደት የተፈጠረው የቋንቋ አሀድ ለማህበራዊ ተግባቦት (መስተጋብር) ተግባር ላይ በሚውልበት ጊዜ ተገልጋዩ ህብረተሰብ የተስማማበትና ማህበራዊ ተቀባይነት ያለው ደንብ መኖሩን እና ሰዋስውም መሠረት የሚያደርገው ይህንኑ ማህበረሰባዊ የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓተ ድንጋጌ መሆኑን ነው።

ከዚህ በመነሳት በዚህ ጥናት ሰዋስው የምንለው የአንድን ቋንቋ የቅርጽ [ከዝቅተኛው (ድምፅ) እስከ ከፍተኛው አሃድ (ዐ.ነገር)ድረስ ያለውን] የአደረጃጀት ሥርዓት፣ የፍቺ፣ የአገባብና፣ የአጠቃቀም ዝምድና ሳይንሳዊ ጥናት ነው የሚለውን ይሆናል።

2.2.1. የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ምንነት፣ ይዘቶች ባህሪያትና ትኩረት

2.2.1.1 የስነ ትምህርታዊ ምንነት

ሰዋስው ከቋንቋ ሥርዓት ጋር የጠበቀ ዝምድና ያለው የጥናት መስክ እና የእውቀት ክፍል መሆኑን ቀደም ብለን አውስተናል። ይህ የጥናት መስክ በውስጡ የተለያዩ በርካታ ንዑሳን ክፍሎችን ይይዛል። ከእነዚህ በርካታ የጥናት መስኮች ወይም የሰዋስው ዘርፎች መካከል ደግሞ በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከቋንቋው የክሂል ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያለው ሥነ ትምህርታዊ ስዋስው መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለተተኳሪዎቹ ተማሪዎች በማቅረብ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ

Odlin (1994:1) ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው በአንድ ወይም በሌላ በኩል ታላሚውን ቋንቋ የሚያግዝ መሣሪያ መሆኑን ይጠቁማሉ። ይቀጥሉናም ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ የሰዋስው አይነቶች ጥምረት የሚታይበት መሆኑን በመግለጽ ከተጣማሪዎቹ

አካላት መካከልም አዛዥ፣ አዕምሮታዊ፣ ሥነ ልሣናዊ እና ገለጭ ሰዋስው እንደሚገኙባቸው ያትታሉ። ከዚህም የተነሳ ይህ የሰዋስው አይነት ወጥ የሆነ የራሱ ባህሪ የሌለው ሲሆን ከተዘረዘሩት የሰዋሰው ዘርፎች የወሰደውን ግብዓት ከመማር ማስተማሩ ጋር አጣምሮ ያቀርባል ይሉናል።

Direven (1990)በ Chalker (1994:34) እንደተገለፀው ሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ፣ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪም ሆነ ለመምህሩ የሚያገለግል መሆኑን ጠቁመው ገላጭ፣ አዛዥ፣ የማስተማሪያ ወይም የማጠቀሻ ሰዋስው አይነቶችን ሁሉ እንደሚያቅፍ አመልክተዋል።

Little (1994) በበኩላቸው ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ረቂቅ እሳቤ መሆኑን በመጠቆም ሥያሜው የታላሚውን ቋንቋ ሥርዓት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ማስተማርን፣ ሥለ ቋንቋው ሥርዓት መረጃ ማግኘት የሚቻልበትን ምንጭ እና የቋንቋን ትምህርት ይዘት የሚያመለክት መሆኑን ያስረዳሉ።

ከላይ ከቀረበው የምሁራን ማብራሪያ የምንረዳው ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ የሰዋስው ዘርፎችን አዋህዶ በመያዙ ጠለቅ ያለ ባህሪ ያለውና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋን መዋቅር ከቋንቋው አገልግሎት ጋር አቀናጅቶ በማቅረብ ትምህርቱን ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የሚያበረክተው አስተዋጾኦ የጎላ መሆኑን ነው።

ይህም ማለት ዘርፉ የቋንቋ ተማሪውንም ሆነ መምህሩን የቋንቋ እውቀት ከማዳበር አኳያ ላቅ ያለ ጠቀሜታ ያለው መሆኑንና በተለይም ለአፍ ፈቱ ተማሪ የራሱን ቋንቋ እንዲረዳው የሚያደርግ ሲሆን ለኢ-አፍ -ፈቱ ደግሞ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት የሚያቀርብለት በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

2.2.1.2 የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች ባህሪያት

ሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች ወቅታዊና ተቀባይነት ባላቸው የሰዋስው ትንታኔዎች መነሻነት፣ ሥለሚማሩት ቋንቋ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራቸው በማድረግና የሰዋስው ይዘቶችን በአውድ አሥደግፎ በማቅረብ፣ ተማሪዎች የቋንቋውን

አገልግሎትና ፍቺ እንዲረዱት የሚያስችል የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደትን የሚከተል መሆኑን አስቀድመን ተመልክተናል።

በመሆኑም ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የአንድን ሠው የተግባቦት ብቃት ከሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ጋር አጣምሮ ቋንቋን ለማስተማር አመቺነት ያለው የአቀራረብ ስልት እንደመሆኑ መጠን የአንድን ቋንቋ ሥርዓት እና ህግጋት በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ በማካተት ተማሪዎች በሚገባ ቋንቋውን እንዲጠቀሙበት የሚያስችልና ለዚህ ተግባር የሚውል የማስተማር ሥነ ዘዴዎችንና ሥልቶችንም አጣምሮ የያዘ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መሆኑን Nunan (1991)እና Newby (2000) ያስገነዝባሉ።

Bygate et.al., (1994)በ Greenbaum (1986) የተጠቀሰውን መሠረት በማድረግ የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች ባህሪያት ያሏቸውን በሚከተለው መልኩ አሥፍረዋቸዋል።

- ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው በመማር ማስተማር መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፤
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የሥነ ልቦናና ሥነ ልሣን መሠረት ያለውና የተማሪውን ሁኔታ ያገናዘበ የአቀራረብ ሥልትን ታሣቢ ያደረገ ነው፤
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎቹ በሚማሩት ቋንቋ ሥርዓት ላይ በማተኮር እንዲማሩት ሁኔታዎችን አመቻች ነው፤
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ በማተኮር ልምምዶችን እንዲያደርጉና በተግባራዊ ግልጋሎትም ወቅት እንዲጠቀሙበት የሚያደርግ ነው።

ይህ የትምህርት ዘርፍ ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት ሲኖሩት የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ደግሞ ቀጥለው በዝርዝር ይቀርባሉ።

2.2.1.3. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘት ትኩረት

በቀድሞው ዘመን ቋንቋን የማስተማር ዓላማና ግብ ተደርጎ የሚታሰበው ተማሪዎቹ የሚማሩትን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ድንጋጌ አውቀው እንዲተነትኑ ማድረግና በተማሩትም ህግ መሠረት ሰዋስዋዊ ሥርዓቱን የጠበቀ አረፍተ ነገር እንዲጽፉ ማስቻል ነበር። ይህም

በወቅቱ የነበረው የሰዋስው ትምህርት እሳቤ በቅርጽ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑን ያስረዳናል።

Nunan (1991) እንደሚሉትም የሰዋስው ወ ትርጉም ዘዴን መሠረት አድርገው በሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎችም በቋንቋው ቅርጽና ህግ ላይ ብቻ ያተኮሩ ነበሩ ይላሉ። በጊዜውም ቋንቋን መማር ማለት ሰዋስዋዊ ህጉን አውቆ መተንተን መቻል ተደርጎ ይታሰብ ነበር።

ይሁን እንጂ ዘመናዊው የሰዋስው ትምህርት እሳቤ ሰዋስው ከቅርጽና ከህግጋት ትምህርት በተጨማሪ ተግቦቦትን የሚያቅፍ መሆን ይገባዋል (ጌታሁን፣ 1989) የሚል በመሆኑ "በሰዋስዋዊ ቅርጾችና ህግጋት ላይ ማተኮር አለበት" የሚለው እሳቤ ተቀባይነት እያጣ መጥቷል። በመሆኑም የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ቅርጽ ወይም መዋቅር ላይ ብቻ ሣይሆን በፍቺና አጠቃቀም ላይ ጭምር መሆን እንደሚገባው Cook (2001) እና Larsen Freeman (1991) ያስገነዝባሉ። ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቅሱት የአንድ ቋንቋ ቅርጽ የቋንቋውን ተዋቃሪ ቅንጣቶች አደረጃጀትና አወቃቀር ብቻ የሚያሳይ ሲሆን ፍቺ ግን መዋቅሩ የያዘውን ትርጉም ያስገነዝባል የሚል ነው። አጠቃቀም ደግሞ የቅርጽና ፍቺ ውህድ የሆነው አሃድ አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ገጽታ ያሳያል።

Palmer (1984) እንዲሁ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋስዋዊ እውቀት ላይ የተመሠረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል በመሆኑ የቋንቋውን ቅርጽ ከፍቺና አጠቃቀም ጋር አጣምረው መማር ይገባቸዋል ። ይህም ተገቢ የሆኑ ዐረፍተ ነገሮችን በመመስረት በንግግር ወይም በጽሁፍ ሃሣባቸውን በሥርዓት እንዲገልጹ ያሽችላቸዋልና ነው በማለት ሃሣቡን ያጠናክሩታል።

የቀረበው ገለፃ የሚያስረዳን የሰዋስው ትምህርት ከቅርጽ ወይም መዋቅር በተጨማሪ ለፍቺና ለአጠቃቀም ትኩረት መስጠት እንደሚኖርበት ነው።

Ellis (2000)ም በበኩላቸው "የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎቹ የሚማሩትን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓት በሚገባ ተረድተው በተግባቦት ወቅት ሥርዓቱ አገልግሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚያሳይ እንደመሆኑ መጠን ሰዋስውና ተግባቦት ተነጣጥለው

መታየት የለባቸውም ::" ይላሉ። በመሆኑም ለተቃና ተግባቦት ሰዋስዋዊ እውቀት አሥፈላጊ መሆኑ ከታመነበት በቅርጽ፣ በፍቺና በአጠቃቀም ላይ ማተኮር ይገባዋል።

በአጠቃላይ የምሁራኑ ማብራሪያና ገለፃ የሚነግረን በቋንቋ ተግባር በሚገባ ተጠቃሚ ወይም ተገልጋይ ለመሆን የቋንቋው፣ የቅርጽ፣ የፍቺና የአጠቃቀም እውቀት ሊኖረን የሚገባ መሆኑን ነው። በተጨማሪም የተዘረዘሩት ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ተነጣጥለው የሚገኙ ያለመሆናቸውና የሰዋስው ትምህርትም ማተኮር ያለበት በእነዚሁ ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ መሆኑን ነው።

2.3. የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት እና ይዘቶች አቀራረብ

2.3.1 የሰዋስዉ ትምህርት አስፈላጊነት

የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ከሚኖራቸው የቋንቋ ክህሎት ጎን ለጎን የቋንቋውንም ሥርዓት እንዲገነዘቡ ለማድረግ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ስለሆነም ከቋንቋ ትምህርት የተሟላ ውጤት ለማግኘት ከቋንቋው የክሂልና ሌሎች የእውቀት ዘርፎች ጋር የሰዋስውንም ትምህርት አብሮ ማስተማር ያስፈልጋል።

በርግጥ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በርካታ ዘመናትን ያስቆጠረ ክስተት ቢሆንም ትኩረቱ ግን በጊዜ ሂደት የተለያየ ነበር። Richards እና Rodgers (1995:3) "በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በየዘመኑ የተነሱ ፍልስፍናዎችና ይህንንም ፍልስፍና መሠረት አድርገው የሚመነጩት የማስተማሪያ ዘዴዎች" ለተባለው ልዩነት ምክንያት እንደሆኑ ጠቁመዋል።

ቋንቋን በማስተማር ረገድም የሰዋስውን ሚና ወይም አስፈላጊነት የሚደግፉም፣ የሚቃወሙም ወገኖች በተለያዩ ዘመናት ተከስተው ነበር። የእነዚህ ወገኖች አመለካከት በጥቅሉ ሲታይ ሦስት ገጽታ የነበረው ሲሆን የመጀመሪያዎቹ፣ በቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር መርሐ ግብር ውስጥ "ሰዋስው በትምህርትነት መሠጠት አለበት" የሚል አቋም የነበራቸው ሲሆኑ በእነዚህ አመለካከት አራማጆች እምነት የቋንቋ ትምህርት ዓላማም ሆነ ግብ "የተማሪዎችን ሰዋስዋዊ ብቃት ማዳበር" ጭምር ሥለሆነ መሠጠቱ የግድ ነው የሚል ነው። ሁለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ ይህንን ሃሣብ በመቃረን የቋንቋ ትምህርቱ "ከሰዋስው ይልቅ ለተግባቦት" ቦታ የሚሠጥ መሆን እንዳለበት

የሚሞግቱ ናቸው። በዚህም መሠረት የሰዋስውን በትምህርትነት መሠጠት አጥብቀው ይነቅፋሉ። ሦስተኛዎቹ ወገኖች ግን የሁለቱን ተቃራኒ ቡድኖች ሀሳብ በማስታረቅ "ሰዋስዋዊ ይዘቶች እና ተግባቦታዊ ክንውኖች ተዋህደው መቅረብ ያለበቸው" መሆናቸውን የሚመክሩ ናቸው (Stern 1992)።

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ተቀባይነት ያለው አመለካከት የሦስተኛዎቹ ወገኖች አሥታራቂ ሃሣብ ነው። ምክንያቱ ደግሞ የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥም ሆነ በመማሪያ መፀህፍቱ ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ የቋንቋውን ህግ ብቻ በመተንተን ላይ አተኩሮ ሳይሆን፣ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ፍቺ፣ አገባብና፣ አጠቃቀም ጭምር አዋህደው በማቅረብ ተማሪዎች መለማመድ አለባቸውና ነው።

በዚህም መሠረት የሰዋስው ትምህርትን አስፈላጊነት በተመለከተ Ur (2008፡4-5) በአንድ ቋንቋ በአግባቡ ለመገልገል ከቋንቋው ተጠቃሚ የሚጠበቀው ሥርዓቱን ማወቅና በተግባቦት ጊዜም ጥቅም ላይ የሚያውለው የሰዋስው ችሎታ ሊኖረው እንደሚገባ በመግለጽ የአንድን ቃላት ቋንቋ ብቻ ማወቅ በቂ ያለመሆኑንና ይልቁንም ቃላቱ ተቀናጅተው ሰፊ አሃድ (መዋቅር) የሚመሠርቱበትን መንገድ ተገንዝቦ መገልገል እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ። ከቀረበው ገለፃ የምንረዳው በአንድ ቋንቋ በአግባቡ ለመገልገል የሰዋስው እውቀትና እውቀቱንም ተግባራዊ የማድረግ ችሎታ አስፈላጊ መሆኑን ነው።

Cunningsworth (1984:18) ደግሞ ሰዋስውን ያላከተተ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የተሟላ ነው ለማለት አያስደፍርም ሲሉ Harmer (1987:4-5) በበኩላቸው ዛሬ ዛሬ በቋንቋ ትምህርት ረገድ ተማሪዎች በቋንቋ ተግባራት መጠቀምንና ይህንን ለማድረግ ይረዳቸውም ዘንድ የቋንቋን ሰዋስዋዊ መሠረት ጭምር መማር እንደሚፈልጉ የሚያሳይ ሁኔት መሆኑን ጭምር ገልፀዋል።

ባየ (1987፡10) እንዲሁ ከአንድ የቋንቋ ተማሪ የሚጠበቀው ችሎታ ሁሉን አቀፋዊ የክህሎትና የሥርዓት ቅንጅት መሆን እንዳለበት በመግለጽ የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከሥርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የበለጠ እውቀት ያለው መሆኑን ጠቁመዋል።

ጌታሁን (1989) በበኩላቸው ሰዋስው ከሀግጋት ትምህርት በተጨማሪ ለተግባቦታዊ ተግባር ፋይዳ ያለው መሆኑን ያስገነዘቡ ሲሆኑ Ur (1986፡88) ም ሰዋስውን መማር የምንማረውን ቋንቋ በሚገባ ለመካን የሚረዳ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው በማለት የአስፈላጊነቱን ደረጃ አሳይተዋል።

ገለፃው የተሟላ የቋንቋ እውቀት ኖሮን ተግባቦታዊ ችሎታችን የሠመረ እንዲሆንልን ከሚያስፈልጉን ግብዓቶች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት መሆኑን የሚጠቁም ነው።

በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት ከቋንቋው የሥርዓት ትምህርት (ሰዋስው) ተነጥሎ ሊቀርብ የሚገባው አለመሆኑንና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ወሳኝ ሥፍራ ያለው መሆኑን ይስማሙበታል።

Brown (1994) የቋንቋ ትምህርት የተማሪውን ክህሎት ከማዳበር ባሻገር ተማሪው ሊገነዘበው የሚገባውን ሰዋስዋዊ እውቀት ጭምር ማካተት ይኖርበታል። ይህም የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ወቅት ከተግባቦት በተጨማሪ የአጠቃቀም ሥርዓቱን ማስተማር አሥፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የቋንቋ እውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግባቦታዊ አገልግሎቱን ከሥርዓቱ ጋር አቀናጅቶ በመገንዘብ በመሆኑ ሰዋስውን የማስተማር ተገቢነት መካድ የሌለበት መሆኑን ያስገነዝባሉ።

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለፃዎች የምንገነዘበው ምንም እንኳን የቋንቋ ትምህርት ግብ ተማሪዎችን የሥነ ልሣን ባለሙያ ማድረግ ባይሆንም አጠቃላይ የሆነውን የተግባቦት ችሎታቸውን ለማበልፀግ ትምህርቱ ማተኮር ያለበት በክሂል ላይ ብቻ ሣይሆን በሥርዓትም ላይ ጭምር መሆኑን ነው። ምክንያቱም "ሁለቱም ችሎታዎች ተማርኩ ከሚል ሠው የሚጠበቁ ናቸውና (ጌታሁን 1989)።

በመሆኑም በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓትን ጠብቆ በአግባቡ ለመገልገል፣ የቋንቋውን ህግጋትና ባህሪያት ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑና ይህንንም የቋንቋውን ሥርዓትና ባህሪያት የማያሳይ ሂደትን የተከተለ አካሄድ የተማሪውን የቋንቋ ብቃት የተሟላ ሥለማያደርገው፣ የሰዋስውን ትምህርት ማስተማር ችላ ሊባል የሚገባው ጉዳይ አይደለም።

2.3.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተሠጥቶት መቅረብ እንዳለበት ቀደም ሲል ለመግለጽ ሞክረናል። ይህ የትምህርት ይዘት በትምህርት ልምድነት ሲመረጥ ሥርዓተ ትምህርቱንና መርሐ ትምህርቱን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

ሥርዓተ ትምህርቱንና መርሐ ትምህርቱን መሠረት አድርገው የሚዘጋጁት የመማሪያ መፃህፍት ደግሞ ተገልጋዩን ወይም ተማሪውን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ይህም ማለት የተማሪውን ዕድሜ፣ ስብዕና፣ የመጣበትን አካባቢ እንዲሁም ድክመት እና ጥንካሬውን ሁሉ ማካተት እንደሚገባቸው Cunningsworth (1984:30) ያስገነዝባሉ።

በዚህ መልኩ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የሚካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ መከተል የሚገባቸው የማቅረቢያ መርሆዎች አሏቸው። በርግጥ እነዚህ መርሆዎች አጠቃላይ የሆነ ሥነትምህርታዊ ገጽታ ያላቸው ናቸው። ይሁን እንጂ የሠዋስው ትምህርት አቀራረብ ከእነዚህ መርሆዎች የራቀ አይደለም።

የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ በማቅረብ ሂደት ለአቀራረብ መርሆዎች ትኩረት መሥጠት የሚኖርብን ያለምክንያት አይደለም። ምክንያቱም አንዳንድ የትምህርት ይዘቶች ከባድና ውስብስብ ቢሆኑም እንኳን አቀራረባቸው ግልጽ እና ስልታዊ ከሆነ ተማሪዎቹ ያለችግር ሊገነዘቧቸው ሲችሉ፤ ነገር ግን የቱንም ያህል ቀላል የሚመስሉ ይዘቶች፣ አቀራረባቸው ግልጽነት ከጎደለው ለተማሪዎቹ ከባድና አስቸጋሪ ከመሆናቸውም በላይ የመማር ተነሳሽነታቸውንም ጭምር ሊያዳክሙ እንደሚችሉ አያጠራጥርምና ነው።

በመሆኑም የትኞቹም የትምህርት ይዘቶች (ሰዋስውንም ጨምሮ) በአግባቡ መቅረብ ይኖርባቸዋል። በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚቀርቡባቸውን መርሆዎች በሚመለከት ምሁራኑ ከሚከተሉት የትምህርት ፍልስፍናና የሙያ መስክ አንፃር የተለያዩ አመለካከቶችን ያንፀባርቃሉ። ይሁንና በአቀራረብ ውስጥ መታየት ከሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች፣ ተማሪዎች ምን መማር እንደሚኖርባቸው ፣ የታለመው ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ እንዴት መሄድ እንዳለበት፣

የትምህርቱ ተገቢነትና ተተግባሪነት ምን ያህል እንደሆነ አጽንኦት መስጠት መሆናቸውን (Rutherford 1987:147) ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በHarmer (1987:18) እንደተጠቆመው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች የመማር ሂደት ላይ ችግር የማይፈጥር፣ ጥሩ፣ ውጤታማ፣ ተወዳጅ እና ስሜት የሚስብ መሆን ይገባዋል። እንደ Stern (1992:128) ገለፃ ደግሞ የሠዋስው ትምህርት በተለያዩ የአቀራረብ መንገዶች ላይ መመስረት ይኖርበታል። ይህም እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት የቋንቋውን አውድ በሌላ መንገድ ከመጠቀም ዓላማና ሥርዓት ባለው ጥናትና ልምምድ ማስተማር ስለሚያስፈልግ ነው ይላሉ።

በድምሩ ምሁራኑ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እንደ ትምህርቱ ድብልቅነትና እንደተማሪው ማንነት መቅረብ እንደሚኖርበት እየመከሩ ሰዋስው ከሚቀርብባቸው የተለያዩ የአቀራረብ ዘዴዎች መካከል አንዱን ብቻ መርጦ መጠቀም ትክክል ያለመሆኑን በአጽንኦት ይጠቁማሉ። ስለዚህ ደግሞ በምክንያትነት የሚያቀርቡት በአሁኑ ወቅት ተቀባይነት ያለው ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባቦታዊ አቀራረብን ተጠቅሞ ማስተማር ውጤታማ ያደርጋል የሚለውን ሃሣብ የተከተለ በመሆኑ ነው። በዚህም መሠረት ቀጥለን የአቀራረብ መርሆዎችን በዝርዝር ለመቃኘት እንሞክራለን።

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የማቅረቢያ መርሆችዎን በተመለከተ በባለሙያዎቹ ዘንድ በአብዛኛው ተቃራራቢነት ባላቸው ጽንሰ ሃሣቦች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሆነው እናገኛቸዋለን። በዚህም መሠረት እንደ Bygate et. al, (1984:22), Cunningsworth (1995:99), Larsen Freeman (1991:292) እና Harmer (1991:18) አገላለጽ የሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮር እና በጥምረታዊ አቀራረብ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

2.3.2.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት ሰዋስዋዊ ህጉ በግልጽ ተብራርቶና በምሳሌ ታግዞ ከቀረበና ገለፃ ከተደረገበት በኃላ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ገለፃና ዝርዝር ምሣሌ መሠረት በማድረግ

መልመጃዎቹን እየሰሩ ትክክለኛውን የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲገነዘቡ የሚያደርግ አካሄድ መሆኑን (Cunningsworth 1995:99) ይገልጻሉ።

ከተጠቃሾቹ ምሁራን ገለፃ የምንረዳው በዚህ የማቅረቢያ ስልት መርህ መሠረት ሰዋስዋዊ ህግጋቱ በቀጥታ ለተማሪዎቹ የሚቀርቡ መሆናቸውን ነው። ይህም ማለት በእያንዳንዱ ሰዋስዋዊ መዋቅር የቅርጽ ልዩነት ላይ ግልጽ ትንተና ይሠጣል። የሥልቱ ዓላማም ተግባቦትን ማከናወን ሳይሆን ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ የቃል ክፍሉን፣ ሀረጋቱንና አረፍተ ነገሮቹን እንዲለዩ ማስቻል ነው። በዚህ ስልት ተማሪዎቹ አንዳንዴ ተግባቦታዊ ተግባራትን የሚያከናውኑበት አጋጣሚ ቢኖርም መምህሩ ጣልቃ በመግባት ስህተት እንዳይሰሩ ቁጥጥር የማድረግና ምጋቤ ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት (Cunningsworth 1984:32-33)። በWoods (1995:76-77) ገለፃ መሠረት ሥልቱ የሚታወቅባቸው የሚከተሉት ጠንካራና

ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል:-

- ሰዋስዋዊ ህግጋቱን በቀጥታ የሚያቀርብ በመሆኑ ጊዜ ይቆጥባል፤
- ተማሪዎቹ ህግጋቱን ከተረዱ በኋላ ምሳሌ ያቀርብላቸዋል፤
- የማገናዘብ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመማር ስልት ያጠናክራል።

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ የአቀራረብ ሥልቱ ደካማ ጎኖች ከሚባሉት ውስጥ ደግሞ ቀጥለው የተዘረዘሩት ተጠቃሾች ናቸው።

- ህግጋቱን በቀጥታ በመግለጽ የሚጀምር በመሆኑ በተለይ ለህፃናት ይከብዳቸዋል፤
- የትምህርቱ አቀራረብ በመምህሩ የሚመራ በመሆኑ የተማሪዎቹን ተሣትፎና የእርስ በእርስ ግንኙነት ይገድባል፤
- የህግጋቱ ገለፃ በተግባቦት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ የመታወስ እድሉ አናሳ ነው፤
- የማቅረቢያ ሥልቱ "ቋንቋን መማር ማለት ህግጋትን ማወቅ ነው" በሚለው ጥንታዊ እሳቤ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለተግባቦት ተገቢውን ቦታ የነፈገ ነው።

የሚሉት ይገኙባቸዋል።

2.3.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ሥልት የመጀመሪያው ግልባጭ ነው። ስልቱ በጥንቃቄ የተመረጡ ምሳሌዎችን በማቅረብ በእነዚያ ምሳሌዎች መሠረት ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን ከሠሩ በኋላ ህግጋቱን በራሳቸው እንዲደርሱባቸውበት የሚያደርግ አካሄድን የተከተለ መሆኑን (Cunningsworth 1995፡99) ይገልፃሉ።

በመሆኑም የአቀራረብ ሥልቱ ተማሪዎቹ ከቋንቋው ዝርዝር ተነስተው አጠቃላይ ወደሆነው የቋንቋው ህግ እንዲሸጋገሩ የሚያስችል አካሄድን የሚከተል መሆኑን (Larsen Freeman 1991) ይጠቁማሉ። Nunnan (1991) በበኩላቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚደረግ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው ህግ በቀጥታ ከመማራቸው በፊት ከዝርዝር ትምህርቱ ተነስተው በራሳቸው የመረዳት አቅም የቋንቋውን ህግ ሊያውቁ የሚችሉበት የትምህርት አቀራረብ ነው። በመሆኑም በዚህ የአቀራረብ ሥልት መሠረት የቋንቋው ሰዋስዋዊ ህጎች በቀጥታ ለተማሪዎቹ አይቀርቡም።

እንደመጀመሪያው ሁሉ ይኸኛውም የአቀራረብ ስልት የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት

ጠንካራ ጎኖቹ፡-

- ተማሪዎቹ ከሚቀርቡላቸው ምሳሌዎች ተነስተው ህግጋትን እንዲያወጡ ስለሚጋብዛቸው በነፃነት የመማርና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤
- አዕምሯቸውን በሥፋትና በጥልቀት እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል፤
- የመማር ፍላጎታቸውን ያነሳሳል፤
- የችግር አፈታት ችሎታቸውን ያዳብራል፤ እና
- የእርስ በእርስ መስተጋብርን ስለሚፈቅድ ለቋንቋ ክሂሎች መዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

የሚሉት የሚጠቀሱ ሲሆኑ ስልቱ ከሚታማባቸው ደካማ ጎኖች መካከል ደግሞ የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው

- ጊዜና ጉልበት ያባክናል፤
- ሰዋስዋዊ ህግጋቱ ለተማሪዎቹ መጀመሪያ ላይ ስለማይቀርቡ ተማሪዎቹ ወደ ተሳሳተ ግንዛቤ እንዲያመሩ ሊያደርግ ይችላል፤
- በህግጋት ትንታኔ መማር የለመዱ ተማሪዎችን ግራ ሊያጋባ ይችላል።

የሚሉት ናቸው።

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳችው ጥንካሬና ድክመት ታይቶባቸዋል። በተለይም አንዱ አቀራረብ የሌላኛው ግልባጭ ከመሆኑ የተነሳ የአንዱ ጥንካሬ የሌላው ድክመት ሆኖ ታይቷል። በመሆኑም አንደኛው የሌላኛውን ክፍተት የሚሞላ መሆኑን ተገንዝቦ እንደ አስፈላጊነታቸው ሁለቱንም አቀራረቦች እያፈራረቁ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደ መሆናቸው መጠን የተለያየ የትምህርት አቀባበል ችሎታ፣ የመማር ስልት ምርጫ ወዘተ ያላቸው መሆናቸውም ልብ ሊባል ይገባል። ይህም ብቻ ሣይሆን የተለያዩ የትምህርት ዓላማዎች፣ የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን የሚከተሉ ከመሆናቸው የተነሳ እነዚህንና መሠል ሁነቶችን ለማቻቻል እንደየሁነቱ ሁለቱንም የአቀራረብ መርሆዎች በተገቢው ሁኔታ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን (Harmer 1987) ያስገነዝባሉ።

2.3.2.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለው የቋንቋ ቅርጽ ላይ መሆኑን Batestone (1994:51) ይናገራሉ። ይህም ማለት ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የአረፍተነገር አመሠራረት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግን ትኩረት ያደረገ የአቀራረብ ዘዴን የሚከተል ነው። በመሆኑም ሥልቱ ተማሪዎቹ የሰዋስው አሃዶችን ነጥለው በመተንተን በቋንቋው ዝርዝር ህግ ላይ ተመሥርተው ትክክለኛ አረፍተነገሮችን እንዲያፈልቁ የሚያስችላቸው ነው።

ይሁን እንጂ የአቀራረብ ስልቱ ልማዳዊ የሆነ የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርህን የተከተለ፣ በመፃህፍት ላይ የተመሠረተና በቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ የሚተቹት ወገኖች ይበዛሉ። ምክንያቱም በዘዴው የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ተግባቦት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው እንዲለዩ፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተ ነገራትን በተናጠል እንዲተነትኑ እና እንዲመሠርቱ በማድረግ ላይ እንጂ እነዚህን ቅርጾች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዷቸው የሚያስችል አይደለምና ነው። በሌላ በኩል ግን ለማስተማር ሥራ ፈጣን መሆኑ፣ ለመምህሩ ትምህርት አሠጣጥ ቀላልና ምቹ መሆኑ ደግሞ ከጠንካራ ጎኑ የሚጠቀሱለት ናቸው።

Harmer (1991) እና Batestone (1994) የአቀራረብ ስልቱን ጥንካሬና ድክመት በሚከተለው መልኩ አስፍረውታል።

- ግብዓቶችን መርጦና አደራጅቶ ማቅረቡ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ ቅርጽ ላይ መገደቡና
- የጽንሰ ሃሣብ ግንዛቤ ማስጨበጡ

ከጠንካራ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ሲሆኑ፤

- ይዘቶችን በመምረጥና በማደራጀት ሂደት የተማሪውን ፍላጎት መሠረት ያለማድረጉ፣
- ለቅርጽ እንጂ ለፍቺ ትኩረት ያለመስጠቱና
- ድርጊታዊ የማስተማሪያ ስልትን ያለመጠቀሙ

ደግሞ ከደካማ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ናቸው።

2.3.2.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት የውጤት ተኮር ግልባጭ ነው። ዓላማው ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋልን የሚመለከት ነው። (Batestone 1994:51) ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በቋንቋው ይበልጥ እንዲገለገሉበት፣ ማለትም በአውድ ውስጥ ትርጉም ሰጪ የሐሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማድረግ የቋንቋውን ቅርጾች

ይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል አቀራረብ መሆኑንም ይገልፃሉ። ከዚህ የምንረዳው ስልቱ ተማሪዎቹ በራሳቸው አውዶች ማለትም ከራሳቸው ገጠመኝ፣ ዳራዊ እውቀት በመነሳት ሰዋስዋዊ ህግጋትን በራሳቸው ጥረት እንዲገነዘቧቸው የሚያደርግ አካሄድን የሚከተል መሆኑን ነው።

ይህ ስልት እንደ ላይኛው ሁሉ የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት። ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል በጉልህነት የሚጠቀሱት ተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍቺና አጠቃቀም ተገንዝበው በቋንቋው መገልገል እንዲችሉ ማድረጉ ሲሆን፣ ከደካማ ጎኖቹ መካከልም፡-

- ለፍቺ ብቻ እንጂ ለቅርጽ ትኩረት ያለመሥጠቱ፣
- ሰዋስዋዊ ስርዓቶችን ለተማሪዎቹ መርጦና አደራጅቶ ያለማቅረቡ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪዎችን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ላይ አለመገደቡና
- የጽንስ ሃሣብ ግንዛቤ ሳያስጨብጥ ተማሪውን በጭፍን ወደ ተግባቦት ልምምድ ውስጥ ማስገባቱ

ተጠቃሽ መሆናቸውን (Batestone 1994) ያስገነዝባሉ።

በውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች መካከል መሠረታዊ የሆኑ ልዩነቶች መኖራቸውን ከገለፃው መረዳት ይቻላል። ምክንያቱም የመጀመሪያው በቅርጽ ላይ ሲያተኩር ሁለተኛው ደግሞ በአጠቃቀም ላይ ያተኮረ ነውና። ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው ድክመትና ጥንካሬ ታይቶባቸዋል።

Batestone (1994:5) ከ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ሁለቱንም አቀራረቦች በማቀናጀት ማቅረብ በሥፋት እየተሠራበት መሆኑን በመጠቆም፣ ይህም ቅንጅታዊ ስልት በተናጠል ሲሰራባቸው በነበሩት ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ላይ የተመሠረተ መሆኑንና የሠዋስው ትምህርትም ለቅርጽም ሆነ ለአጠቃቀም ትኩረት መስጠት ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ እንደሆነ ያስረዳሉ።

በመቀጠልም የትምህርቱ አቀራረብም በቅርጽ ላይ ከሚደረግ የጽንስ ሃሣብ ማስጨበጥ ልምምድ ተነስቶ በተገቢው ሁኔታ ወደ አውዳዊ የተግባቦት ልምምድ ሊሸጋገር እንደሚገባውና የተማሪዎችም ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ወይም ቅርጽ ላይ መገደብ እንዳለበት ወይም የተወሰነ አላማን ይዞ መነሳት እንዳለበት ይገልፃሉ።

ተማሪዎች በተማሯቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ልምምድ ሲያደርጉ በቂ ቁጥጥር ካልተደረገባቸው የተነሱበትን ሰዋስዋዊ ቅርጽ እየተውት ሊሄዱ እንደሚችሉና ይህም በውጤት ተኮር የሚቀርበው ሰዋስው ወደ ሂደት ተኮር የሚገባበትን እድል እንደሚወስነው (Batestone1994:52) ያስገነዝባሉ።

ከዚህም የተነሳ ተማሪዎች በተገቢው መንገድ እውቀቱን ሊያቀናጁ ባለመቻላቸው በሁለቱ አቀራረቦች መካከል ክፍተት ሊፈጠር ስለሚችል፣ ይህንን ክፍተት ለመሙላት "ጥምረታዊ አቀራረብን መተግበር" እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

2.3.2.5. ጥምረታዊ አቀራረብ

እንደ Batestone (1994) አገላለጽ ይህ የአቀራረብ ስልት ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልቶችን ለማስተሳሰርና በመካከላቸው ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል የአቀራረብ ስልት ነው። ስልቱ የተመሠረተው ተማሪዎች በውጤት ተኮር አቀራረብ የሚማሩትን የቋንቋ ቅርጽ የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ ተግባራዊ ልምምዶችን እያደረጉ በአገልግሎት ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል በሚለው እሳቤ መሠረት ላይ ነው። በመሆኑም የዚህ አቀራረብ ዋነኛ ዓላማ ተማሪዎች ጥንቃቄና ቁጥጥር ከተሞላበት (ውጤት ተኮር አቀራረብ) ወደ ውጤታማ የቋንቋ አጠቃቀም (ሂደት ተኮር) የሚያደርጉትን እድገት ማገዝ ነው።

በአጠቃላይ በጥምረታዊ አቀራረብ ሂደት ተማሪዎች ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን እንዲከታተሉ የሚጠበቅባቸው ሲሆን በሠዋስው ላይ የተመሰረቱ ተግባራትንም በሚሠሩበት ጊዜ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ትኩረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የክለሳ ድርሳናቱ ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ይህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነትና ዝምድና ባላቸው ሦስት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን መሠረት በማድረግ ዝርዝር ትንታኔ

ቀርቦበታል። ጥናቱ የሚያተኩረው በተተኳሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ምን ገጽታ እንደነበረው እና እንዳለው በመቃኘት ከሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው መርሆዎች አንጻር በጊዜ ሂደት የታየውን ለውጥና መሻሻል ወይም አለመሻሻል መገምገም በመሆኑ በዚህ ምዕራፍ ውስጥም በእነዚሁ ጉዳዮች ላይ የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ተደርጎባቸዋል።

በዚህም መሰረት በተዛማጅ ቅኝቱ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ የቀረቡት ከመማሪያ መፃህፍት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም ክፍሉ ስለቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት፣ ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳና አይነቶች ማብራሪያ ቀርቦበታል።

የምዕራፉ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ከሰዋስውና ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ጋር ዝምድና ባላቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረግ ሲሆን በንዑሳን ክፍሎቹ ውስጥም የሰዋስው ምንነት፣ የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ምንነት፣ የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች ባህሪያትና የይዘት ትኩረት፤ እንዲሁም አስፈላጊነት በሚሉት ላይ ፍተሻ ተደርጎባቸዋል።

በምዕራፍ የመጨረሻውና ሦስተኛው ክፍልም እንዲሁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሚቀርቡበት ጊዜ ሊከተሏቸው ስለሚገቧቸው የአቀራረብና የአደረጃጀት መርሆዎች ቅኝት የተደረገባቸው ናቸው።

በተለይም ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዓላማ፣ ተተኳሪዎቹን የመማሪያ መፃህፍት ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የማቅረቢያ መርሆዎች አንፃር የታየውን ለውጥ መመርምር በመሆኑ ግምገማው የሚደረግባቸውን የማቅረቢያ መስፈርቶች ትኩረት በመስጠት ለመቃኘት ተሞክሯል።

በመጨረሻም በቀጣዩ የጥናቱ የትንታኔ ክፍል (ምዕራፍ አራትም) የመተንተኛ መስፈርቶች ሆነው የሚያገለግሉት እነዚሁ በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱት የአቀራረብ መርሆዎች መሆናቸውን ከወዲሁ ለመጠቆም እንወዳለን።

2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርእስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መልኩ ዝምድና ያላቸውን ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎች ለመቃኘት ተሞክሯል። ቀደምት ሥራዎቹ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ሆነው የቀረቡ በመሆናቸው በአይነት በአይነታቸው ይዳሰሳሉ።

ከመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ሥራዎች መካከል ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተዘዋዋሪ ዝምድና ካላቸው ጥናቶች መካከል የሁሉባንተ (1994)፣ ሰለሞን (1987)፣ ስሜ (1996) አስካለ (1992)፣ እንደገና (1994)፣ ኪዳን (1993)፣ ካሣሁን (1995)፣ ውድ አዲስ (1994) ይገለጡ (1988) እና ዮሀንስ፣ (1993) ተጠቃሾች ናቸው። ከእነዚህ መካከል ዮሀንስ፣ ይገለጡ፣ አስካለና ሰለሞን በሁለተኛ ደረጃ የመማሪያ መጻህፍት ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የተቀሩት በአንደኛ ደረጃ የመማሪያ መፃህፍት ላይ ያተኮሩ ናቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ የመማሪያ መፃህፍት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ያተኮሩት የጥናት ስራዎች በየክልሎቹ በተዘጋጁት የአማርኛ መፃህፍት እና በየክልሎች የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች በተዘጋጁት መፃህፍት ላይ ከማተኮራቸው በስተቀር የአቀራረብ ስልታቸውና የምርምር አካሄዳቸው ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ ስራ ጋር የቀረበ ዝምድና አላቸው የሚባሉት ያዮሀንስ፣ ይገለጡ፣ አስካለና ሰለሞን ሥራዎች በ9ኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሰዋስው ትምህርት ግምገማ ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የእይታ አድማሳቸው በሰዋስው ትምህርት አመራረጥ እና አደረጃጀት ላይ እንጂ በአቀራረብ ላይ ያነጣጠሩ አልነበሩም። ከዚህ በተጨማሪ በተተኳሪው መማሪያ መፅሐፍ ላይ ከማተኮር በዘለለ የንጽጽርም ሆነ በጊዜ ሂደት ስለታየ ለውጥ ያሉት ነገር የለም። ይሁን እንጂ ማዕከላዊ የማጠንጠኛ ነጥባቸው የሰዋስው ትምህርት በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ የሚመረምሩ በመሆናቸው እርስ በርሳቸውም ሆነ ከዚህ ጥናት ጋር ይዛመዳሉ።

በሌላ በኩል ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችም ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል የተስፋዬ በቀለ "በ(1993) ዓ.ም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል ኢ-አፍ-ፊት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት ተጠቃሽ ነው።

ተስፋዬ በጥናቱ ትኩረት የሰጣቸው ጥያቄዎችም በመልመጃ ውስጥ የቀረቡት የቋንቋ ክፍሎች ቅርፃዊ ሥርዓትና ፍቺ ይዘው ቀርበዋልን? ትኩረት የተሠጣቸው የሰዋስው ግብዓቶች አደረጃጀታቸው ምን ይመስላል? የሚሉ ነበሩ። ከመጠይቅና ከሠነድ ምርመራ ባገኘው መረጃ መሠረትም የሰዋስው መልመጃዎቹ ለታላሚው ቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትና ለፍቺው ሚዛናዊ ትኩረት እንዳልሠጡ፣ ግብአቶቹም በአብዛኛው ከጥቅል ሰዋስዋዊ ባህሪ ወደ ዝርዝር ባህሪ የሚሄዱ ያለመሆናቸውን እንደ ችግር አንስቷቸዋል። በመጨረሻም የታዩት ደካማ ጎኖች የሚሻሻሉበትን አቅጣጫ በመጠቆም ጠንካራ ጎኖቹም ሊበረታቱ እንደሚገባ የመፍትሄ ሀሣቡን አቅርቧል።

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው የኢያሱ መሠለ (2003) ጥናት ነው። ኢያሱ "በ1997 ዓ.ም በተሻሻሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሥነ ትምህርትዊ ሰዋስው ይዘት አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል ጥናት አቅርቧል። የኢያሱ ጥናት ዓላማ በተተኳሪዎቹ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ያለውን ደካማና ጠንካራ ጎን መጠቆም ነው።

ጥናቱንም ከዳር ለማድረስ ከጽሁፍና ከቃል መጠይቅ በተጨማሪ የሰነድ ምርምር በማድረግ ወደ ጥናቱ ማጠቃለያ ደርሷል። በውጤቱም የሠዋስው ትምህርት ይዘቶች ከቋንቋው ሰዋስዋዊ ክፍሎች የተወጣጡ አለመሆናቸው፣ የግልጽነት ችግር የሚስተዋልባቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያልተዛመዱ እንደሆኑ፣ ከተከታታይትና ከተለጣጣቂነት አንፃርም ክፍተት ያለባቸው መሆናቸውን እና የአቀራረብ ችግር እንደ ተስተዋለባቸው በመጠቆም መፍትሄ ያላቸው ሃሣቦችን ሠንዝሯል።

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) በበኩሉ "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ያቀረበው ጥናት ተጠቃሽ ነው። የጥናቱ አላማ የተጠቀሱት ሁለት ክልሎች በሚጠቀሙባቸ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በማነፃፀር ተመሳስሎና ልዩነታቸውን ነቅሶ ማውጣት ነው። ጥናቱን ከድምዳሜ ለማድረስም የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና የሰነድ ምርምራ የተጠቀመ

ሲሆን በውጤቱም ክልሎቹ መሠረት ያደረጉት አንድ አይነት መርሀ ትምህርት ቢሆንም በአቀራረብና በአደረጃጀታቸው መለያየታቸውን፣ በሁለቱም ክልሎች የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርሆዎችን አልሞ አለመተግበር፣ የጽንሰ ሃሣብ፣ የአርትኦትና ከመርሀ ትምህርቱ የመውጣት ችግሮች በጥናቱ ሂደት የተደረሰባቸው ግኝቶች መሆናቸውን ገልጿል።

እስሌማን (2003) እንደዚሁ "በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር" በሚል ርዕስ ጥናት አካሄዷል። የጥናቱ አላማ የነበረው በ1998 ዓ.ም ተሻሽሎ ሥራ ላይ በዋለው የ12ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀትና አቀራረብ ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር መገምገም የሚል ነው። በመሆኑም ጥናቱ የሰዋስው ይዘቶቹ አደረጃጀትና አቀራረብ ምን ይመስላል? ይዘቶቹ ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ምን ያህል ትኩረት ሰጥተዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያለመ ነበር። ላላማዎቹንም ከግብ ለማድረስ ቃለ መጠይቅ፣ የጽሁፍ መጠይቅና የሰነድ ምርመራን በመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴነት ተጠቅሟል። በመጨረሻም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከግልጽነት፣ ትክክለኛነት፣ ተገቢነት፣ ተከታታይነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ጥሩ ሆነው የተገኙ ሲሆኑ ይዘቶቹ የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ለፍቺና አጠቃቀም ትኩረት ያልሠጡ መሆናቸውን ጠቁሟል።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች መካከል የተስፋዬ፣ የሐዋዝና የእስሌማን ሥራዎች በርዕስ ጉዳያቸው ይመሳሰሉ እንጂ በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃ ይለያያሉ። ከዚህ በተጨማሪ ጥናቶቹ በተጠቀሰው ዘመን ያሉትን ወይም የነበሩትን መፃህፍት ይዘውት ከተነሱት መስፈርት አንፃር ከመፈተሽ ባለፈ የንጽጽርም ሆነ መጻህፍቱ በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥ አያሳዩም። ከመረጃ መሰብሰቢያ አንፃርም ጥናቶቹ መጠይቆችንና የሰነድ ምርምራን የተጠቀሙ ሲሆኑ ይህ ጥናት ግን በእነዚህና መሰል ተዛማጅ ጉዳዮች የተለየ ነው።

ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ተመሳሳይነት የሚስተዋልበት የኢያሱ 2003 ጥናት ነው። ኢያሱ በ1997 ዓ.ም በተሻሻሉት የ9ኛና የ10 ክፍል መማሪያ መፃህፍት የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘት አመራረጥ አቀራረብና አደረጃጀትን በተመለከተ የሠራው

ጥናት በርዕሰ ጉዳዩ እና በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች የሚመሳሰል ሲሆን ተጠኚዎቹ መማህፍትም በዚህ ጥናት የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ይሁን እንጂ የኢያሱ ጥናት ያተኮረው በሰዋስው ትምህርት ይዘት "አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት" ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን "አመራረጥ"ን እና "አደረጃጀት"ን አይመለከትም። ከሥነ ዘዴ አኳያ ኢያሱ መጠይቆችንና የሰነድ ምርመራን ሲጠቀም የኔ ግን መጠይቆችን አያካትትም።

ዋናውና መሠረታዊ ልዩነት ግን ኢያሱ በተጠቀሰው ዓ.ም ተሻሽለው የታተሙትን መማህፍት ብቻ የቃኘ ሲሆን ከዚያ በፊት ከታተሙት ጋር ለማነፀፀር አልሞከረም። ይህ ጥናት ግን ላለፉት ሰላሳስድስት አመታት ሥራ ላይ በዋሉት የመማሪያ መማህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በመፈተሽ የታየውን ለውጥ መመርመር ዓላማው በመሆኑ ከኢያሱ ጥናት በእጅጉ ይለያል።

እንግዲህ እስከ አሁን ያየናቸው ጥናቶች ከሰዋስው ትምህርት እሳቤዎች አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዝምድና ቢኖራቸውም፤ ይዘውት ከተነሱት የጥናት ዓላማ፣ ከመማሪያ መማህፍቱ የክፍል ደረጃ፣ ከታተመበት ዘመን፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ፣ ከአጠናን ዘዴ፣ ከጥናቱ አካሄድ ወዘተ አንፃር ፍጹም ተዛማጅ ወይም አንድ አይነት አይደሉም። በመሆኑም ይህንን ጥናት ቀደም ካሉት ጥናቶች የሚለዩት ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

የጥናቱ ርዕስ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ሥራ ላይ ባሉና በነበሩ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መማህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ያሳየውን ለውጥ የሚገመግም ሲሆን ጥናቱ በተተኳሪዎቹ የመማሪያ መማህፍት ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸው በመፈተሽ በጊዜ ሂደት ምን ለውጥ እንደታየ በመመርመር ላይ ያተኩራል። እስካሁን ያየናቸው ጥናቶች ግን በአንድ ወቅት ታትመው ሥራ ላይ በነበሩት መማህፍት ላይ ብቻ የተገደቡ በመሆናቸው የዚያን ወቅት የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ከመጠቆም በዘለለ በጊዜ ሂደት ያሣዩትን ለውጥ በመፈተሽ የገመገሙ ባለመሆናቸው ከዚህ ጥናት በእጅጉ ይለያሉ።

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዓላማ ከ1968 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩና ባሉ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን በመፈተሽ በጊዜ ሂደት የተስተዋለውን ለውጥ መገምገም ነው። በመሆኑም ጥናቱ ከምርምር ዘርፎች መካከል አይነታዊ የምርምር ዘዴን መሠረት ያደረገ ሲሆን በአቀራረቡ ደግሞ ገላጭ ስልትን ተከትሏል።

3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጮች በመሆን የሚያገለግሉት ከ1968 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ታትመው አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩትና ያሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ናቸው። በሰነድነት የሚፈተሹትም በተጠቀሱት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ናቸው። ግምገማው የሚካሄደው የሰዋስውን ትምህርት ይዘት አቀራረብን አስመልክቶ በክለሳ ድርሳናቱ ክፍል በሚቀርቡት ንድፈ ሃሳቦች መሰረት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ ከተተኳሪዎቹ መጻህፍት ውስጥ ተለይተው ከወጡ በኋላ ከአቀራረብ መርሆዎች አንጻር እንዴት እንደቀረቡና በጊዜ ሂደትም ያሳዩትን ለውጥና መሻሻል ወይም አለመሻሻል መመርመር ነው ።,

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

ማንኛውም አይነት ጥናት በሚካሄድበት ወቅት እንደ ምርምሩ አይነትና ባህሪ ተመራማሪው መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችለውን ሁነኛ ዘዴ መምረጥ ይገባዋል። በመሆኑም ይህ ጥናት ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ በመፈተሽ በጊዜ ሂደት የታየውን ለውጥ መመርመር በመሆኑ ይዘት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይችል ዘንድ በቂ መረጃ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ የታመነበት የሰነድ ፍተሻ (document Analysis) ነው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ያለው (1994፡196) መዛግብት በጽሁፍ መልክ ከተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የመረጃ

ምንጮች ሲሆኑ የታተመ ወይም ያልታተመ ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል መፃህፍት የመማሪያም ይሁኑ ሌሎች በዚህ ሥር የሚካተቱ መሆናቸውን ገልጿል።

3.3. የመማሪያ መፃህፍትና የክፍል ደረጃ አመራረጥ

የጥናቱ ትኩረት ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩትና ባሉት የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ እርከን በሆኑት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፃህፍት ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ክፍሎች ከዘጠነኛ እስከ አሥራሁለተኛ ሲሆኑ የሁሉም ክፍሎች የመማሪያ መፃህፍት በሙሉ በጥናቱ ውስጥ ቢካተቱ ሊበዙና ጥናቱን በቀላሉ እዳር ለማድረስ አስቸጋሪ ሥለሚሆን የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ብቻ ተመርጠዋል።

በእነዚህ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ መፃህፍት የመመረጣቸው ሌላው ምክንያት በሀገራችን አጠቃላይ ትምህርት ተብሎ የሚታወቀው ከአንደኛ እስከ አስረኛ ያለው የክፍል ደረጃ ነው። ዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች ደግሞ የአጠቃላዩ ትምህርት የማገባደጃ ክፍተኛ ደረጃዎች ናቸው። በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት በተሻለ ሁኔታ ይቀርብባቸዋል የሚል እምነት ሥላለ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ከተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች በላይ ወይም በታች ያሉት ያልተመረጡት በተለይ ከ1984 ዓ.ም ወዲህ የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በየክልሎቹ በመሆኑ ወጥነት የማይስተዋልባቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ እንደ አፍ መፍቻና እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተብለው የሚዘጋጁ በመሆናቸው ነው (ጌታሁን 1993፡1)።

በተጠቀሰው ዘመን ሥራ ላይ የነበሩ የመማሪያ መፃህፍት የተመረጡት በአላማ ተኮር የንሞና ሥልት ሲሆን ተተኳሪዎቹ መፃህፍ ከመጀመሪያዎቹ 1968 እትም ጀምሮ የተሻሻሉት እና እየተለወጡ የመጡት ናቸው። (ዝርዝሩን ገጽ 5 ይመለከታል)

3.4. የጥናቱ ዘመን አመራረጥ

የሰዋስው ትምህርት አሰጣጥ በርካታ ዘመናትን ያስመዘገበ ክስተት ነው። የማስተማሪያ ዘዴውም ከጥንቱ የሰዋስው ወ ትርጉም ዘዴ እስከ ዘመናዊው ተግባቦታዊ ዘዴ ድረስ

በየጊዜው እየተሻሻለና እየተለወጠ የመጣ ነው። አቀራረቡም እንዲሁ ከመዋቅራዊ እስከ መስተጋብራዊ ድረስ እያደገ መምጣቱን የመስኩ ባለሙያዎች ያብራራሉ። ይህንንም ተከትሎ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን ተከትለው ሲቀርቡ ታይተዋል።

ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት ትኩረት ወደ ሆነው ዋናው ጉዳይ ስንመጣ ጥናቱ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ያለውን ዘመን ሲመርጥ መነሻውን ዘመን 1968 ዓ.ም ያደረገበት ምክንያት፡-

የመጀመሪያው በትምህርት ሚኒስቴር ስር በሥርዓተ ትምህርትና ሱፐርቪዥን ዋና ክፍል ሥር "የአማርኛ ቋንቋ ቡድን" የሚል ተቋቁሞ ራሱን የቻለ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርትና መርሃ ትምህርት መዘጋጀት የጀመረበት ወቅት መሆኑ ነው። ሁለተኛው ከ1960ዎቹ በፊት ከነበረው "የማስተማሪያ መፃህፍት፣ ተጨማሪ መፃህፍት፣ የመርጃ መፃህፍትና የግል ንባብ መፃህፍት" በሚል በግል ደራሲያን ለገበያ ከሚዘጋጁት መፃህፍት መካከል መርጦ ለማስተማሪያነት ከሚመደብበት አሰራር ይልቅ ወጥ ሆነው ራሳቸውን ወደ ቻሉና ለየክፍል ደረጃው ወደተዘጋጁ መፃህፍት ሽግግር የተደረገበት ዘመን በመሆኑና ሦስተኛው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ለውስን የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኘው ከ1968 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በመሆኑ ነው ደምሴ(1999)።

3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሥርዓት ባለው መንገድ ከመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ተለይተው እንዲወጡና በስነ-ድምጽ፣ስነ-ምዕላድ፣ስነ-አገባብና ስነ-ፍች ንዑስ ክፍል በየፈርጃቸው ተለይተው እንዲመደቡ ከተደረገ በኋላ መጻህፍቱ በተዘጋጁበት ዓመተ-ምህረት ቅደም ተከተል በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የማቅረቢያ መርሆዎች አንፃር እንዴት እንደቀረቡና በጊዜ ሂደትም ያሳዩት ለውጥና መሻሻል መኖር አለመኖሩ እየተመረመረ ትንተናው ተካሂዷል።

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት እንደየህትመት ዘመናቸው ቅደምተከተል ከመጀመሪያው የ1968ቱ እትም ጀምሮ፣ በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት የሥነ ትምህርታዊ መርሆዎች ወይም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ከሚቀርቡባቸው ስልቶች አንፃር ይተነተናሉ። ትንተናው የሚካሄደውም ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩና ባሉ የ9ኛና 10ኛ ክፍል በድምሩ አሥራሁለት የተለያዩ መፃህፍት ውስጥ በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ይሆናል።

ከእነዚህ መፃህፍት የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን ሂደት የተለያዩ አካሄዶችን መምረጥና መጠቀም የሚቻል ሲሆን ይህ ጥናት የተከተለው የትንተና አካሄድ ግን አንድን የማቅረቢያ መርህ በመምዘዝ፣ እያንዳንዱን ተተኳሪ የመማሪያ መፅሐፍ ከዚያ መርህ አንፃር ምን እንደሚመስል፤ ወይም በእያንዳንዱ ተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቃሹ የማቅረቢያ መሥፈርት እንዴት እንደተተገበረ በመመርመር ትንተናውን የማካሄድ ስልትን ነው።

አጥኚው ይኽኛውን የአካሄድ ስልት የመረጠበት ምክንያት፣ እያንዳንዱን ዝርዝር የማቅረቢያ መስፈርት በመዉሰድ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ እንዴት እየተተገበረ እንደሆነ ለማሣየት ምቹ ሁኔታ ይፈጥርልኛል ብሎ በማሰቡና የተሻለ አማራጭ ነዉ ብሎ በማመኑ ነዉ።

በተጨማሪም ምዕራፉ በተተኳሪዎቹ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የትኞቹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከመቼ ጊዜ ጀምረው እንደቀረቡም ቅኝት ይደረግበታል።

4.1 ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ሰዋስውን በተመለከተ ያላቸው አቋም

በሀገራችን የትምህርት ታሪክ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለውስን የክፍል ደረጃ ማለትም ለ(9ኛ፣ 10ኛ ወዘተ) ተብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ኃላፊነት በተሠጠው አካል በዘመናዊ መልኩ ተዘጋጅቶ የቀረበው በ1968 ዓ.ም መሆኑን ቀደም ብለን ጠቁመናል። ይህ ጥናት የሚያተኩረውም ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው እየተሻሻሉና እየተለወጡ በመጡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ላይ ነው።

ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የነበሩት የተተኳሪዎቹ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት "የመማሪያ መጻህፍቱ አቋም" በሚለው የመግቢያ ክፍላቸዉ ውስጥ ሰዋስው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሊቀርብ ስለሚገባበት መንገድ 21 ገጽ ዝርዝር ማብራሪያ ያቀረቡ ሲሆኑ፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በተመለከተ ኃላፊነት የተሰጠዉ " የሥርዓተ ትምህርትና ሱፐር ቪዥን ቡድን መምሪያ ዳይሬክሲዮን " አቋም በጥቅሉ ሲታይ፡-

1ኛ ሰዋስው ለብቻው ተለይቶ እንደ አንድ ክፍለ ትምህርት መሠጠትም ሆነ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ መቅረብ የሌለበት መሆኑን፣

2ኛ. ከቋንቋው የክሂል ዘርፎች ጋር ተጣምሮ በአንድ ላይ መቅረብ የሚገባው መሆኑን፣

3ኛ የተማሪዎች ሥህተት መታረም የሚገባው በሰዋስው ትንተና ሳይሆን በልዩ ልዩ አገባብ መሆኑና

4ኛ የምዘና ሥልቱም ሥርዓቱን በቃል አሥጠንቶ በፈተና ላይ ከማቅረብ ይልቅ ተማሪው በእውናዊ ተግባቦት ወቅት ተግባር ላይ ያውለው እንደሆነ በመመልከት መሆኑን የሚጠቁም ነበር።

ቡድኑ ለዚህ ድምዳሜ መነሻ የሆነዉንም ምክንያት "... ሰዋስው ከቋንቋው የወጣ ስርዓት በመሆኑ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሊቀርብም ሆነ በክፍል በትምህርትነት ሊሰጥ ለብቻው መቅረብ አልነበረበትም። ባለፈው ስርዓተ ትምህርት ግን ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ይሰጥ ነበር" በማለት ከ1968 ዓ.ም በፊት የነበረው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተገቢ አለመሆኑን አስረድቷል።

ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ሰዋስውን በተመለከተ ያላቸውን አቋም በተመለከተ ደግሞ በመግቢያው ክፍላቸው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የተማሪዎችን ክህሎት ከማዳበር በተጨማሪ የስነ ልሳን እውቀታቸውንም ማበልጸግ እንደሚገባ ይጠቁማሉ። በመሆኑም በመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ወቅትም የሰዋስው ትምህርት ከቋንቋው የክሂል እና የእውቀት ዘርፎች ጋር ተጣምሮ መሰጠት እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ሲሆኑ አቀራረባቸውም ይህንኑ መርህ የተከተለ ይመስላል።

4.2. ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች

ይህ ክፍል ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ እየተሻሻሉ እና እየተለወጡ በመጡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሰዋስው ትምህርት ረገድ የታየው ለውጥ የተቃኘበት ነው። በየጊዜው በተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የትኞቹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በየትኛው ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከመቼ ጀምሮ እንደተካተቱ በመቃኘት ሂደት ሥነ ድምጽን፣ ሥነ ምዕላድን፣ ሥነ አገባብን (ሐረግና አረፍተ ነገርን)ና ሥነ ፍቺን እንደ አብይ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ዘርፍ በመውሰድ የተደረገው ዳሰሳ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1 ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሠዋስው ትምህርት ረገድ በጊዜ ሂደት የቀረቡ ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ዓ.ም					
		1968	1972/3	1984	1991/2	1997	2004
1.	ሥነ ድምጽ				√		
	1. ጠብቀውና ላልተው የሚነበቡ ድምጾችን መለየት			√	√	√	√
	2. ጠብቆ የሚነበበውን ሆሄ መለየት			√	√		
	3. የድምጽ መርዘምና ማጠር						√
2.	ሥነ ምዕላድ	√	√		√		
	4. የጥምር ቃላት አመሠራረት			√	√		√
	5. ከግስ ስም መመስረት			√	√		√
	6. ከሥም ቅጽል መመስረት			√	√		√
	7. ከግስ ቅጽል መመስረት			√	√		√
	8. የውልድ ግሶች አመሠራረት		√	√	√		√
	9. ራሳቸውን በመድገም የሚመሠረቱ ቃላት			√			
	10. የሥም ገላጮችን መለየት		√	√	√	√	
	11. የግስ ገላጮች			√	√	√	
	12. ቃላትን በምዕላዶች መከፋፈል			√		√	√
	13. የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎች			√	√	√	√
	14. የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን መለየት			√	√		
	15. ስሞችን ማብዛት			√	√		√
	16. በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ			√	√		√
	17. አንስትና ተባዕቱ ያታ				√		

	18. የባለቤትና ተሣቢ አፀፋን መለየት				√		
	19. ክግስ አርዕስት መመስረት				√		
	20. ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን በማገናኘት ቃል መመስረት				√		
	21. ክግስ ቦዝ አንቀጽ መመስረት				√		
	22. የስሞችንና ቅጽሎችን ግሣዊ ቅርጽ መፈለግ				√		
	23. በቃላት ላይ የአርባታና ምስረታ ምዕላዶችን መቀጠል				√		
	24. በቃልና በምዕላድ መካከል ያለ አንድነትና ልዩነት				√		√
	25. ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ			√	√	√	√
3.	ሥነ -አገባብ						
	3.1. ሥነ ሐረግ						
	26. በተሠጡ ቃላት ሐረግ መመስረት	√	√	√	√	√	√
	27. ስማዊና ግሣዊ ሀረጋትን መለየት			√		√	
	28. ሐረጋትን በአይነታቸው መመደብ				√		√
	29. ቅጽላዊ ሐረግ					√	√
	30. መስተዋድዳዊ ሐረግ					√	√
	31. ውስብስብ ሐረጎችን ወደ ተራ ዐ.ነገር መሸንሸን					√	
	32. የሐረግ አይነትና ምንነት						√
	33. የስማዊ ሐረግ አመሠራረት				√		√
	34. የቅጽላዊ ሐረግ አመሠራረት						√
	35. ተውሳክ ግሣዊ ሐረግ						√
	3.2. አረፍተ ነገር						
	36. በተሠጡ ቃላትና ሐረጋት አረፍተ ነገር መመስረት	√	√	√	√	√	√
	37. አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዐ.ነገሮችን ማያያዝ	√	√				√
	38. በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠጡ ቦዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃላት መመላት	√	√				√
	39. ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን አረፍተ ነገሮች አስተካክሎ መፃፍ			√	√	√	√
	40. ተራ አረፍተ ነገሮችን ወደ ውስብስብ መቀየር			√	√	√	√
	41. የአንድን ቃል ቅርጽ በመለወጥ ባለቤትና ተሣቢ አድርጎ አረፍተ ነገር መስራት			√	√	√	√
	42. የቃላት ድግግሞሽን በማስቀረት አረፍተ ነገሮችን እንደገና መፃፍ			√			
	43. በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላት በሌሎች ቃላት መተካት		√		√		
	44. አረፍተ ነገሮችን አስተካክሎ እንደገና መፃፍ		√		√		
	45. በጅምር የቀሩ አረፍተ ነገሮችን መጨረስ				√	√	
	46. የአረፍተ ነገሮችን ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ መለየት				√	√	
	47. ተዘበራርቀው የተቀመጡ አረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተል ማስያዝ					√	
	48. ውስብስብ ሐረጎችን ወደ ተራ አረፍተ ነገሮች መሸንሸን				√	√	
	49. የአረፍተ ነገር ክፍሎች						√
	50. በአረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ቃላትን ሙያ መግለጽ						√
	51. የአረፍተ ነገርን ባለቤትና ተሣቢ መለየት				√		
	52. የአረፍተ ነገርን ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ማጣጣም				√		
	53. አንድን የአረፍተ ነገር ስልት ወደ ሌላ መለወጥ				√		√
	54. መስተዋድዶችን በመጠቀም ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት				√		
4.	ሥነ ፍቺ						
	4.1. ቃላት						
	55. የቃላት አውዳዊ ፍቺ	√	√	√	√	√	√
	56. የቃላት ቀጥተኛ (መዝገብ ቃላዊ) ፍቺ	√	√	√	√	√	√
	57. የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ	√	√	√	√		√
	58. የቃላት ተቃራኒ ፍቺ	√		√	√	√	√
	59. የቅጥያዎች ፍቺ			√			
	60. የቃላት እማሬያዊና ፍክሬያዊ ፍቺ					√	√
	4.2. ሐረጋት						
	61. የሐረጋት ፍቺ	√	√	√	√		
	62. የሐረጋት አውዳዊ ፍቺ		√	√	√	√	√
	63. የሐረጋት ተቃራኒ ፍቺ						√
	4.3. ዐ.ነገራት						
	64. የአረፍተ ነገር አገባባዊ ፍቺ		√				

4.2.1. በ1968 ዓ.ም. በታተሙት መፃህፍት ውስጥ

በዚህ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡት የተተኳሪዎቹ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት ሥነ ድምጽን በተመለከተ ምንም አይነት ይዘት አልያዙም።

ስነ ምዕላድን በተመለከተ ግን በ9ኛ ክፍል (ገጽ 101) ላይ "የጥምር ቃላት አመሠራረት"ና በ10ኛ ክፍል (ገጽ 133) ላይ ደግሞ "የቃላት ምስረታ" የሚል በድምሩ ሁለት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ይገኛሉ።

በሥነ ሀረግ ትምህርት ይዘት ረገድም ይህነው የሚባል ይዘት ቀርቦ አይታይም። በወቅቱ ቀርቦ የነበረው የትምህርት ይዘት "በተሠጡ ሀረጋት አረፍተ ነገር መመስረት" የሚል ነው። በርግጥ ይህ ይዘት በዐ.ነገር ምስረታ ክፍል የሚጠቃለል ቢሆንም ከሀረግ ጋር የተያያዘ ዝምድና ያለው ይዘት አለ ከተባለ የምናገኘው ይህንን ብቻ ነው።

ወደ አረፍተ ነገር ስንመጣ በአመዛኙ ከምስረታ ጋር የተያያዙ በርካታ፣ግን አንድ አይነት አቀራረብ ያላቸው ይዘቶች እናገኛለን።

በዚህ ክፍል አረፍተ ነገርን በተመለከተ ቀርበው የምናገኛቸው ይዘቶች [በተሠጡ ቃላትና ሀረጋት አረፍተ ነገር መመስረት፣ አጣማሪ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ማያያዝ፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ ባዶ የተተው ቦታዎችን በተስማሚ ቃላትና ሀረጋት መሙላት፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት በሌላ ቃል ወይም ሀረግ መተካት እና አንድን አረፍተ ነገር በሌላ መልኩ እንደገና ማዋቀርንና መፃፍን] የሚመለከቱ ናቸው።

በመጨረሻም የቃላት አውዳዊ፣ ቀጥተኛ፣ ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺዎች፣ ሥነ-ፍቺን በሚመለከት የቀረቡት ይዘቶች መሆናቸውን በተደረገው የሠነድፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

በዚህ ወቅት የተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ከፍተኛ ትኩረት የሠጡት ለሥነ ፍቺና ለሥነ አገባብ በተለይም ለዓረፍተ ነገር ምስረታ ሲሆን ለሥነ ሀረግና ለሥነ ምዕላድ የሠጡት ትኩረት እጅግ አነስተኛ ነው።ሥነ ድምጽን በተመለከተ ምንም ያሉት ነገር የሌለ ሲሆን ሥነ ምዕላድን፣ሀረግንና አረፍተ ነገርን በተመለከተ ቅርጽ ተኮር የሆነ አንድም ይዘት አልቀረበም።

መማሪያ መፃህፍቱ በመግቢያቸው ክፍል እንደገለጹት ተግባቦታዊ አቀራረብን ለመተግበር ያሰቡ ቢሆንም የቅርፃዊ ሰዋስውን ወይም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት የዘነጉ ይመስላሉ። በክለሳ

ድርሳኑ ክፍል ለመግለጽ እንደሞከርነው ደግሞ ተማሪዎቹ ሊኖራቸው የሚገባው የክሂል እውቀት ወይም የተግባቦት ችሎታ ብቻ ሳይሆን የሥርዓትም እውቀት ጭምር መሆን ይገባዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከቋንቋው የክሂልና ሌሎች የእውቀት ዘርፎች ጋር አጣምሮ የማቅረብ ችግር ታይቶባቸዋል። በአጠቃላይ ቅርጻዊ ሰዋስው በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ተገቢ ቦታና ሽፋን አግኝቶ አልቀረበም ነበር። ይህም የሆነዉ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ተቀባይነት እያጣ የመጣዉን " የሰዋስዉ ትምህርት በቋንቋዉ ቅርጽና ህግጋት ላይ ማተኮር አለበት" የሚለዉን አመለካከት በመተካት ተቀባይነት እያገኘ በመጣዉ " ዘመናዊ የሰዋስዉ ትምህርት እሳቤ ከቋንቋ ቅርጽና ህግጋት ይልቅ ተግባቦትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት" የሚለዉን አመለካከት በማራመዳቸዉ ምክንያት ይሆናል።

4.2.2 በ1972/3 ዓ.ም. ተሻሽለው በታተሙት መፃህፍት ውስጥ

በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ በ1968 ዓ.ም ከቀረቡት ጋር ሲነፃፀሩ ምን? አዲስና የተለየ ይዘት ይዘው እንደቀረቡ ለማወቅ በተደገው ዳሰሳ፤ ተሻሽለው የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት እንደ 1968ቶቹ ሥነ ድምጽን በተመለከተ ምንም ያሉት ነገር የለም። በመሆኑም በዚህ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ረገድ የታየ አዲስ ነገር የለም።

ሥነ ምዕላድን በተመለከተ "ከግስ፣ ውልድ ስም፣ ግስና ቅጽል መመስረት" 9ኛ (ገጽ 39) እና ስለ "ስም ገላጭ" (ገጽ 45) በድምሩ ሁለት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካትተው ይገኛሉ።

ሥነ አገባብን (ሀረግንና አረፍተ ነገርን) በተመለከተ በ1968 ከቀረቡት የተለየ ነገር ቀርቦ አይገኝም።

ሥነ ፍቺን በተመለከተ ግን ባለፈው ቀርበው ከነበሩት በተጨማሪ "የአረፍተ ነገር አገባባዊ ፍቺ" የሚል 9ኛ (ገጽ 45) እና 10ኛ (ገጽ 73) ላይ እናገኛለን።

በአጠቃላይ በ1972/3 ዓ.ም ተሻሽለው የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት በ1968 ዓ.ም ከቀረቡት ጋር ሲነፃፀሩ በሰዋስው ትምህርት ረገድ የታዩ ጉልህ ለውጥና መሻሻል የለም። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሥነ-ምዕላድን በተመለከተ ሁለት እና ሥነ ፍቺን በተመለከተ አንድ ይዘት

ከመቅረቡ ውጪ አዲስ ነገር ያልታየባቸው መሆናቸውን በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ለመግለጽ እንሞክርነው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎቹ ሊኖራቸው ከሚገባው የቋንቋ ክህሎት ጎን ለጎን የቋንቋውንም ሥርዓት እንዲገነዘቡ ማድረግን ጭምር የሚያካትት ነው። ይህም ማለት ከቋንቋ ትምህርት የተሟላ እውቀት ለማግኘት ከቋንቋው የክሂልና የሥነ ጽሁፍ ዘርፎች በተጨማሪ የሰዋስውም ትምህርት አብሮ ሊሰጥ ይገባዋል። መማሪያ መፃህፍትም ሲዘጋጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችንና ተግባቦታዊ ክንውኖችን አዋህደው ማቅረብ ይገባቸዋል።

ይሁን እንጂ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1968 ዓ.ም የታተሙትና በኋላም በ1972/3 ዓ.ም ተሻሽለው እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ተደጋግመው በመታተም ለአሥራ ሥድስት አመታት ያህል አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ለቋንቋው ሰዋስዋዊ ሥርዓት ተገቢ ቦታና በቂ ትኩረት ባለመስጠታቸው ዘመኑን ሰዋስው በተተኳሪዎቹ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እንዳይካተት እገዳ የተደረገበት እና ትምህርቱም ከመማሪያ ክፍል የራቀበት የገዘንጋታ ዘመን ልንለው እንችላለን።

4.2.3 በ1984 ዓ.ም በታተሙት መፃሕፍት ውስጥ

በዚህ ወቅት እንደ አዲስ ተዘጋጅተው እስከ 1990/91 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት በሰዋስው ትምህርት ይዘት ረገድ በፊት ከነበሩት መፃህፍት ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል የታየባቸው ሆነው ተገኝተዋል። ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ጥቅም ላይ ውለው የነበሩት መፃህፍት ቅርፃዊ ሰዋስውን በተመለከተ ያሉት ነገር እንደሌለ አሥቀድመን ገልፀን ነበር። ወቅቱንም ባየ (1987) እና ጌታሁን (1993) "የሰዋሰው ትምህርት ቸል የተባለበት ዘመን" በማለት ይገልጹታል። ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ የተቻለውም ወቅቱ ቅርፃዊ ሰዋስው ወይም የሰዋስው ትምህርት ትኩረት የተነፈገበት ዘመን መሆኑን ነው። ይህም የሆነበት ደግሞ የወቅቱ መፃህፍት አዘጋጅ ቡድን የሰዋስውን ትምህርት በተመለከተ ያራምደው በነበረው አቋም ምክንያት እንደሆነ የመማሪያ መፃህፍቱን አቋም በዳሰሰንበት ክፍል አንስተነዋል።

የሰዋስው ትምህርት በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ መቅረብም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ ክፍል ውስጥ መሠጠት ችላ የተባለበት ያ የዝንጋታ ዘመን አብቅቶ የ1984ቱ መማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ ግን የሠዋስው ትምህርት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ተገቢውን ቦታና ሽፋን ማግኘት ጀመረ። ይህንን እንድንል ያስቻለንም በዚህ ወቅት በተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ተካትተው ሥለሚገኙ ነው። ዝርዝሩን ቀጥለን እንመለከታለን።

በ1968 ዓ.ም ሆነ 1972/3 ዓ.ም በተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሥነ ድምፅን በተመለከተ የቀረበ ይዘት የሌለ መሆኑን አሥቀድመን ገልፀን ነበር። በ1984ቱ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ይህንን የትምህርት ይዘት በተመለከተ ጠብቀውና ላልተው ስለሚነበቡ (ስለሚነገሩ) ድምጾች የቀረበ ይዘት (ገጽ 5፣25 እና 73)ላይ ቀርቦ እናገኛለን። በመሆኑም ሥነ ድምጽን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ ለተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በይዘትነት ተካትቶ መቅረብ የጀመረው በዚህ ወቅት ነበር ማለት ነው።

በሌላ በኩል ሥነ-ምዕላድን በተመለከተም በዚህ ወቅት በርካታ ይዘቶች መቅረባቸውን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። በ1968 እና በ1972/3 ዓ.ም በተዘጋጁት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ይህንን ሰዋስዋዊ የትምህርት ዘርፍ በተመለከተ ቀርቦ የነበረው "የጥምር ቃል አመሠራረት"፣ ከግስ፡-ስም፣ ግስና ቅጽል መመስረት" እና ስለ "ቅጽል ቃላት" ብቻ እንደነበረ አስቀድመን ገልፀን ነበር። በዚህ ወቅት እንደ አዲስ የተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ግን ቃላት ምሥረታን በሚመለከት አምስት፣ ነባና ጥገኛ እንዲሁም የእርባታና የምስረታ ምዕላድን በተመለከተ አራት፣ ገላጮችን በተመለከተ (የሥምና የግስ) ሁለት፣ የቃል ክፍልን በተመለከተ ሦስት በድምሩ አሥራ አራት ያህል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መቅረባቸውን ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም የወቅቱ መማሪያ መፃህፍት በሥነ ምዕላድ ረገድ ካለፉት ይልቅ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል አሳይተዋል።

ከሥነ ድምጽና ሥነ ምዕላድ በተጨማሪ ሥነ አገባብንም በተመለከተ ስለ ሀረግና አረፍተ ነገር የቀረቡ አዳዲስ ይዘቶች መታየት ጀምረዋል። ሥነ ሀረግን በተመለከተ በ1968 እና በ1972/3 ዓ.ም የተዘጋጁት መፃህፍት የ"ሀረግ ምሥረታን ማለትም ተማሪዎቹ በተሠጣቸው ቃላት ሀረግ እንዲመሠርቱ ከማድረግ ውጪ ስለ ሀረግ ያቀረቡት ተጨማሪ ነገር የሌለ መሆኑን

ገልፀን ነበር። በዚህ ወቅት ታትመው የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ግን ከሀረግ ምሥረታ በተጨማሪ ስለ "ሀረግ አይነት"፣ በተለይም "ሥማዊና ግሳዊ ሀረግ"ን በተመለከተ ያቀረቡት ይዘት መኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህም በመነሳት በዚህ ወቅት የተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ስነ ሐረግን በተመለከተ ከቀዳሚዎቹ መማሪያ መፃህፍት የተሻለ ይዘትና አቀራረብ ታይቶባቸዋል ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል አረፍተ ነገርንም በተመለከተ የወቅቱ መማሪያ መፃህፍት ከቀዳሚዎቹ አንፃር ሲታዩ፣ ቀድመው ከቀረቡት ይዘቶች በተጨማሪ "ሰዋስዋዊ ሥህተት ያለባቸውን ዐ.ነገሮች አስተካክሎ መፃፍ፣ ተራ አረፍተ ነገሮችን ወደ ውስብስብ መቀየር፣ የስምን ቅርጽና አገባብ በመቀየር የባለቤትነትና የተሣቢነት ሙያ እንዲኖረው አድርጎ አረፍተ ነገር መስራትና የቃላትን ድግግሞሽ በማስቀረት አረፍተ ነገሩን እንደገና መፃፍ" የሚሉ ይዘቶችን እና ይዘቶቹንም የማቅረቢያ ስልቶች ተካትተው ተገኝተውባቸዋል። በመሆኑም በዚህም ረገድ መፃህፍቱ መሠረታዊ ሊባል የሚችል ለውጥ ያደረጉ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል።

በመጨረሻ ደረጃ ሥነ ፍቺን በተመለከተ ግን እንደ ሌሎቹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ያን ያህል የጎላ ለውጥ ወይም ልዩነት አልታየም። ከዚህ በፊት በሁለት ዙር ታትመው የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት የቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተ ነገራትን ፍቺ የሚመለከቱ ይዘቶችን ያካተቱ ሲሆኑ ከዚህ ለየት ባለ መልኩ በዚህ ወቅት የቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ግን ከበፊቶቹ በተጨማሪ "የቅጥያዎች ትርጉም" የሚል ይዘት አካትቶ ቀርቧል።

በመሆኑም ወቅቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ ከ1968 በፊት እንደነበረው "ሰዋስው ከቋንቋ ትምህርቱ ሌሎች ይዘቶች ተነጥሎ እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ ወይም የጥናት መስክ ለብቻው በመቅረብና በመሠጠት ላይ ሳያተኩር፤ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ እንዳለውም ሰዋስውን በሰዋስውነቱ ማስተማር ወይም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ከቋንቋው የተለያዩ የክሂልና የእውቀት ዘርፎች ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ቸል እንደተባለበትም የዝንጋታ ዘመን" ሳይሆን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በተለያዩ የአቀራረብ ሥልቶች ከቋንቋው ልዩ ልዩ የእውቀትና የክሂል ዘርፎች ጋር በማቅረብ ረገድ አዲስ የአቀራረብ አቅጣጫ የታየበት የሽግግር ዘመን ነበር ማለት ይቻላል።

ለዚህ አባባላችን ምክንያቱ ደግሞ አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው በዚህ ወቅት ተዘጋጅተው የቀረቡት የመማሪያ መፃህፍት ሥነ ድምፅን በሚመለከት አዲስ የትምህርት ይዘት

የተካተተባቸው፣ በሥነ ምዕላድ ዘርፍም በርካታ ይዘቶች የቀረቡባቸው ሲሆኑ፤ በሥነ-አገባብ ዘርፍም ሐረግንና አረፍተ ነገርን የሚመለከቱ አዳዲስ ሰዋስዋዊ ቅርጾች በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች መታየት የጀመሩበትና በሥነ ፍቺም መስክ ከቃል፣ ሀረግና አረፍተ ነገር በተጨማሪ "የቅጥያዎች ፍቺ" የሚል አዲስ ይዘት የቀረቡባቸው በመሆናቸው ወቅቱ፣ ሰዋስው በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ አዲስ የአቀራረብ ሥልትን ተከትሎ የተከሠተበት እና ገንኖም የወጣበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላልና ነው።

4.2.4. በ1991/2 ዓ.ም በታተሙት መፃህፍት ውስጥ

በ1984 ዓ.ም ተዘጋጅተው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት እስከዚህ ጊዜ ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ በተጠቀሰው ጊዜ ለተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ቦታቸውን አስረክበዋል። በመሆኑም በዚህ ወቅት የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ የታየው ለውጥ እንደሚከተለው ይቀርባል።

ሥነ ድምጽን በተመለከተ አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው እስከ 1984 ዓ.ም በነበሩት መፃህፍት ውስጥ የቀረበ ነገር አልነበረም። በዚህ ወቅት በተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ ግን እንደ አዲስ መከሠቱን ገልፀን ነበር። በ1991/92 በታተሙት መፃህፍት ውስጥ ደግሞ ስፋቱና ጥልቀቱ ጨምሮ፤ ሥርጭቱም በርከት ብሎ ተገኝቷል።

ይህን ያልንበት ምክንያትም በ1984ቱ መፃህፍት ውስጥ ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ (ሲነገሩ) የፍቺ ልዩነት ስለሚያመጡ ቃላት የሚመለከቱ ይዘቶች ብቻ ተካትተው የቀረቡ ሲሆኑ በዚህ ወቅት ግን የጠበቀው ቃሉ ሳይሆን በቃሉ ውስጥ የሚገኘው ድምጽ መሆኑን በመጠቆም፣ ያንን የጠበቀ ድምጽ መለየትን የሚመለከቱ ይዘቶች በ9ኛ ክፍል (ገጽ 57)፣ የተገደፉ (የተደበቁ) ድምጾች መለየትን በ10ኛ ክፍል (ገጽ 136) እና በአንድ ቃል ውስጥ የሚገኙ "ፎኒም" ድምጾችን በሌላ በመተካት የትርጉም ልዩነት መፍጠር የሚችሉ ይዘቶች 9ኛ ክፍል ገጽ 18 ላይ ቀርበው እናገኛቸዋለንና ነው።

ሥነ ምዕላድን በተመለከተ በ1984 ዓ.ም የታተሙት መፃህፍት፣ በ1968 ከታተሙትና በኋላም በ1972/3 ተሻሽለው ከቀረቡት አንፃር ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል መታየቱን ገልፀን ነበር። በ1991/2 በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ደግሞ ከባለፈው የ(1984ቱ) መማሪያ

መፃህፍት ይልቅ የተስፋፉ ይዘቶችንና የአቀራረብ ስልቶችን እናገኛለን። በዚህ ወቅት ከታዩት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል፦

- ከግስ አርዕስትና ቦዝ አንቀጽ መመስረት (9ኛ ገጽ 42፣111)፣
- የስሞችና የቅጽሎችን ግሳዊ ቅርጽ መፈለግ (10ኛ ገጽ 128)፣
- እንስትና ተባዕት ፆታን መለየት (9ኛ ገጽ 54)፣
- የተሣቢንና የባለቤት አፀፋን መለየት (9ኛ ገጽ 5 እና 19፣10ኛ ገጽ 41)፣
- በአንድ ቃል ላይ የእርባታና የምስረታ ምዕላዶችን መቀጠል (10ኛ ገጽ 143)፣
- በ3ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አንስተ ፆታ፣ ኃላፊ ጊዜ አስደራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጾችን መመስረት (10ኛ ገጽ 154)

የሚሉት ተጠቃሾች ናቸዉ።

በሌላ በኩል ሥነ-ሀረግን በተመለከተም የተከሠተ ለውጥ መኖሩን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። በ1984 ዓ.ም በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ይህንን የትምህርት ይዘት በተመለከተ ሥማዊ እና ግሣዊ ሀረግን መለየትን በተመለከተ፣ 10ኛ ክፍል (ገጽ 52 እና 53) ላይ ከቀረበው ይዘት በሥተቀር ተጨማሪ ነገር እንደሌለ ቀደም ብለን ጠቁመን ነበር።

በዚህ ወቅት በቀረቡት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ወይም ከቀረቡት በተጨማሪ ስለ ሐረግ አመሠራረት 10ኛ (ገጽ 48)፣ ሀረጋትን መመደብ (ሁሉንም ሀረጎች ባካተተ መልኩ) 9ኛ (ገጽ 29)፣ ጥገኛ ሐረጋትን መለየት 10ኛ (ገጽ 128) እና አረፍተ ነገርን ወደ ስማዊ ሀረግ መለወጥ 10ኛ (ገጽ 21) የሚሉ ይዘቶች ቀርበው ይገኛሉ።

አረፍተ ነገርን በተመለከተ በ1984 ዓ.ም ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተጨማሪ በዚህ ወቅት ከተካተቱት መካከል፦

- ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ወደ ተራ አረፍተ ነገር መቀየር (10ኛ ገጽ 40)፣
- ሀተታዊ አረፍተ ነገርን ወደ ትዕዛዛዊና ጥያቄያዊ አረፍተ ነገር መለወጥ (10ኛ ገጽ 9 104፣ 105፣ 142 እ፣ 171) እና
- መስተዋድዶችን በመጠቀም ውስብስብ ዐ.ነገሮችን መመስረት (10ኛ ገጽ 24) የሚጠቀሱ ናቸው።

በዚህ ወቅት በታተሙት መፃህፍት ውስጥ የተለየ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ያልቀረበበት ክፍል ሥነ ፍቺ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በተጨማሪ በዚህ ወቅት በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የታየው አዲስ ነገር የቋንቋን ባህሪ በተመለከተ የቀረበው ሠፊ ሐተታ ነው። በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከ(ገጽ 11-13) ድረስ የቀረበው ይኸው ማብራሪያ ስለ ቋንቋ ምንነትና ባህሪያት በዝርዝር የሚያስረዳ ሲሆን ይህም ጽንሰ ሃሳብ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ባሉት መፃህፍት ውስጥ በዚህ መልኩ ተገልጾ አናገኘውም።

ሌላው በዚህ ወቅት የታየው አዲስ ክስተት "ሥነ-ልሣን " የሚለው ስያሜ ከዚያ በፊት "ሰዋስው" በመባል ይታወቁ ለነበሩት ሥነ ትምህርታዊ ይዘቶች መጠሪያነት መዋሉ ነው።

በአጠቃላይ በ1991/92 የታተሙት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት፣ በ1984 ዓ.ም ከታተሙት መማሪያ መፃህፍት አንፃር ሲታዩ ተጀምረው ወይም ቀርበው የነበሩት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የበለጠ እየተጠናከሩ፣ ሥፋትና ጥልቀታቸው እያደገና ከቋንቋው የክሂል እና የእውቀት ዘርፎች ጋር እየተጣመሩ የመቅረብ ሂደታቸው ይበልጥ ተጠናክሮና ተስፋፍቶ የቀጠለ መሆኑን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ውጤት ማረጋገጥ ችለናል።

4.2.5. በ1997 ዓ.ም በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ

አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው በ1991/2 እንደ አዲስ ተዘጋጅተው እስከ 1996 ዓ.ም ሲያገለግሉ የቆዩት መማሪያ መፃህፍት በ1997 ዓ.ም ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። ቀጥለን የምናየው በሰዋስው ትምህርት ረገድ የታየውን የይዘት ለውጥ ይሆናል።

በመሆኑም በዚህ ወቅት ማሻሻያ የተደረገባቸው መማሪያ መፃህፍት በ1991/2 ተጀምሮ የነበረውን የቋንቋ ባህሪያት ገለፃና ማብራሪያ አሥፋፍቶ በመቀጠል የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ 9ኛ (ገጽ 1)፣ የቋንቋዎች እኩልነት 10ኛ (ገጽ 1) አካትተው ይዘዋል።

ሥነ-ድምጽን በተመለከተ የተለየ ይዘት ያልታየ ሲሆን ሥነ ምዕላድን በተመለከተ ግን ፍጹም አዲስና የተለየ ነው ባይባልም በአቀራረብ ደረጃ ግን ልዩነት መታየቱን መገንዘብ ተችሏል። ለምሳሌ፡በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ወስጥ ከ(ገጽ9) ጀምሮ "የቃል ክፍሎች" በሚል ርዕስ የቀረበው ማብራሪያ ከዚያ በፊት በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያልታዩ ነው። ምክንያቱም በዚህ ርዕስ ስር መማሪያ መጽሐፉ በዘመናዊ የሰዋስው ምሁራን ድንጋጌ (ባየ 1987 እና ጌታሁን 1989) መሠረት የቃል ክፍሎች (አምሥት) መሆናቸውን በዝርዝር ከገለጸ

በኋላ በተለየ መልኩ ደግሞ ስምን በሚመለከት የቅርጽና የአገባብ ባህሪያቱን ወይም በአረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን ሰዋስዋዊ ሙያ (ባለቤትነት፣ ተሣቢነት፣ ዘርፍነት) በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን፤ ከቅርጽ አንፃርም /-አች/ የሚለውን የብዜት ምዕላድ የሚወስድ መሆኑን፣ ከአወቃቀር አንፃርም ጠቋሚና መጣኝ ምዕላዶች ቀድመውት እንደሚገቡና አይነትን የሚገልጽ ኦሳላማሽ እንደሚወስድ የሚያስረዳ መግለጫ አቅርቧል።

ጉዳዩን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን "ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የማቅረብ ሥልት" በሚለው ክፍል እንደገና እንመለስበታለን። በእርግጥ በዋናነት የታየው የአቀራረብ ስልት ለውጥ ነው። ይሁን እንጂ ይህ የአቀራረብ ስልት ለውጥ በውስጡ የይዘቱን ያልታዩ ገጽታዎች በማቀፉ ለይዘት ለውጥ መከሰት ምክንያት ሆኗል።

በሌላ በኩል በዚሁ መማሪያ መጽሐፍ (ገጽ 11) ላይ ሥለ ነፃና ጥገኛ ምዕላድ ምስስሎሽና ልዩነት የቀረበውም መግለጫና በማብራሪያው ውስጥ የተካተቱት ዝርዝር ጉዳዮች ከዚህ በፊት በቀረቡት መፃህፍት ውስጥ ያልታዩ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በግስ ላይ ሥለሚገኙ የባለቤትና ተሣቢ አፀፋዎች 9ኛ (ገጽ 12) እና የእርባታና ምስረታ ምዕላዶች ተግባር 10ኛ (ገጽ 30) በዚህ ወቅት ለየት ባለ የአቀራረብ ሥልት የተከሠቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ናቸው።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች እስከ ተጠቀሰው ዘመን (1997 ዓ.ም ድረስ) በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በቀጥታ አይገኙ እንጂ ፈጽመው ያልነበሩና አዲስ ናቸው ማለት ግን አይደለም። በዚህ ጊዜ የታየው አዲስ ነገር፣ ሥለ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ የቀረበው ሙያዊ ብያኔ፣ ሰዋስዋዊ ተግባር፣ አገባብና የአመዳደብ ሥልታቸው አዲስ መሆን ነው።

ሥነ ሐረግን በተመለከተ በዚህ ወቅት መሠረታዊ ሊባል የሚችል የአቀራረብ ልዩነት ተከስቷል። ይህንንም ያልንበት ምክንያት በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት መማሪያ መጻሕፍት ሐረግን በተመለከተ ካቀረቧቸው ዝርዝር ጉዳዮች መካከል በተለይ ሥለ ተውሳከ ግሣዊ ሀረግ፣ መስተዋድዳዊና ቅጽላዊ ሐረግ ምንነት፣ አመሠራረት፣ የመሪ አቀማመጥ፣ እና መሠል ተያያዥ ጉዳዮች ያቀረቧቸው የትምህርት ይዘቶች በከዚህ ቀደሞቹ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ቀርበው እናገኛቸውም።

በሥነ ምዕላድ ክፍሉ ባቀረብነው ማጠቃለያ ውስጥ እንደገለጽነው ሁሉ በሥነ ሀረግ ክፍሉም ቀርበዋል የተባሉት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ፈጽመው አዲስ ናቸው ማለታችን አይደለም። ይህም ማለት ከዚህ በፊት በነበሩት መፃህፍት ውስጥም ተካትተው ቀርበው ነበር። ይሁን እንጂ የይዘቶቹ አቀራረብ ሥፋትና ጥልቀት እየጨመረ በመጣ ቁጥር ሥለ ይዘቶቹ የሚነሱት አዳዲስና የተለያዩ ገጽታዎች በአዲስ ይዘትነት እንድናነሳቸው ስላስገደዱን ነው። ለዚህም ነው ለውጡ አቀራረቡን ተከትሎ የመጣ ለውጥ ነው ያልነው። የበለጠ ደግሞ ጉዳዩን በቦታው እናየዋለን።

በዓረፍተ ነገር ደረጃ ጎልቶ የወጣ የይዘትም ሆነ የአቀራረብ ልዩነት አልታየም። ሥነ ፍቺን በተመለከተ ግን ስለ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ የፍቺ ሥርዓት የቀረበ ይዘት ይገኛል። የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ የፍቺ ገጽታን በተመለከተ የቀረቡት መግለጫዎች በተለይ የእማሬያዊ ፍቺ አዲስ ባይሆንም ሥያሜው አገልግሎት ላይ የዋለው በዚህ ወቅት በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ መሆኑን ከሠነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል።

4.2.6. በ2004 ዓ.ም በታተሙት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ

በ2004 ዓ.ም በአዲስ መልክ የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት እስከዚህ ጊዜ ድረስ ለክፍል ደረጃው በማስተማሪያነት ከተዘጋጁት መፃህፍት በብዙ መልኩ የተለዩ ናቸው።ይሁን እንጂ ይዘን የተነሳነውን ዓላማ ብቻ መሠረት በማድረግ በሥነ ድምጽ፣ ሥነ ምዕላድ፣ በሀረግና በአረፍተ ነገር እንዲሁም በሥነ ፍቺ ረገድ እንደ አዲስ የቀረቡትን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ብቻ ለመቃኘት እንሞክራለን።

በዚህ ወቅት በሥነ ድምጽ የይዘት ትምህርትነት ተካትቶ የቀረበው የተለየ ነገር "የድምጽ መርዘምና ማጠር" ነው። ይህ የትምህርት ይዘት በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ በ(ገጽ 28፣ 84 እና 85) ላይ ለሦስት ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ቀርቧል። እስከዚህ ጊዜ ድረስ በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሥለድምጽ መርዘምና ማጠር የተባለ ነገር አልነበረም። የመልመጃው ትዕዛዝ የሚከተለውን ይመስላል። "የሚከተሉት ቃላዊ ግጥሞች በያዟቸው ቃላት ውስጥ ባሉት ድምጾች መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር እንዲሁም በአንድ ላይ መነበብ ወይም ተነጣጥለው መነበብ የተነሳ የሚመጣውን የፍቺ ልዩነት በተሠጣችሁ ምሣሌ መሠረት አሳዩ።" የሚል ነው።

ትዕዛዙ በግጥሙ ውስጥ ያሉትን ቃላት ፍቺ ለማወቅ የቃሉን የአነባበብ ሥልት ማለትም የድምጾቹን መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር እንዲሁም በአንድ ላይ መነበብ ወይም ተነጣጥለው መነበብ ማወቅ የግድ የሚል መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ከዚህ የምንረዳው ደግሞ የድምጽ መርዘምና ማጠር እንደ መጥበቅና መላላት ሁሉ ሥነ ትርጉማዊ ባህሪ ያለው ወይም የፍቺ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ነው። በመማሪያ መጽሐፉ (ገጽ 84) ላይም እንዲሁ "በቃላት ውስጥ የሚረዝሙና የሚያጥሩ ድምጾች ስንል... ጠብቆ ተነበበ ማለት ተረግጦ ተነበበ ማለት ነው። ተረግጦ ተነበበ ማለት ደግሞ ረዝሞ ተነበበ ማለት ነው።" በማለት ተናባቢ ድምጾች የስንኝ ቤት ሆነው ሲቀርቡና በቃል መጀመሪያ ላይ ሲገቡ ረዝመው እንደሚነበቡ ወይም ቀለም እንደሚሆኑ የሚያስረዳ ማብራሪያ ቀርቧል።

የቀረበውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት በተመለከተ ከትክክለኛነት፣ ከግልጽነትና ተገቢነት አንፃር ሊነሱና ሊመለሡ የሚገባቸዉን በርካታ ጉዳዮች ለባለሙያዎች እንተዋቸዋለን። ምክንያቱም የድምጽ ርዝመት ከአናባቢዎች ክትትሎሽ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ሲሆን ይህንን ጉዳይ በተመለከተ እስከ አሁን ድረስ ተቀባይነት ያለው አመለካከት በአማርኛ ቋንቋ የአናባቢዎች ክትትል የማይፈቀድ መሆኑና ተከታትለው ቢገኙ እንኳን ክትትሎሹን በማስቀረት የቋንቋውን ህግ ማስከበር ይቻል ዘንድ ከፊል አናባቢዎችን በመካከላቸው ማስገባት የሚያስፈልግ መሆኑን ነው።

የሆነው ሆኖ ሥነ ድምጽን በተመለከተ በዚህ ወቅት የቀረበው አዲስ የትምህርት ይዘት መሆኑን ብቻ በመጠቆም ወደ ቀጣዩ ጉዳያችን እናልፋለን።

በሥነ ምዕላድ የትምህርት ይዘት ረገድ በዚህ ወቅት ቀርቧል ሊባል የሚችለው የተለየ ነገር በቃልና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት 9ኛ (ገጽ 109) የሚመለከተው ነው። ከዚህ በፊት በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ምዕላድን በተመለከተ የእርባታና የምስረታ ምዕላድ፣ ጥገኛ ምዕላድና ሥርወቃል፣ የሚሉ ይዘቶች ቀርበው ነበር። በዚህ ወቅት ደግሞ እነዚህ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ጠለቅና ሠፋ ያለ የይዘት አቀራረብ ስልትን ተከትለው እስካሁን ያልተዳሰሰውን የተራ ቃልንና ነፃ ምዕላድን አንድነት እና የቃልንና የምዕላድን ምስስሎሽና ልዩነት የሚገልጹ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካትተው እናገኛቸዋለን።

በሥነ ሀረግ ዘርፍ ቀርቧል ሲባል የሚችለው የተለየ ነገር ሥለ ሀረጋት የአመሠራረት ድንጋጌ፣ የተዋቃሪ አካላቱ ዝምድና እና ከመሪ አሠላለፍ ሥርዓት አንፃር ቀኝ ብቻ ወይም ቀኝም ግራም መሪ የመሆንን ጉዳይ በተመለከተ የቀረበው ማብራሪያና ምሣሌ ነው።

አረፍተ ነገርን በተመለከተ እንዲሁ የአረፍተ ነገር ክፍሎች በሚል ከዚህ በፊት ስማዊ እና ግሣዊ ሀረግ ተብሎ የቀረበው የትምህርት ይዘት በእነዚህኞቹ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ባለቤት ተሣቢና ማሠሪያ አንቀጽ በማለት በሦስት ከፍለው አቅርበውታል 9ኛ (ገጽ 86)።

4.3. ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለጸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የማቅረቡ ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮር እና ጥምረታዊ የአቀራረብ መርህን ሊከተል እንደሚገባው አንስተን ነበር። ቀጥሎ የሚቀርበውም የአቀራረብ መርሆዎቹ በተጠቀሰው ጊዜ በቀረቡት መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያላቸው ገጽታም ሆነ በጊዜ ሂደት ያሳዩት ለውጥ እና መሻሻል ወይም አለመሻሻል ምን እንደሚመስል ነው።

4.3.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የነበረው ገጽታ

4.3.1.1. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1968 ዓ.ም

በምዕራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ ስልት ይቀርባሉ ሲባል፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሥለሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱ ዝርዝር መግለጫ ወይም ማብራሪያ ከቀረበና በምሳሌ የተደገፈ መለማመጃ ከተዘጋጀ በኋላ ይህን ተከትሎ የሚተገበር ጥያቄ ተሠናድቶ፣ ተማሪዎች ያንን እየሠሩ በሂደት ትክክለኛውን የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚያስችል አካሄድን የሚከተል መሆኑን ለመግለጽ ነው። በዚህም መሠረት በ1968ቱ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ይህ የአቀራረብ ስልት ምን ገጽታ እንዳለው ቀጥሎ ይቀርባል።

በዚህ ወቅት በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ብዛት ከነድግግሞሽ መጠናቸው ስላሳ አራት ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አካሄድ የሚታይባቸው ሁለት ያህሉ ብቻ መሆናቸውን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። ከእነዚህ ይዘቶች መካከል የመጀመሪያው ሥነ አገባብን በተመለከተ (ገጽ 69) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሥነ ምዕላድን በሚመለከት ነው (ገጽ 101)። እነዚህ ሁለት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልትን የተከተሉ ናቸው የተባለበት ምክንያት ስለሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ዝርዝር ማብራሪያ ካቀረቡ በኋላ ምሳሌ በማቅረብ ተማሪዎቹ ቀሪውን መልመጃ በምሳሌው መሠረት እየሰሩ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸውን በሂደት እንዲያዳብሩ የሚያስችላቸውን የአካሄድ ስልት የተከተሉ በመሆናቸው ናቸው።

በዚህ መሠረት በመማሪያ ክፍሉ (ገጽ 69) ላይ የቀረበው ማብራሪያ፡-

> አንዱን ሃሳብ ፣ አንዱን ድርጊት በትክክል ሊገልጽ የሚችል ቃል አንድ ብቻ ነው። በሚል ሲሆን ይህንንም አባባል በምሳሌ አስደግፎ አቅርቦታል።

ምሳሌ፡- *ገበሬው ወደ ገበያ የወሰደውን እህል እንደ ደላሎችና ትናንሽ ነጋዴዎች ሁሉ ቁጭ ብሎ በጣሳ እየሰፈረ _____ በኋላ ገንዘቡን ቋጥሮ ደስ ብሎት ወደ ቤቱ ገባ። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ከቸረቸረ፣ ከሸጠ...” ከሚሉት ሁለት አማራጭ ቃላት መካከል ሁኔታውን ሊገልጽልን የሚችለው ቃል “ቸረቸረ” መሆኑን* ያብራራል።

ምክንያቱንም ሲገልጽ “... በዐ.ነገሩ ውስጥ ትናንሽ ነጋዴዎች፣ ቁጭ ብሎ በጣሳ መስፈር፣ እንደ ደላሎች... የሚሉ ሀረጎች ችርቻሮን የሚጠቀሙ፣ የሚያመለክቱ መሆናቸውና በዚህም ላይ ሽጦ የሚለው ቃል ደግሞ ምንም እንኳን በባዶ ቦታው ሊገባ ቢችልም ያሻሻጡን ሁኔታ “ቸረቸረ” እንደሚለው ቃል በጉልህና በገሃድ የሚገልጽ ባለመሆኑ ነው”

ይላል። ከላይ የቀረበውን ማብራሪያ በማስከተል፡-

> “እንግዲህ ይህንን መመሪያና ምሳሌ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ ሊገባ የሚችለው ቃል አንድ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ከተሠጡት አማራጭ ቃላት ውስጥ አንዱን የሚሻለውንና ያንን ሁኔታ የበለጠ የሚገልፀውን ብቻ መርጠህ ካስገባህ በኃላ በተለይ ከሌሎች ቃላት ያንን ቃል ለምን እንደመረጥህ ምክንያትህን እየሠጠህ እያብራራህ ዓፍ።

የሚል ትዕዛዝ አቅርቧል።

ይህንንም ትዕዛዝ ተከትሎ የቀረበ መልመጃ ይገኛል። በመሆኑም ከላይ ከቀረበው ማስረጃ የምንረዳው አቀራረቡ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አካሄድን የተከተለ መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል መማሪያ መጽሐፉ በ(ገጽ 101) ላይም ለዚህ አቀራረብ ማስረጃ የሚሆን ሌላ ምሣሌ እናገኛለን። ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱ የጥምር ቃላት አመሠራረትን የሚመለከተ ሲሆን ዝርዝሩ የሚከተለውን ይመስላል።

> ... ህብረተ-ሰብ የሚለው ቃል በንዑስ ጭረት እንደተዓፈ ተመልከት። በእንዲህ አይነቱ መንገድ የሚዓኙ ቃል ከሁለት ቃላት የተመሠረተ አንድ ቃል በመሆኑ "ድርብ ቃል" ተብሎ ይጠራል። እንግዲህ "ህብረተ-ሰብ" የሚለው ቃል "ነብረት" እና "- ሰብ" ከሚሉት ሁለት የተለያዩ ቃላት የተገኘ መሆኑን በማስተዋል "- ሰብ" በሚለው ቃል ሊያልቁ የሚችሉ ቃላትን በሙሉ ዓፍና ምን ማለት እንደሆነ ትርጉማቸውን ግለጽ።

ከላይ ሥለ ድርብ ቃላት አመሠራረትና የትርጉም ሥልት የቀረበውን መግለጫ ተከትሎ ህብረተ-ሰብ በሚለው ምሳሌ የታጀበውና ስለጥምር ቃላት የቀረበው መልመጃ የአቀራረብ ሥልቱ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አካሄድን የተከተለ መሆኑን የሚጠቁም ነው።

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት 34 ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል በእንዲህ አይነት የአቀራረብ ሥልት የቀረቡት ሁለቱ ይዘቶች ብቻ መሆናቸው ስልቱ ለመተግበሩ ማሣያ ከመሆናቸው በዘለለ መማሪያ መጽሐፉ ይህንን የአቀራረብ ሥልት በተገቢው መጠን ተግብሮታል ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም በዚህ ወቅት የቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ በማቅረብ ረገድ ክፍተት ታይቶበታል ማለት ይቻላል።

በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ሥልትን ተከትሎ የቀረበው ከሰላሳ አንዱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች (ከነድግግሞሽ መጠናቸው) መካከል በመጽሐፍ (ገጽ 70) ላይ ሚገኘውና ሥለ ቃላት አገባብ የሚያትተው አንድ የትምህርት ብቻ ነው። ይህም የትምህርት ይዘት በተመሳሳይ ወቅት ታትሞ ሥራ ላይ ከዋለው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ (ገጽ 69) ላይ በቀጥታ የተገለበጠ በመሆኑ ዝርዝሩን በዚያው ክፍል አይተነዋል። አንድን የትምህርት ይዘት እንዳለ ማለትም ምንም አይነት የይዘት

ሥፋትና ጥልቀትም ሆነ የአቀራረብ ልዩነት ሳይኖረው ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ማቅረቡ የሥነ ትምህርታዊ ድንጋጌዎችን የጣሰ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም።

በመሆኑም በዚህ ወቅት የቀረበው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ሥልትን ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አቅርቧል ለማለት አያስደፍርም።

ምክንያቱም ከ31 ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱን ብቻ በዚህ ሥልት ያቀረበ በመሆኑና ያም ደግሞ በተመሳሳይ ወቅት ለ9ኛ ክፍል ከተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለምንም ለውጥና መሻሻል የተወሰደ በመሆኑ ነው።

በአጠቃላይ በ1968 ዓ.ም በታተሙት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ሥልት ከማቅረብ አንፃር ጉልህ ክፍተት ታይቶባቸዋል ማለት ይቻላል። ወደዚህ መደምደሚያ እንድንደርስ ምክንያት የሆነን አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው የ9ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ ካካተታቸው 34 ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል ሁለቱን ብቻ በዚህ ሥልት ሲያቀርብ፤ የ10ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ በበኩሉ ከያዛቸው 31 ይዘቶች መካከል አንዱን ብቻ በዚህ የአቀራረብ ስልት ያቀረበ በመሆኑ ነው።

4.3.1.2 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተሻሽለው የታተሙት የ9ኛም ሆነ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ከመጀመሪያዎቹ የሚለዩት በመጠናቸው ማነስ፣ በምንባቦቻቸው ርዕሶች፣ በገጽ ቁጥር መበላለጥና የድርሰት ትምህርትን በሚመለከት አንዳንድ ርዕስ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር ሰዋስውን በተመለከተ የተለየ ነገር የለባቸውም። ተሻሽሎ በቀረበው የ9ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ ሥልት የቀረበ ምንም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አልተገኘም። በ10ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ቢሆን በቀድሞው (9ኛ ክፍል ገጽ 69) እና (10ኛ ክፍል ገጽ 70) ላይ ከቀረበው በተጨማሪ ምንም የቀረበ ይዘት አልታየም። ይህ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ግን በ1972 የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም በ(ገጽ 37) ላይ እንዳለ ቀርቧል።

ከዚህ በመነሳት በ1972/3 ዓ.ም ተሻሽለው በቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ይህንን የአቀራረብ ሥልት ተከትሎ የቀረበ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አለ ለማለት

አያስደፍርም። በመሆኑም በ1972/3 ዓ.ም ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎ ላይ ውለው በነበሩት የ9ኛም ሆነ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ሥልት ከማደራጀት አንፃር መማሪያ መፃህፍቱ ድክመት የታየባቸው በመሆናቸው ሥልቱ በተገቢዉ ሁኔታ ተተግብሯል ለማለት አያስደፍርም።

4.3.1.3 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1984 ዓ.ም

በዚህ ወቅት እንደ አዲስ የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት በ1968 ዓ.ም ከተዘጋጁትም ሆነ በ1972/3 ተሻሽለው ከቀረቡት ጋር በንጽጽር ሲታዩ በሰዋስው ትምህርት ረገድ በርካታ አዳዲስ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አካትተው ይዘዋል። ይሁን እንጂ እነዚህን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ በሚያቀርቡበት ወቅት ይህንን የአቀራረብ ስልት አልተገበሩትም። ይህም ማለት ከቀረቡት በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱንም እንኳን በዚህ ስልት አላደራጁትም። በመሆኑም መጻህፍቱ ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅመው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር ከፍተኛ ክፍተት የታየባቸው መሆናቸውን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን በዚህ ወቅት እንደ አዲስ ታትመው የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ሥልቱን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከ1968ቱም ሆነ ከ1972/3ቱ ጋር ሲነፃፀሩ ምንም ያሳዩት ለውጥና መሻሻል የለም። እንዲያው አንድና ሁለት ተብለው በምሳሌነት ቀርቦ የነበረዉ ጅምርም መጥፋቱን ማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ በመነሳት በ1968 ም ሆነ በ1972/3 ዓ.ም በነበሩት መፃህፍት ውስጥ የነበረው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የማቅረብ ድክመት እየቀጠለ መምጣቱን በተደረገው ፍተሻ ማረጋጋጥ ተችሏል።

4.3.1.4. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም

በ1991 ዓ.ም የተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይህንን የአቀራረብ ስልት መሠረት አድርጎ ያቀረባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ ማረጋገጥ የተቻለው መማሪያ መጽሐፉ ይህንን ስልት ተከትሎ ያቀረበው አንድም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት የሌለ መሆኑን ነው።

ይህ አጠቃላይ ሁኔት የሚያመለክተን መማሪያ መጽሐፉ ከዚህ የአቀራረብ ሥልት አንፃር ከፍተኛ ሊባል የሚችል ክፍተት ያለበት መሆኑን ነው። ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ

ስልት አደራጅቶ የማቅረቡ ሂደት ድክመት ያሳየው በዚህ ወቅት በታተመው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ አለመሆኑን አስቀድመን ገልፀን ነበር። ምክንያቱም በ1973 ተሻሻሎ በቀረበውም ሆነ በ1984 እንደ አዲስ በቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ምንም አይነት ሰዋስዋዊ ይዘት በዚህ ሥልት ተደራጅቶ ስላልቀረበ ነው። በመሆኑም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ስልት አደራጅቶ በመማሪያ መፃህፉ ውስጥ የማቅረቡ ክፍተት ምንም አይነት መፍትሄ ሳይገኝለት ከ1968ቱ የመጀመሪያ እትም ጀምሮ እስከ 1991ዱ ድረስ የቀጠለ መሆኑን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

የ9ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ ከተዘጋጀ አንድ አመት ቆይታ በኋላ በ1992 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ሥልት አደራጅቶ በማቅረብ ረገድ ከ9ኛ ክፍሉ ያልተለየ ነው። ይህ የመማሪያ መጽሐፍ በ1991 ከታተመው የ9ኛ ክፍል መጽሐፍም ሆነ ከሱ በፊት ታትመው ቀርበው ከነበሩት የ10ኛ ክፍል መፃህፍት አንፃር በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አካትቶ ቢይዝም በአቀራረብ ረገድ ግን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልትን ተግባራዊ አላደረገም። በመሆኑም በዚህ ወቅት የቀረበውም የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በ1984 ዓ.ም ከቀረበው ተመሳሳይ መማሪያ መጽሐፍ አንፃር ሲታይ የተለየ ነገር አልተገኘበትም። ይህም የሚነግረን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ሥልት ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የማደራጀቱ ጉዳይ ለውጥና መሻሻል ያልታየበት መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1991/2 ዓ.ም ድረስ አራት ጊዜ ተደጋግመው በቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ስፋትና ጥልቀት እያገኙና ሥርጭታቸውም እየተሻሻለ ቢመጣም፣ በአቀራረብ ረገድ ግን መማሪያ መፃህፍቱ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልትን ያልተገበሩ መሆናቸው ጉልህ ክፍተታቸው ሆኖ ቆይቷል። ይህም ማለት መፃህፍቱ ሥላቀረቧቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች፣ ሰዋስዋዊ ህግጋቱ በግልጽ ተብራርተውና በምሳሌ ተደግፋው ሲቀርቡ አልታዩም። ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት ደግሞ በእያንዳንዱ ሰዋስዋዊ መዋቅር የቅርጽ፣ የአገባብና የፍቺ ልዩነት ላይ ግልጽ ትንተና የሚያደርግና ህግጋቱ እንዴት እንደሚሠሩና እንደሚተገበሩ የሚያስረዳና ማብራሪያ የሚቀርብ መሆኑን ገልፀን ነበር። በተጠቀሰው ዘመን የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ግን በዚህ ረገድ ከፍተኛ ውስንነት ታይቶባቸዋል።

4.3.1.5. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ1997 ዓ.ም

በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው ከ1968 ጀምሮ እስከ 1991/2 ዓ.ም ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ሥልት አደራጅቶ የማቅረቡ ጉዳይ ችል ተብሎ የቆየ መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል።

ይሁን እንጂ ይህ ሁኔት በ1997 ዓ.ም ተሻሽለው በቀረቡት የተተኳሪዎች ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ለውጥና መሻሻል ማሳየት ጀምሯል። በመሆኑን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደራጅቶ የማቅረቡ ሂደት መሻሻል ያሳየው በዚህ ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል።

ዝርዝር ጉዳዩን በመጀመሪያ ከ9ኛ ፣ ቀጥሎ ደግሞ ከ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የተለያዩ ገጾች ማሳያ የሚሆኑ ምሳሌዎችን በማንሳት እናያለን።

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰባት ያህል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ያቀራረብ ሥልት መሠረት፣ ማለትም ስለ ሰዋስዋ የትምህርት ይዘቶቹ ዝርዝር ማብራሪያ በመስጠት፣ ህግጋቱ እንዴት እንደሚሠሩ በምሳሌ አስደግፎ በማሳየት፣ ሥላቀረባቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች መዋቅራዊ ቅርጽ መግለጫ በማቅረብ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እንደ ክፍተት ሲታይ የነበረውን፣ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ሥልትን ተጠቅሞ የማደራጀት ችግር ለመቅረፍ ሞክሯል።

ሠንጠረዥ-2 በ1997 ዓ.ም በታተመዉ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ገጽ	ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ገጽ
1.	የቃል ክፍሎች	9	5	ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች	29
2.	የስም የቅርጽና አገባብ ባህሪያትና ሰዋስዋዊ ሙያ	9-10	6	የቃላት እማሬያዊና ፍክሬያዊ ፍቺ	85-86
3.	የምዕላድ ምንነትና አይነት	10-11	7	አያያዥ ቃላት	110
4.	የባለቤትና ተሣቢ አፀፋ	11-12			

መማሪያ መጽሐፉ ከላይ በሰንጠረዥ-2 የተዘረዘሩትን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ማቅረብ አለማቅረቡን ለማረጋገጥ፣ በዚህ ሥልት

ቀርበዋል የተባሉትን ሁሉንም ይዘቶች እዚህ ማቅረቡ አስፈላጊም ተገቢም ባለመሆኑ አንዱን ብቻ ለአብነት እንመለከታለን።

መማሪያ መጽሐፉ በገጽ 9 ላይ "ስም" የሚለውን የቃል ክፍል ያቀረበበትን መንገድ እንመለከት፡- ለተማሪዎቹ ማስተዋወቅ የጀመረው ከአምስቱ የቃል ክፍሎች አንዱ መሆኑን በመጠቆም ሥለ ቅርጹ፣ የአገባብ ባህሪው እና ሰዋስዋዊ ሙያዊ ሠፋ ያለ ማብራሪያና መግለጫ በማቅረብ ነው። ቀጥሎም ስም በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ባለቤትና ተሣቢ ሆኖ እንደሚገባ፣ ከቅርጽ አንፃር /-ኦች/ የሚለውን አብዝቶ ምዕላድ እንደሚወስድ፣ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ከሌሎች ተዋቃሪ አካላት ጋር በሚሰለፍበት ጊዜ ጠቋሚ ወይም መጣኝ መስተአምር ቀድሞት ሊገባ እንደሚችል እና አይነትን የሚገልጽ አጎላማሽ ሊወስድ እንደሚችል በመግለጽ ካስተዋወቀ በኋላ ስም፣ የባለቤትነትን፣ የተሳቢነትንና የዘርፍነትን ሙያ እንዴት እንደሚከውን በምሳሌ የተደገፈ ማስረጃ አቅርቧል። በመጨረሻም መጽሐፉ በተለያዩ ገጾቹ የተለያዩ መልመጃዎችን አቅርቧል።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ይህ የአቀራረብ ሥልት ሥለ ሠዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱ አሥቀድሞ ማብራሪያ በመስጠትና ቀጥሎም ሰዋስዋዊ ቅርጹ እንዴት እንደሚሠራ በምሳሌ የተደገፈ ማስረጃ ካቀረበ በኋላ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ቅርጽ የአገባብ ባህሪ በይበልጥ እንዲገነዘቡት ለማድረግ የተለያዩ መለማመጃዎችን የሚያስከትል የአቀራረብ ሥልት መሆኑን ገልፀን ነበር። ከዚህ አንፃር መማሪያ መጽሐፉ "ስም" የሚለውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ለተማሪዎቹ ያቀረበው በዚህ የአቀራረብ ሥልት ድንጋጌ መሠረት መሆኑን መረዳት ተችሏል። ቀሪዎቹ ስድስት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የቀረቡት በዚሁ ስልት በመሆኑ ዝርዝራቸውን አናየውም። በዚሁ ወደ 10ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ እንሸጋገራለን።

የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም አራት ያህል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት ያቀረበ መሆኑን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

ሠንጠረዥ-3 በ1997 ዓ.ም በታተመዉ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት	ገጽ	ተ.ቁ.	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት	ገጽ
1	የእርባታና ምስረታ ምዕላዶች	30	3	ቅጽላዊ ሐረግ	101
2	ተውሳከ ግሣዊ ሀረግ	56	4	መስተዋድዳዊ ሐረግ	117

በዚህ የአቀራረብ ሥልት መሠረት ከቀረቡት አራት ያህል ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ሦስቱ ሐረግን መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ተመሳሳይ የሆነ የአቀራረብ ስልት ታይቶባቸዋል። መማሪያ መጽሐፉ ከላይ የቀረቡትን ሦስት የሀረግ ዓይነቶች በተመለከተ ምንነታቸውን፣ አመሰራረታቸውን፣ መሪያቸውንና የመሪያቸውን አሠላለፍ በተመለከተ ማብራሪያ ካቀረበና በምሳሌ የተደገፈ መግለጫ ከሠጠ በኋላ ተማሪዎቹ የበለጠ እንዲረዷቸው የተለያዩ የመለማመጃ ጥያቄዎችን በመጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ አቅርቦላቸዋል። የእርባታና የምስረታ ምዕላዶችን በተመለከተ መጽሐፉ የተከተለው አቀራረብም ተመሳሳይ ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት በ1968ቱ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ጊዜ፣ በተመሳሳይ ወቅት በቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ጊዜና ጎላም በ1972ቱ የ10ኛ ክፍል መማሪያ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ታይቶ፤ በ1984 እና በ1991/2 ዓ.ም በታተሙት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ጭራሹኑ ተዘንግቶ የነበረው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ሥልት የማቅረቡ ሂደት በ1997 ዓ.ም ተሻሽለው በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በ9ኛ ክፍሉ 7 ጊዜና በ10ኛ ክፍሉ 4 ጊዜ ቀርቦ መታየቱ የተሻለ ትኩረትና ቦታ የተሠጠው መሆኑን ያሳያል።

ለዚህም ነው አስቀድመን ወቅቱ፣ ስልቱ በተተኳሪዎቹ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ማንሰራራት የጀመረበት ጊዜ ነው ያልነው። በርግጥ በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የተተኳሪዎቹ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት በውስጣቸው ካካተታቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች ብዛት አንፃር የአቀራረብ ሥልቱ ተገቢ የሆነ ትኩረት ተሠጥቶታል ማለት ባይቻልም ጭራሹኑ ከተረሳበት የ1984ቱ እና የ1991/2ቱ መፃህፍት አንፃር የተሻለ ሽፋንና ትኩረት አግኝቷል።

ይሁን እንጂ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ለተማሪዎች በማቅረብ ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረቦች በተመጣጠነ ሁኔታ ሊተገበሩ እንደሚገባቸው በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ገልፀን ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ሁለቱም የአቀራረብ ሥልቶች ደካማና ጠንካራ ጎን ያላቸው መሆናቸውና የአንዱ ድክመት በሌላው ጥንካሬ የሚሞላ በመሆኑ ነበር። ከዚህ አንፃር በዚህ ወቅት ማንሰራራት ያሳየው ይህ የአቀራረብ ስልት የሱ ግልባጭ ከሆነው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሥልት ጋር ሲነፃፀር ተመጣጥኗል ለማለት እንደማይቻል ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ችለናል።

4.3.1.6 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በ2004 ዓ.ም

በዚህ ወቅት እንደ አዲስ የቀረበው የ9ኛና ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በድምሩ ዘጠኝ ያህል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት ያቀረበ መሆኑን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

ሠንጠረዥ-4 በ2004 ዓ.ም በታተመዉ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት	ገጽ	ተ.ቁ.	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት	ገጽ
1.	የቃላት አገባባዊ ፍቺ	7	6	ሥነ ሐረግ	71
2.	ሥነ ምዕላድ	25	7	የአረፍተ ነገር ክፍሎች	86
3.	አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት	64	8	የቃላት መጥበቅና መላላት	125
4.	የቃላት አማራያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	67	9	አረፍተ ነገር	142
5	የቃላት ክፍሎች	69			

እነዚህን ከላይ በሰንጠረዥ-4 የተዘረዘሩትን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች፣ መማሪያ መጽሐፉ ለተማሪዎቹ ያቀረባቸው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ሥልት ነው። ይህንንም እንድንል ምክንያት የሆነን የትምህርት ይዘቶቹን በማቅረብ ሂደት የተብራራ ገለፃና ዝርዝር መግለጫዎችን አስቀድሞ በማምጣቱና ማብራሪያውን ተግባራዊ የሚያደርጉ ምሣሌዎችን በማቅረብ፣ ተማሪዎቹ የሚሠሯቸው መልመጃዎችን መጨረሻ ላይ በማምጣቱ ነው። በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ አይነቱ አቀራረብ ደግሞ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሆነ የአካሄድ ስልትን የተከተለ ነው።

ከላይ ከቀረቡት ማሳያዎች በመነሳት በዚህ ወቅት የታተመው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ከሱ በፊት ከቀረቡት ሁሉ በርከት ያሉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ አቀራረብ ስልት መሠረት ያቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ይህም ማለት በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ በቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጀመረው ይህ አቀራረብ ስልት የበለጠ ተጠናክሮና ትኩረት ተሠጥቶት መተግበሩን መረዳት ተችሏል። ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት የማቅረብ ሂደት እያደገና እየጎለበት መምጣቱ የሚበረታታ ቢሆንም በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ተካትተው ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ብዛት አንፃር አመዘኖ የሚገኘው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ነው።

በመጨረሻም በዚሁ ወቅት የቀረበው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በውስጡ ከያዛቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል 8 (ስምንት) ያህሉ በዚህ የአቀራረብ ሥልት ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው።

ሠንጠረዥ-5 በ2004 ዓ.ም በታተመዉ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ገጽ	ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ገጽ
1	ሀረግ	27 እና113	5	በቃላት ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾች	83
2	አያያዥና የመሸጋገሪ ቃላትና ሐረጋት	43	6	በቃላት ውስጥ የሚረዝሙና የሚያጥሩ ድምጾች	84
3	የዓረፍተ ነገር አየነቶች	44	7	የቃላት ቀጥተኛ ወይም መዝገብ ቃላዊ ፍቺ	96
4	የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	45	8	የቋንቋ ባህሪያት	10-12

እነዚህ ከላይ በሠንጠረዥ-5 በዝርዝር የቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ሥልት ተዋቅረው የቀረቡ ናቸው የተባሉበት ምክንያት በክለሳ ድርሳኑ ሥለ አቀራረብ ስልቱ ምንነት ያነሳነውን መስፈርት አሟልተው በመገኘታቸው ነው።

ለምሳሌ፡- በመማሪያ መጽሐፉ (ገጽ 27)ላይ "ሐረግ" በሚል ርዕስ ስር የቀረበውን የትምህርት ይዘት ብንመለከት መማሪያ መጽሐፉ ይዘቱን ለተማሪዎቹ ያቀረበበት ሥልት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አካሄድን ተክትሎ መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ምክንያቱም መጽሐፍ ይዘቱን በማቅረብ ረገድ የተከተለው የአቀራረብ ስልት በመጀመሪያ ደረጃ ሐረግን በተመለከተ ከመዋቅራዊ ቅርጽ አንፃር "ከቃል የሠፋና ከአረፍተ ነገር ግን ያነሰ" መሆኑን፣ "እያንዳንዱ የቃል ክፍል ከሌሎች ቃላት ጋር እየተቀናጀ ሀረግ የመመስረት እድል ያለው" መሆኑን፣ ከአይነት አንፃር ደግሞ በቃል ክፍሎች ቁጥር ልክ "ስማዊ፣ ቅጽላ፣ ግሣዊ፣ ተውሳከ ግሣዊ እና መስተዋድዳዊ" ተብለው በአምስት የሚከፈሉ መሆናቸውን፣ "የሀረጉ አይነት የሚወሰነውም በሐረጉ መሪ ቃል፣ የቃል ክፍል መሆኑን"ና ከዚህም የተነሳ "መሪው ስም ከሆነ ሐረጉ ስማዊ ሐረግ የሚባል መሆኑን..." የሚያስረዳ ሠፊ ማብራሪያና መግለጫ ካቀረበ በኋላ የተለያዩ ምሳሌዎች አቅርቧል።

ምሳሌ፡- አንሻ አክስቷን ለመጠየቅ ወደ አዳማ ሄደች።
የሐረጉ መሪ,= ሄደች
የሐረጉ አይነት= ግሣዊ ሐረግ
በማለት።

በመጨረሻም በቀረበው ምሣሌ መሠረት የሚሠሩና ከሥራቸው የተሠመረባቸው ሀረጎችን የያዙ አስር ያህል አረፍተ ነገሮችን አቅርቧል። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውም በቀረቡላቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸውን ሀረጋት መሪዎች በመለየት የሐረጉን አይነት መናገር (መግለጽ) ነው።

በመሆኑም በዚህ ወቅት የቀረበው መማሪያ መጽሐፍ "ሐረግን" በተመለከተ የቀረበውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት፣ ለተማሪዎቹ ለማቅረብ የተከተለው ሥልት፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አካሄድን መሠረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። ቀሪዎቹ ስምንት ያህል ይዘቶችም የቀረቡት በዚሁ መልክ ተመሳሳይ የሆነ ስልትን ተከትለው መሆናቸውን በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ በ1997 ተሻሽሎ ከቀረበውም ሆነ ከዚያ በፊት ከነበሩት የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ጋር ሲነፃፀር በተሻለ ሁኔታ የአቀራረብ ስልቱን የተገበረ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት በአዲስ መልክ የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ይህንን ሥልት ከመተግበር ወይንም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት መሠረት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር ከሌሎቹ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። በመሆኑም ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹን በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የማቅረብ ሂደት ተገቢ የሆነ ትኩረትና ሽፋን እያገኘ በመምጣቱ በ1997 የተጀመረው መነቃቃት ይበልጥ ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

4.3.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩትና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ

4.3.2.1.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1968 ዓ.ም

ይህ የአቀራረብ ስልት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱን ማቅረብ የሚጀምረው ዝርዝር ገለፃና ማብራሪያ በማቅረብ ሳይሆን በጥንቃቄ የተመረጡ ምሳሌዎችን በማቅረብና በእነዚያ ምሳሌዎች መሠረት፣ ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን መልመጃዎች ከሠሩ በኋላ ህግጋቱን በራሳቸው እንዲደርሱባቸው የማድረግ ስልትን የሚከተል መሆኑን በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ለመግለጽ

ሞክረናል። በዚህም መሠረት በ1968 ዓ.ም የታተመውን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በማስቀደም ሥልቱ መተግበር አለመተግበሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል በዚህ ሥልት ቀርቧል ተብሎ ለአብነት የሚጠቀሰው በ(ገጽ 74) ላይ የሚገኘው ቀጣዩ የትምህርት ይዘት ብቻ ነው። በዚህ ገጽ ላይ ሦስት ምሣሌዎች የቀረቡ ሲሆኑ በቀረቡት ምሣሌዎች ሥልት የሚሠሩ 12 ያህል የመለማመጃ ጥያቄዎች ምሣሌው ተከትለው ተዘርዝረዋል።

አስረጂዎቹ፡-

ሀ. ቢስ
ገፀ-ቢስ

ለ. አልባ
ሥርዓት-አልባ

ሐ. ኢ
ርቱዕ ኢ-ርቱዕ

የሚሉ ናቸው። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው በቀረቡላቸው አሥራ ሁለት ቃላት ተጠቅመው ከቃላቱ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ ተቀጥለው የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ቃላትን፣ መዝገበ ቃላት በመጠቀም ወይም ሠው በመጠየው መፈለግ ነው።

ይህ አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ለሆነ የአቀራረብ ስልት ማስረጃ ይሆናል ብለን ያቀረብነው አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው ስልቱ ምሣሌዎችን በመጀመሪያ ደረጃ በማቅረቡና ተማሪዎቹም በተሠጣቸው ምሣሌ መሰረት ቀጣይ መልመጃዎችንና ተግባራትን እንዲሠሩ የሚጋብዛቸው በመሆኑ ነው።

ይሁን እንጂ በተደረገው ፍተሻ ማረጋገጥ የተቻለው በዚህ መልኩ ተደራጅቶ ያገኘነው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ከላይ ለአብነት የተጠቀሰው ብቻ ነው። በመሆኑም በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር ድክመት የታየበት መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ወቅት ተዘጋጅቶ በነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም በዚህ የአቀራረብ ስልት ተቃኝተው የቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ሁለት ብቻ ናቸው ። የመጀመሪያው ከላይ በዘጠነኛ ክፍሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ (ገጽ 74) ላይ ያየነው የትምህርት ይዘት ምንም አይነት የአቀራረብም ሆነ የይዘት

ለውጥ ሳይደረግበት በ10ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ (ገጽ 69) ላይ የቀረበው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ(ገጽ 133) ላይ የሚገኘው ነው። በዚህ ገጽ ላይ የሚገኘው ይዘትም የሚከተለውን ይመስላል፦

"በምንባቡ ውስጥ 'ቅንጫቢ' ብሎ "ቅንጭብጫቢ" የሚል አነጋገር አለ፤ በዚህ አይነት የሚመሠረቱ አስር ያህል ቃላት ጽፈህ አቅርብና በመጀመሪያዎቹና በተመሰራቹ ቃል መካከል ያለውን የሐሳብ ልዩነት ተናገር።"

የሚል ነው።

ከላይ የቀረበው መመሪያ (ትዕዛዝ) የሚነግረን ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ተመሳሳይ የአመሠራረት ስልትን የሚከተሉ እንደ "ስባሪ፤ ልቃሚ፤ ጥራጊ..." አይነት ቃላትን በመፈለግ "ስብርባሪ፤ ልቅምቃሚ ጥርግራጊ..." አይነት ቃላትን እንዲመሠረቱና እንደ "ቅንጫቢ" እና ቅንጭብጫቢ ባሉት የመጀመያዎቹና ምስርቶቹ መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት እንዲናገሩ የሚጋብዝ መሆኑን ነው።

ይሁን እንጂ በተሠጠው ምሳሌ ውስጥ "ቅጭብጫቢ" የሚለው "አነጋገር" እንዴትና በምን የአመሠራረት ህግጋት ሊመሠረት እንደቻለ የቀረበ ማብራሪያም ሆነ ገለፃ ባለመኖሩና ተማሪዎቹ ከቀረበላቸው ምሳሌ ብቻ በመነሳት ተመሳሳይ የአመሠራረት ሥልት ያላቸውን ቃላት እንዲፈልጉ የሚያዝ በመሆኑ፤ የይዘቱ አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሥልትን የተከተለ ነው ለማለት ያስችላል።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ሥልት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር የ9ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ አንድ ሰዋስዋዊ ይዘት ብቻ ያቀረበ ሲሆን የ10ኛ ክፍሉም ከዚያ ያልተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑ መማሪያ መፃህፍቱ ሥልቱን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ክፍተት የታየባቸው መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

4.3.2.2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም

በ1973 ዓ.ም ተሻሽሎ በቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ የአቀራረብ ስልት ተደራጅተው የቀረቡት (አምስት) 5 ያህል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሠንጠረዥ-6 በ1972/3 ዓ.ም በታተመዉ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ገጽ	ተ.ቁ	ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች	ገጽ
1	የቃላ አገባባዊ ፍቺ	11	4	የስም ገላጮች	45
2	ጥምር ቃላት	38	5	ተመሳሳይ ፍቺ	109
3	የቃላት ምስረታ	39			

ላይ በሠንጠረዥ-6 ከቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል በ(ገጽ 39) ላይ የሚገኘውን ይዘት አቀራረብ በአስረጂነት እንመልከት።

(ገጽ 39) በ"5" ረድፍ ማለትም በ"ሀ"፣ በ"ለ"፣ በ"ሐ"፣ በ "መ"ና በ "ሠ" የተሠጠውን የመጀመሪያ ምዛሌ ተመልክተህ ለእያንዳንዱ ቃል በተተወልህ ክፍት ቦታዎች ሁሉ አብረው ሊሄዱ የሚችሉትን ቃላት መላ።

በማለት የሚከተለውን ምዛሌ አቅርቧል።

ምሳሌ፡-

	ሀ	ለ	ሐ	መ	ሠ
ሀ	ወዘፈ	ተወዘፈ	ወዛፍ	ተወዛፍ	ውዝፍ

በዚህ ምሳሌ መሰረት 10 ግሶች ቀርበዋል።

ከላይ በምሳሌ አንድ ሥር ተዘርዝሮ ስለቀረበው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አቀራረብ በርካታ ነገሮች ማለት ቢቻልም ከጥናቱ ትኩረት አንፃር እየቃኘን ያለነው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ያለውን አካሄድ ብቻ በመሆኑ የግልጽነት፣ ተገቢነት ወዘተ ጉዳይ ወደ ጎን እንተወዋለን። በመሆኑም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብን ብቻ መሠረት አድርገን የአቀራረብ ሥልቱን ስንፈትሽ፣ ከቀረበው ምሳሌ መረዳት የምንችለው ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምዛሌዎች መሠረት በማድረግ ቀሪዎቹን የመልመጃ ጥያቄዎች በመስራት ሂደት ወደ ሚፈለገው ግብ በራሳቸው ጊዜ እንዲደርሱ የሚያደርግ የአካሄድ ስልትን የተከተለ በመሆኑና ስለ ሰዋስዋዊ ይዘቱ የተለያዩ ባህሪያት ያቀረበው ዝርዝር ማብራሪያና መግለጫ ያለመኖሩ፣ መማሪያ መጽሐፉ ከላይ የቀረበውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ስልት ያቀረባቸው መሆኑን መረዳት እንችላለን።

በመሆኑም በዚህ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ስልት አደራጅቶ በማቅረብ

ረገድ ከ1968ቱ የተሻለ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የ1968ቱ መማሪያ መጽሐፍ በዚህ ስልት ያቀረበው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አንድ ብቻ ሲሆን ይኸኛው ግን አምስት ያህል ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ሥልት አቅርቧቸዋልና።

በሌላ በኩል በ1972 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከያዛቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ስልት ያቀረበው በ(ገጽ 16) ላይ የሚገኘውን አንድ ይዘት ብቻ ነው። በዚህ ስልት ቀርቧል የተባለው ይህ የትምህርት ይዘት በ1968 ዓ.ም. ከቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ (ገጽ 74) ላይ እንዳለ የተወሰደ በመሆኑና ዝርዝር አቀራረቡንም በዚያው ክፍል ያየነው በመሆኑ አንደግመውም።

ከዚህ አንፃር የ1972ቱ የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ከላይ ከተጠቀሰው አንድ ይዘት በስተቀር በዚህ የአቀራረብ ሥልት ተደራጅቶ የቀረበ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት የሌለው በመሆኑ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ አካሄድ የማቅረብ ብቃቱ በጣም ደካማና በ1968 ተዘጋጅቶ ከቀረበውም ያልተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም በተጠቀሰው ጊዜ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የማቅረቢያ ስልት ተጠቅመው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በተገቢው መጠንና ልክ ያለማቅረባቸውን መገንዘብ ተችሏል።

4.3.2.3. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1984 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተዘጋጅተው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አካትተው መቅረባቸውን አስቀድመን ለመግለጽ ሞክረን ነበር። በተጨማሪም እነዚሁ መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ተጠቅመው ማቅረብ አለማቅረባቸውን በቃኘንበት ክፍል በዚህ ሥልት የቀረበ ምንም አይነት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት እንዳልተገኘም ጠቁመን ነበር።

በዚህ ወቅት የቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ስልት ማቅረብ አለማቅረቡን ለማወቅ በተደረገው ጥናት ማረጋገጥ የተቻለው በውስጡ አካትቶ የያዛቸውን ሁሉንም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ያቀረባቸው በዚህ ሥልት መሆኑን ነው።

እነዚህን በዚህ የአቀራረብ ስልት ተደራጅተው የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ሁሉንም በዚህ ክፍል እናያቸውም። ነገር ግን ለማስረጃ ያህል፦

- ገጽ 5. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት በተሠጠህ ምሳሌ መሠረት ስያሜ አውጣላቸው።

ምሳሌ፦ አከማች= ክምችት

ቀለጠፈ= ቅልጥፍና

የሚሉ ምሳሌዎችን ካቀረበ በኋላ በዚህ መሠረት የሚሠሩ ስድስት ያህል የተለያዩ ግሶችን አቅርቧል። በዚህ ስልት የቀረቡ በርካታ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ በ(ገጽ 19፣25፣33፣34፣54፣60፣61፣73) ላይ ይገኛሉ።

እንግዲህ ከላይ ያቀረብናቸው ምሳሌዎች በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ አካሄድ ማቅረቡን የሚያስረዱ ናቸው። ለአብነት ያህል ብቻ እነዚህን አቀረብናቸው እንጂ ሌሎቹም በተመሳሳይ የአቀራረብ ሥልት የቀረቡ ናቸው።

ከላይ ከቀረበው ምሳሌ የምንረዳው መማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹን ለተማሪዎች በሚያደራጅበት ጊዜ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ያቀረበው ይዘቱን የሚገልጽና የሚያስረዳ ማብራሪያ ሳይሆን፣ ሞዴል የሆኑ ምሳሌዎችን ብቻ ነው። ምሳሌዎቹም በሰዋስዋዊ ትምህርቱ ዙሪያ ተማሪዎቹን አንዳች አይነት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ናቸው። ቀጥሎም በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት የሚሠሩና ከምሳሌዎቹ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የአካሄድ ስልት ያላቸው መልመጃዎችን አቅርቧል። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው፣ የተሰጣቸው ምንም አይነት መግለጫና ማብራሪያ ሳይኖር ከቀረበላቸው ምሳሌና በዚያ መሠረት ከሚሠሩት መልመጃዎች በመነሳት ወደ ተፈለገው ግብ መድረስ ነው። ይህ አይነቱ የአቀራረብ ስልት ደግሞ ቀደም ተብሎ እንደተገለፀው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሆነ አካሄድን ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቢያ ስልት ያልነው ነው።

በመሆኑም በዚህ ወቅት ተዘጋጅቶ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀረረብ ሥልት ተጠቅሞ ከማቅረብ አንፃር የበለፀገ ነው ማለት ይቻላል።

ይሁን እንጂ በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ለመግለጽ እንደሞከርነው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርም ሆነ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አካሄድ የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው። አንዱ አካሄድ

የሌለው ግልባጭ በመሆኑ የአንዱ ክፍተትና ድክመት በሌላው ጥንካሬ እንደሚካካስም አውስተን ነበር። በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችም በሁለቱም ሥልቶች በተመጣጣነ ሁኔታ መቅረብ እንዳለባቸው ጠቁመን ነበር።

እዚህ የምናስተውለው ግን እንደዚያ አይደለም፤ የዚያን ግልባጭ እንጂ። መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ሁሉም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ሥልት ብቻ መቅረባቸው፣ መጽሐፉ አቀራረቡን በተመለከተ በስፋት ተግብሮታል ቢባልም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ደግሞ ፈጽሞ የዘነጋና ችል ያለ መሆኑ ደግሞ በጣም ደካማ ያለኝዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በዚህ ወቅት የቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም አካትቶ የያዛቸው በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ያቀረበው በዚሁ ስልት ነው። ማሳያ የሚሆኑ ምሳሌዎችን በጥቂቱ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

- ገጽ 4 ከዚህ ቀጥሎ በተሠጠህ ምሳሌ መሠረት የስም ገላጮችን ለይተህ በማውጣት አሳይ። ምሳሌ፦ <u>እውነተኛ</u> ታሪክ አይረሳም። የተሠመረበት ቃል የሥም ገላጭ ነው።

ምሣሌውን መሠረት በማድረግ የሚሠሩ 5 ዐ.ነገሮች ቀርበዋል።

ከላይ የቀረበው ማስረጃ የሚያሳየን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ሥልት መሠረት የቀረበ መሆኑን ነው። በመሆኑም ከዚህ የማቅረቢያ መስፈርት አንፃር መጽሐፉ ጠንካራ ነው ቢባልም በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ እንዳየነው ሁሉ እዚህኛውም መጽሐፍ ውስጥ የታየው ችግር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረቦችን አመጣጥኖ ያለማቅረብ ነው። ተመሳሳይ የአቀራረብ ስልት ያላቸው ይዘቶች በ(ገጽ 5፣16፣47፣52፣ና63) ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት ከማቅረብ አንፃር ከእነሱ በፊት ቀርበው ከነበሩት ጋር ሲነፃፀሩ በከፍተኛ መጠን ተግብረውታል ቢባልም አስቀድመን እንደገለጽነው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ባለመጠቀማቸው የሚዛናዊነት ችግር ታይቶባቸዋል።

4.3.2.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም

በዚህ ወቅት የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ከያዟቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል በዚህ ስልት ያቀረቧቸው ነበሩ። ሁሉንም በዝርዝር ለማቅረብ ሁኔታው ሥለማይፈቅድ ለማሣያ ያህል የተወሰኑትን ብቻ ለመጥቀስ እንሞክራለን። በመጀመሪያ የ9ኛ ክፍሉን እናይና የ10ኛውን እንቀጥላለን።

- (ገጽ 42) ምሣሌውን መሠረት በማድረግ አዳዲስ ቃሎችን መስርቱ

ምሳሌ፡- ከተተ= መክተት

ወደደች= መውደድ

በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚሠሩ 8 ቃላት ቀርበዋል።

ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቱ አርዕስታዊ ስም እንዴት እንደሚመሠረት የሚያሳይ ነው። ይሁን እንጂ በቀረበበት ሁኔታ ስለ ግስና አርዕስታዊ ስም ምንነት፣ ስለ አርዕስት አመሠራረት እና መሠል ጉዳዮች የተሠጠ ወይም የቀረበ ማብራሪያ የለም። ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምሣሌ መሠረት በማድረግ ብቻ መልመጃውን ለመስራት ጥረት ያደርጋሉ። በዚህም ሂደት "በተደጋጋሚ በሚደረግ ልምምድና ሙከራ ወደ ተፈለገው ግብ ይደርሳሉ" የሚለውን የአቀራረቡን መርህ መሠረት ባደረገ መልኩ የተዋቀሩ ይዘቶች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ተመሳሳይ የአቀራረብ ስልት ያላቸው ይዘቶች በ(ገጽ 5፣ 18፣ 19፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 36፣ 37፣ 42፣ 49፣ 52፣ 57፣ 58፣ 66፣ 71፣ 81፣ 82፣ 91፣ 110፣ 115) ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ በመነሳት በዚህ ወቅት ቀርቦ በነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ሥልት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር ሠፊ ሥራ ተሠርቷል ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ መጽሐፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ያለመተግበሩ እዚህም ጋ ያለ በመሆኑ ከወቀሳ አያመልጥም።

በዚሁ ወቅት ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ሥልት የማቅረቡ ሥራ የተተገበረ መሆኑን ከሚከተሉት ማሣያዎች መረዳት ይቻላል።

- ገጽ 143 ከሚለተሉት ቃላት መጨረሻ ላይ የተለያዩ የእርባታና የምስረታ ምዕላዶችን በመጨመር ቃላቱን አሥፋፉ።

ምሣሌ፦ 1. ዐመል 2. ሕዝብ

ሀ. ዐመለኛ ሀ. ሕዝባዊ

ለ. ዐመለኛነት ለ. ሕዝባዊው

ሐ. ዐመለኛነትህ ሐ. ሕዝባዊውን

በምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 10 ቃላት ቀርበዋል።

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት የሚቻለው በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር ሥልቱን ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ነው።በዚ ስልት የቀረቡ ይዘቶች በመጽሀፉ (ገጽ9፣ 10፣ 21፣ 31፣ 41፣ 48፣ 49፣ 60፣ 66፣ 67፣ 85፣ 104፣ 115፣ 116፣ 135፣ 143፣154) ላይ ይገኛሉ።

ይህንኑ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ስልት ማቅረብ አለማቅረቡን በቃኘንበት ክፍል መጽሐፍ በዚህ ስልት ያቀረበው አንድም ሠዋስዋዊ የትምህርት ይዘት እንዳልነበረ በቦታው ጠቁመን ነበር።

መጽሐፉ ሁሉንም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ ስልት ማቅረቡና ከአጠቃላይ ወደ ዝረዝር በሆነ ሥልት ደግሞ ምንም አይነት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት ያለማቅረቡ ደካማ ቢያሰኘውም፤ በአጠቃላይ በ1984-ም ሆነ በ1991/2 ዓ.ም ቀርበው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሆነ አቀራረብን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ጠንካሮች ነበሩ ማለት ይቻላል።

4.3.2.5. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ1997 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ ቀርቦ በነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ገጾቹ ላይ፣ በተጠቀሰው የአቀራረብ ስልት የቀረቡ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ይገኛሉ። ከዚህ በፊት እንደምናደርገው ሁሉ ለማስረጃ ያህል የተወሰኑትን ብቻ እንጠቅሳለን።

❖ (ገጽ 30) ተራ ቁጥር አንድን ምሳሌ በማድረግ ባዶ ቦታዎቹን በተስማሚ ቃሎች አሟሉ

ምሳሌ፦

1	ሰበረ	ሰባበረ	ተሰባበረ	አሳበረ	ሰበራ	ሰባራ	ስባሪ	መስበር

ምሣሌውን መሠረት አድርገው የሚሠሩ 10 ያህል ግሶች ቀርበዋል። በዚህ ስልት የቀረቡ ይዘቶች በ(ገጽ 12፣25፣26፣29፣31፣45፣46፣52፣59፣68፣69፣77፣78፣79) ላይ ይገኛሉ።

ከላይ ከቀረበው ምሳሌ መገንዘብ የሚቻለው መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ስልት ያቀረበ መሆኑን ነው። ይህንንም ለማለት መነሻ የሆነን በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ስለአቀራረቡ ያቀረብነው ገለፃ ነው። መማሪያ መጽሐፉ ይዘቶቹን በማቅረብ ሂደት ያቀረበው ማብራሪያም ሆነ መግለጫ አይገኝም። ምሳሌዎችን አስቀድሞ በማምጣትና መልመጃዎችን በማስከተል ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ምሳሌ መሠረት መልመጃውን እንዲሠሩ የማድረግ ስልትን የተከተለ ነው። ይህ የአካሄድ ሥልት ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ መሆኑን ደጋግመን ገልፀነዋል።

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዚህ የአቀራረብ ሥልት አንፃር በማደራጀት ረገድ በ1991 ዓ.ም ከታተመው መጽሐፍ ጋር ሲነፃፀር የጎላ ልዩነት አይታይበትም። ምክንያቱም በአንድ በኩል ሁሉም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ሊባል በሚችል መልኩ የተደገሙ ሲሆኑ በሌላ መልኩ እንደ አዲስ ከቀረቡትም መካከል በርካታዎቹ በዚህ ሥልት ተዋቅረው በመቅረባቸው ነው።

በዚሁ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ያቀራረብ ስልት በበርካታ ገጾቹ ላይ አቅርቧል። ለአብነትም ያህል የሚከተሉትን እናነሳለን።

❖ ገጽ 38 ቀጥሎ የቀረቡትን ምሣሌዎች መሠረት በማድረግ ከተከታዮቹ ግሶች ቅጽሎችን ወይም ስሞችን መስርቱ

ምሳሌ ሀ. ከበደ= ከባድ (ቅጽል)

ለ. በላ= በላተኛ (ስም)

ምሣሌውን መሠረት በማድረግ የሚሠሩ 10 ያህል ግሶች ቀርበዋል።

በዚህ የአቀራረብ ስልት መሰረት ተዋቅረው የቀረቡ ይዘቶች በ(9፣ 20፣ 21፣ 26፣ 28፣ 29፣ 35፣ 38፣ 48፣ 55፣ 92፣ 101፣ 102፣ 111፣ 116፣ 158) ላይ ይገኛሉ።

ከላይ በዝርዝር ያቀረብናቸው ምሣሌዎች መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማደራጀቱን የሚያሳዩ ናቸው። ይህንንም ያልንበት ምክንያት በተደጋጋሚ ስለገለጽነው አንደግመውም።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ይህንን ስልት ተጠቅመው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር በ1991/2 ከታተሙት ጋርም ሆነ በ1984 ቀርበው ከነበሩት አንፃር ሲነፃፀሩ(በተለይ የ10ኛው) የተሻለ ነው ማለት እንችላለን። ምክንያቱም በ1984 እና 1991/2 ዓ.ም ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት በውስጣቸው ያለውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አጠቃላይ ያቀረቡት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ስልት ብቻ ነበር። የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት ብቻ ማቅረብ ደግሞ ተገቢ ያለመሆኑን በምዕራፍ 2 ጠቁመናል። ምክንያቱም ደግሞ የአቀራረብ ስልቱ ደካማ ጎን አለውና ነው። በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት መጻህፍት አብዛኛውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልትን ተከትለው ያቀረቡ ሆነው ተገኝተዋል። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልትንም የመተግበር አዝማሚያ ያሳዩ በመሆናቸው የተሻሉ ያሰኛቸዋል።

4.3.2.6.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ በ2004 ዓ.ም

በዚህ ወቅት በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ይህንን ያቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አደራጅቶ ማቅረቡን ከሚከተሉት ማስረጃዎች መገንዘብ ተችሏል።

- *(ገጽ 70) በሚከተለው ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር አንድ የቀረበውን ምሣሌ መሠረት በማድረግ ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ግሶች አሟሉ።*

ምሳሌ፦

ቡተነ	ተቡተነ	አስቡተነ	አባተነ	ቦታተነ	ተቦታተነ	አስቦታተነ

በዚህ መልኩ የሚሠሩ 10 ያህል ግሶች ቀርበዋል። በዚህ ስልት የቀረቡ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ (ገጽ 7፣39፣70፣109፣124፣128፣141፣154፣156፣171፣172፣173) ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች የሚያሳዩን መማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ስልት አደራጅቶ ማቅረቡን ነው። ምክንያታችን ደግሞ ሥለ አቀራረብ ሥልቱ በክለሳ ድርሳኑ ምዕራፍ 2 ላይ ያቀረብነውን ገለፃ ያሟሉ መሆናቸው ነው።

በዚሁ ወቅት እንደ አዲስ ተዘጋጅቶ የቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም በተለያዩ ገጾቹ ላይ ይህንኑ የአቀራረብ ሥልት ተጠቅሞ የተለያዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አቅርቧል።

- *(ገጽ 60) ከአንድ ግስ እስከ አምስት የሚደርሱ ስሞችን መመስረት ይቻላል።*

ምሳሌ፦

ተ.ቁ	ግስ	ጥሬ ዘራዊ ስም	ሳቢ ዘራዊ ስም	አርዕስታዊ ስም	ግልጋሎታዊ ስም	ውጤታዊ ስም
1	ሾመ	ሹመት	አሻሻም	መሾም	መሾሚያ	ሹም
2	መረጠ	ምርጫ	አመራረጥ	መምረጥ	መምረጫ	ምርጥ
3	ሞት	ሞት	አሟሟት	መሞት	መሞቻ	መ·ት

በምሳሌው መሠረት የሚሠሩ 5 ግሶች ቀርበዋል።በዚህ ስልት የቀረቡ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ (ገጽ 14፣26፣61፣64፣74፣82፣84፣96፣125፣127፣169) ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ ከላይ ያቀረብናቸው ምሳሌዎች መማሪያ መጽሐፉ የአቀራረብ ስልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ አካሄድ ያቀረበ ለመሆኑ ማሣያዎች ናቸው።

በዚህ ወቅት የቀረቡት የመማሪያ መፃህፍት ከዚህ የአቀራረብ ሥልት አንፃር ከሁሉም የተሻሉ ናቸው። ምክንያቱም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ሥልት ብቻ ከማቅረብ ይልቅ ሁለቱንም ሥልቶች በተመጣጠነ ደረጃ የተጠቀሙ ናቸውና።

በአጠቃላይ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ያለውን የዚህ አቀራረብ ስልት ጉዞ ስናይ ሦስት ገጽታ ያለው ሆኖ እናገኛዋለን። የመጀመሪያው በ1968 እና 1972/3 ዓ.ም ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እጅግ በጥቂቱ ሊባል በሚችል መልኩ የተከሠተበት ወቅት ነው።

ሁለተኛው በ1984 እና 1991/2 ዓ.ም ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ደግሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በሙሉ በዚህ ሥልት የማቅረብ ሂደት የታየበት ሲሆን ሦስተኛው በ1997 እና በ2004 ዓ.ም በቀረቡት መፃህፍት ውስጥ ግን ከፊል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደዝርዝር ቀሪዎቹን ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ የአቀራረብ ሥልት ማቅረብ የተጀመረበትና እየጎለበት የመጣበት መሆኑን ካደረግ ነው የሠነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ችለናል።

ቀጣዩ ንዑስ ክፍል ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በተደጋጋሚ እየተዘጋጁት እና እየተሻሻሉ አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩትና አሁንም በመስጠት ላይ ባሉት የ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በውጤት ተኮር የአቀራረብ ሥልት መቅረብ አለመቅረባቸውን እና ከቀረቡም በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥ የምንዳስስበት ነው።

4.3.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም በነበሩትና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ

በዚህ ንዑስ ክፍል የምንመለከተው ሰዋስዋው የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት አደራጅቶ የማቅረቡ ሂደት ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ምን መልክ እንደነበረውና እንዳለው ነው።

እንደ ሐዋዝ 2000፡16 ገለጻ ይህ የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች ቋንቋዊ ቅርጾችን እየዘረዘሩ እንዲገልጿቸው፣ እንዲለውጧቸው፣ እንደገና እንዲያዋቅሯቸውና ሰዋስዋዊ ህጉ እንዴት እንደሚሠራ ግንዛቤ እንዲያገኙ እድል የሚሠጣቸው የአቀራረብ ስልት ነው። በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለጸውም ስልቱ መሠረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ባሉት የቋንቋው ቅርጾች ላይ ሲሆን ተማሪዎቹ በቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጽ ላይ በማተኮር የቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተ ነገራት አመሠራረት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግን ማዕከል ያደረገ የአቀራረብ ዘዴ ነው።

4.3.3.1. ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1968 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ ለአገልግሎት የበቃውን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ የአቀራረብ ስልቱን ተጠቀሞ ያቀረባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ የዚህ ጥናት አቅራቢ ባደረገው አሰሳ መገንዘብ የቻለው፣ በዚህ የአቀራረብ ስልት ተደራጅቶ የቀረበ አንድም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አለመኖሩን ነው።

ጉዳዩ በዚህ ብቻ አያበቃም። በተመሳሳይ ወቅት በተዘጋጀውና አገልግሎት ላይ ውሎ በነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ከዘጠነኛ ክፍሉ የተለየ ለውጥ አልታየበትም። መሆኑም በወቅቱ ተዘጋጅተው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በዚህ ረገድ ያቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አለመኖሩ ታውቋል።

ይህም በመሆኑ የአቀራረብ ስልቱ ከነበረው ሥነ ትምህርታዊ ጠቀሜታ ወይም ጠንካራ ጎን አንፃር ማለትም፤ የቋንቋው ቅርፆች እንዴት እንደሚዋቀሩና ሰዋስዋዊ ህጉም በምን መልኩ እንደሚሠራ ወይም ተግባራዊ እንደሚደረግ ተማሪዎቹ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ዕድል አሳጥቷቸዋል።

ይሁን እንጂ ይህ እንዲሆን የተደረገው አዘጋጅ ቡድኑ የሰዋስውን ትምህርት በተመለከተ በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በምን መልኩ መቅረብ እንዳለበት በተከተለው አቋምና በወሰደው እርምጃ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

ለዚህ ድምዳሜ መነሻ የሆነን ጉዳይ ወደ "መማሪያ መጽሐፉ አቋም" እንድን መለስ ይጋብዘናል። አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው አዘጋጆቹ "የመማሪያ መጽሐፉ አቋም" በሚለው ክፍል ሰዋስው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለብቻው ተነጥሎ መቅረብ እንደሌ ለበት፣ ተማሪዎቹ የሚሠሩት ስህተትም መታረም ያለበት(የሚገባው) በሰዋስው ትንታኔ ላይ በተመሠረተ የአካሄድ ስልት መሆን እንደማይገባውና ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በቃል አሥጠንቶ ፈተና ላይ ማቅረብ ተገቢ የምዘና ሥልት ያለመሆኑን ማስፈራቸውን ገልፀው ስለ ነበረ ነው። ውጤቱም የነገረን በዝግጅቱ ወቅት ይህንኑ አቋማቸው የተገበሩት መሆናቸውን ነው።

በርግጥ በሰዋስው ትምህርት ረገድ የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥም ሆነ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ የቋንቋው ህግ በመተንተን ላይ ብቻ አተኩሮ ሳይሆን

ፍቺን፣ አገባብና አጠቃቀምንም ጭምር አዋህዶ መቅረብ እነደነበረበት ይታመናል። ይሁን እንጂ ለቅርፃዊ ሰዋስው ምንም ቦታ ያልሠጠውና ትኩረቱን በተግባቦት ላይ ብቻ ያደረገው የወቅቱ የመማሪያ መፃህፍት ዝግጅት፤ ወቅቱ ቅርፃዊ ሰዋስው ችላ የተባለበት ከመሆን አልፎ ሆነ ተብሎ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ እንዳይካተትና ከመማሪያ ክፍል ውስጥም እንዲርቅ የተደረገበት ነበር ማለት ይቻላል።

ነገር ግን ተማሪዎቹ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓትን ጠብቀው በአግባቡ ለመገልገል፣ የቋንቋውን ህግጋትና ባህሪያት ማወቅ አሥፈላጊያቸው መሆኑና፤ የቋንቋውን ህግጋትና ባህሪያት የሚያሳይ አካሄድን የተከተለ የመማሪያ መፃህፍት ዝግጅትም ሆነ የቋንቋ ትምህርት አሠጣጥ ደግሞ፣ የተማሪውን የቋንቋ ብቃት የተሟላ ስለሚያደርገው የቅርፃዊ ሰዋስውን ትምህርት ከፍቺ፣ አገባብና አጠቃቀም ጋር አጣምሮ ማስተማርና ይዘቱንም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ አካትቶ ማቅረብ ባይረሳ ይመረጥ ነበር።

4.3.3.2. ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዚህ የአቀራረብ ስልት ያቀረባቸውን ሁለት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች (ገጽ 45 ና 39) ላይ እናገኛቸዋለን። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች፣ አቀራረባቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አካሄድን የተከተለ በመሆኑ በዚያው ክፍል አንስተናቸው ነበር። ይሁን እና ሰዋስዋዊ ይዘቱ በቋንቋው ቅርጽ ላይ ብቻ ያተኮረና አቀራረቡም ውጤት ተኮር ስልትን የተከተለ በመሆኑ እዚህም እንጠቅሳለን። ዝርዝሩን ከ(ገጽ 68) ይመለከታል። ከዚህ በመነሳት አቀራረቡ በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተገቢ ቦታ ያልተሠጠው መሆኑን እንረዳለን።

በሌላ በኩል በ1972 ዓ.ም ተሻሽሎ ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን የአቀራረብ ስልት ተከትሎ የቀረበ ምንም አይነት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አይገኝም።

በአጠቃላይ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተከትሎ የቀረበ ሰዋስዋዊ ይዘትን በተመለከተ በ1973 ዓ.ም በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ውስጥ (ገጽ 39 እና 45) ላይ ሁለት ጊዜ ከመቅረቡ በስተቀር ጭራሽ ተዘንግቷል ማለት ይቻላል። በመሆኑም ዘመኑን የቅርፃዊ ሰዋስው የዝንጋታ ዘመን ልንለው እንችላለን።

በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ስለ "መማሪያ መፃህፍት አይነቶች" በገለጽንበት ወቅት ዘመናዊ ወይም ተግባቦታዊ የምንላቸው መማሪያ መፃህፍት በሚዘጋጁበት ወቅት ታሳቢ የሚያደርጉት፣ ተማሪዎቹ በቋንቋው እንዲግባቡ ማድረግን በመሆኑ ከቋንቋው ቅርጽ ይልቅ ለቋንቋው ተግባር ወይም ተግባቦት ትኩረት የሚሠጡ መሆናቸውን ገልፀን ነበር። የወቅቱ መማሪያ መፃህፍትም በዚህ ሥልት የተቃኙ ይመስላሉ። ምክንያቱም መፃህፍቱ ምንም እንኳን ቅርፃዊ ሰዋስውን ባያካትቱም የመፃህፍቱ አጠቃላይ ገጽታ የሚነግረን ለተግባቦታዊ ክንዋኔዎች የተሻለ ቦታ የሠጡ መሆናቸውን ነው። በዚሁ ወደ 1984ቱ መማሪያ መፃህፍት እናልፋለን።

4.3.3.3. ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1984 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በውስጡ አካትቶ ከያዛቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል በዚህ የአቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ያቀረባቸው መኖራቸውን ከሚከተሉት ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል።

- *ገጽ 60 የሚከተሉትን የመድረሻ አብዥ ቅጥያዎች ["-ዎች"፣ "-ኦች" ወይም "-ኣት"] በመጠቀም ቀጥሎ ያሉትን ቃላት ወደ ብዙ ቁጥር ለውጣቸው።*

  ምሳሌ፡- *ሀ. ገበሬ= ገበሬዎች (-ዎች)*

  ለ. ልምድ= ልምዶች (-ኦች)

  ሐ. ቃል= ቃላት (-ኣት)

በቀረበው ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 10 ያህል ስሞች ተዘርዝረው ቀርበዋል።

በዚህ ስልት የቀረቡ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች በሥፋት እናገኛለን። ለምሳሌ፡- ከግስ ስም መመስረት (ገጽ 5፣) የስም ገላጮች (ገጽ 12፣ 24፣ 25፣ 32፣ 54 እና 70) ቅጥያዎችን መለየት (ገጽ 19)፣ ከስም ቅጽል መመስረት (ገጽ 54)፣ የግስ እርባታ (ገጽ 60)፣ ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ (ገጽ 70)፣ የዉልድ ግሶች አመሰራረት (ገጽ 34)፣ ነጠላ ቁጥሮችን ወደ ብዙ ቁጥር መለወጥ (ገጽ 6) እና ያሉ ይዘቶች በዚህ የአቀራረብ ሥልት የቀረቡ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል።

በመሆኑም ከላይ ማሳያ ይሆናሉ ተብለው ከቀረቡት ምሳሌዎች የምንረዳው በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት አዋቅሮ ማቅረቡን ነው።

በ1968 በታተመው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ ስልት ተደራጅቶ ቀረበ ሰዋስዋዊ የትምህርትይዘት እንደሌለና በ1973 ተሻሽሎ በቀረበው ውስጥ ግን ሁለት ይዘቶች ብቻ በዚህ ስልት ቀርበው እንደነበር ገልፀን ነበር። በ1984 ዓ.ም ቀርቦ ከነበረው መማሪያ መጽሐፍ የምንረዳው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ አቀራረብ ስልት ተጠቅሞ የማቅረቡ ክፍተት የተሞላ ይመስላል። በመሆኑም የ1984ቱ መማሪያ መጽሐፍ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል የታየበት ሆኖ ተገኝቷል።

በተመሳሳይ መልኩ በ1984 ዓ.ም ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ የአቀራረብ ሥልት መሠረት ቀርበው እናገኛቸዋለን። ማሣያ የሚሆኑ ምሳሌዎችን ቀጥለን እናቀርባለን።

- ገጽ 16፡- "በኃላም" በሚለው ቃል ውስጥ "በ-" መነሻ ቅጥያ፣ "-ም" መድረሻ ቅጥያ በመባል ይታወቃሉ። ከምንባቡ ውስጥ የእነዚህ አይነት ቅጥያዎች ያሏቸውን ቃላት አውጥተህ ቃሉን ከቅጥያዎቻቸው ለይተህ አሳይ።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ትዕዛዛት የሚያመለክቱት መማሪያ መጽሐፉ በውጤት ተኮር ሥልት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማቅረቡን ነው ። በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ እነዚህን መሠል ትዕዛዛት እናገኛለን። ከዚህ በመነሳት በዚህ ወቅት ተዘጋጅቶ የነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዚህ ረገድ ጠንካራ ጎን ታይቶበታል። ምክንያቱም በ1968 ቀርቦ በነበረው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ሆነ በ1972 ተሻሽሎ በቀረበው ምንም አይነት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት በዚህ የአቀራረብ ስልት ተደራጅቶ አልተገኘም ነበርና። በመሆኑም በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው የ1984ቱ መማሪያ መጽሐፍ ነው ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት ከማቅረብ አንፃር በፊት ከነበሩት እጅግ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል።

በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ስለመማሪያ መፃህፍት አይነቶች ባነሳንበት ጊዜ ጥንታዊ ወይም መዋቅራዊ የሚባሉት መማሪያ መፃህፍት ዋነኛ ትኩረታቸው በቋንቋው መዋቅር ወይም ሥርዓት ላይ ሲሆን ዓላማቸውም "ተማሪዎቹ በቋንቋው የመዋቅር እውቀት ካላቸው በቋንቋው መግባባት ይችላሉ" የሚለውን ሃሣብ የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው ለቋንቋው ቅርፃዊ ጉዳይ ወይም ሰዋስው ከፍተኛውን ትኩረት እንደሚሠጡ ገልፀን ነበር።

በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍትም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ረገድ በቅርጽ ላይ በማተኮራቸው ይህ ሁነት ተንፀባርቆባቸዋል። ምክንያቱም መፃህፍቱ በአብዛኛው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹን በቅደም ተከተል በሚያቀርቡበት ጊዜ ትኩረት ያደረጉት፣ ቅርጾቹ በተግባራዊ ተግባቦት ወቅት የሚኖራቸውን ሚና ወይም በእውናዊ የቋንቋ አጠቃቀም ወቅት እንዴት እንደሚገለገሉባቸው በሚያሳይ መልኩ ሳይሆን በቅርጾቹ ላይ ብቻ በመሆናቸው ነው።

4.3.3.4.ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም

በዚህ ወቅት የታተመው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ካካተታቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል በርካታዎቹን በዚህ የአቀራረብ ሥልት ያደራጃቸው መሆኑን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ መረዳት ተችሏል። ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን እናያለን።

- *(ገጽ 29) የሚከተሉትን ሀረጎች ስማዊ፣ ግሣዊ፣ መስተዋድዳዊና ገላጭ ሐረግ በማለት ለዩ።*

ምሳሌ፦

ሀ. ቀይ ዶሮ=ስማዊ ሀረግ

ለ. በጣም ጎበዝ= ቅጽላዊ ሀረግ

ሐ. ወደ ገቢያ= መስተዋድዳዊ ሀረግ

መ. ቀላል ነው= ግሣዊ ሀረግ

በዚህ መልኩ የቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በርካቶች ሲሆኑ ከገዘርገር ወደ አጠቃላይ ስልት ቀርበዋል ያልናቸው አብዛኛዎቹ ይዘቶች በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት የሚቻለው መማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት ያቀረበ መሆኑን ነው። ይህንንም ያልንበት ምክንያት መጽሐፉ ያካተታቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ገጽታ እንዴት፣ መቼና በምን መልኩ ተግባቦታዊ ተግባር ላይ እንደሚውሉ በሚያሳይ መልኩ ባለማቅረቡ ነው።

በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ የተቻለው በዚህ ወቅት የቀረበው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር የአቀራረብ ሥልት አደራጅቶ ከማቅረብ አንፃር በ1984 ዓ.ም የተጀመረውን አጠናክሮ የገፋበት መሆኑን ነው። ከዚህም በመነሳት መጽሐፉ የመዋቅራዊነት ባህሪ ጎልቶ ታይቶበታል።

የ9ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ በ1991 ዓ.ም የታተመ ሲሆን የ10ኛ ክፍሉ ግን አንድ አመት ያህል ዘግይቶ በ1992 ዓ.ም ሊታተም በቅቷል። ቀጥሎ ደግሞ ስልቱ በዚህ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ምን ገጽታ እንዳለው እንደሚከተለው ቀርቧል።

በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ሥልት በተለያዩ ገጾቹ ላይ አደራጅቶ አቅርቧል። ለማስረጃ ያህል፦

- *(ገጽ 184) ቀጥሎ የቀረቡትን ሥርወ ቃላትና ቅጥያዎች በማገጣጠም የተሟላ ፍቺ ያላቸውን ቃላት መሥርቱ።*

  ምሳሌ፦ -ኩ

  (ደረስ-)

  ኣ-

  ቃሉ= ኣደረስኩ

  በዚህ ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 6 ጥያቄዎች ቀርበዋል። በ(ገጽ 67፣135፣134፣184) ላይ መሰል አቀራረቦች ይገኛሉ።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች መማሪያ መጽሐፉ ውጤት ተኮር ሥልትን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ለማደራጀቱ ማስረጃዎች ናቸው። እነዚህን መሠል አቀራረቦች በመጽሐፉ በርካታ ገጾች ላይ ይገኛሉ።

በሁሉም ምሣሌዎች ውስጥ የቀረበው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት በቅርጽ ላይ ያተኮረ እንጂ ቅርጹን እንዴት ለተግባቦታዊ ተግባር ማዋል እንደሚቻል የሚያስረዳ ነገር አይታይበትም። ይህ በቅርጽ ላይ ትኩረት አድርጎ ይዘቶችን የማቅረቡ ተግባር ደግሞ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ሥልት እንደሚባል አስቀድመን መግለፃችን ይታወሳል።

በመሆኑም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የማቅረቡ ሂደት በዚህ ወቅት ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ተስፋፍቶ መቀጠሉን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር ሥልት ከማቅረብ አንፃር እንደ 1984ቶቹ መጻሕፍት ናቸው። በ1984 ዓ.ም ተጀምሮ የነበረው ይኸው ስልት በ1991/2 ውስጥም በስፋት ተተግብሮ ይገኛል። በመሆኑም መማሪያ መፃህፍቱ ከአይነት አንፃር በተለይም ሰዋስውን በተመለከተ "መዋቅራዊ" በሚለው ጎራ ልንመድባቸው እንችላለን።

4.3.3.5. ውጤት ተኮር አቀራረብ በ1997 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ በቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የአቀራረብ ስልቱ መተግበሩን የሚያረጋግጡ በርካታ ማስረጃዎች ይገኛሉ።

ነገር ግን አብዛኞቹ ይዘቶች ከ1991 መጽሐፍ እንዳለ የተወሰዱ በመሆናቸው በዚያው ክፍል ያየናቸውና በተሻሻለው መጽሐፍ ውስጥም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አካሄድን ተከትለዋል ብለን ያቀረብናቸው ናቸው።

ይሁን እንጂ መጽሐፉ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ሥልትን ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማቅረቡን ማሣያ የሚሆኑ ሌሎች ምሣሌዎችን ለማየት እንሞክራለን።

- *ገጽ 29 በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች (ጥገኛ ምዕላዶች) ለይታችሁ ካወጣችሁ በኋላ ቃል መሥራችና የእርባታ በማለት ለዩዋቸው።*

ምሳሌ፦ ቤትሽ

ቤት [-ሽ] የእርባታ ምዕላድ

ገደላማ

ገደል [-ኣማ] ቃል መስራች ምዕላድ

በቀረበው ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 6 ቃላት ቀርበዋል። በ(ገጽ 43 እና 138) ላይ መሰል አቀራረቦች ይገኛሉ።

እነዚህ ከላይ በማሳያነት የቀረቡት ምሳሌዎች መጽሐፉ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ያቀረበ መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ ይዘቶቹ በቅርጽ እንጂ በአገባብ ላይ ያላተኮሩ መሆናቸው ነው።

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልትን ባየንበት ክፍል በዚህ ወቅት ተሻሽለው በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ስልቱ መተግበር መጀመሩን ገልፀን ነበር። ይሁን እንጂ ስለ ሰዋስዋዊ ይዘቱ የቀረበው መግለጫና ማብራሪያ በአብዛኛው ያተኮረው በሰዋስዋዊ ይዘቱ ቅርጽ ላይ መሆኑን በዚህ ወቅት በተደረገው ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት የማቅረቡን ሁነት የተገበሩት መሆናቸውን መገንዘብ የተቻል ሲሆን፣ በ1984 ዓ.ም ተጀምሮ የነበረው ይህ የአቀራረብ ስልት በ1991/2 እንደ አዲስ በተዘጋጁት ውስጥም ሆነ በ1997 ተሻሽለው በቀረቡት ውስጥ እያደገና እየዳበር መቀጠሉ ተረግጧል።

በመጨረሻ ደረጃ በዚህ ንዑስ ክፍል ቀርቦ የምናገኘው፣ በመርሃ ትምህርቱ መለወጥ ምክንያት በ2004 ዓ.ም በአዲስ መልክ የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ማቅረብ አለማቅረባቸውን ይሆናል።

4.3.3.6. ውጤት ተኮር አቀራረብ በ2004 ዓ.ም

በ2004 ዓ.ም ታትሞ በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የአቀራረብ ስልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማቅረቡን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎችን በመጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ እናገኛለን።

- *(ገጽ 24) ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በነፃ ምዕላድና በጥገኛ ምዕላድ ለለያችሁ በኋላ በምሣሌው መሠረት ሠንጠረዡ ውስጥ አስፍሩ*

ምሳሌ፦

ተቁ	ቃል	ነፃ ምዕላድ	ጥገኛ ምዕላድ
1.	ቂመኛ	ቂም	-ኛ

በዚህ ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 8 ቃላት ቀርበዋል።

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት የሚቻለው መማሪያ መጽሐፉ በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ያቀረባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን ነው። እነዚህም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ዋነኛ ትኩረታቸው በቋንቋው ቅርጽ ወይም ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ ነው።

በመጀመሪያው ምሳሌ ላይ የምናስተውለው አንድን ቃል ወደ ነባና ጥገኛ ምዕላድ መሸንሸንን ነው። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውም በቃሉ ውስጥ የሚገኙትን ነባና ጥገኛ ምዕላዶች በመለየት በተሠጣቸው ምድብ ቦታ ላይ ማስፈር ነው። በእነዚህ ምሳሌዎች አማካኝነት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ተግባቦትን መሠረት ያላደረጉና በቅርጽ ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆናቸው የአቀራረብ ስልቱ ውጤት ተኮር ለመሆኑ ማስረጃችን ነው።

በመሆኑም በዚህ ወቅት የተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ሥልት አደራጅቶ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል።

በተመሳሳይ ወቅት የተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም ሥልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማቅረቡን ከሚከተሉት ምሣሌዎች መረዳት ተችሏል።

- *(ገጽ 139) ምሣሌውን በመከተል መልመጃውን ሥሩ።*

  ምሳሌ፦

ግስ	*ከግስ የተመሠረተ ስም መሰል ቃል*	*ከግስ የተመሠረተ ቅጽል*
ቀጠፈ	*መቅጠፍ*	*ቀጣፊ*
ሰነፈ	*መስነፍ*	*ሰነፍ*

በምሳሌው መሠረት የሚሠሩ 6 ቃላት ቀርበዋል።

ከላይ ያቀረብናቸው ምሣሌዎች የሚነግሩን በዚህ ወቅት ተዘጋጅቶ የቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የአቀራረብ ሥልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ያቀረበ መሆኑን ነው።

በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደገለጽነው ይህ አቀራረብ የሚያተኩረው በቅርጽ እንጂ በተግባቦት ላይ ያለመሆኑን ነበር። የቀረቡት ምሣሌዎችም የሚያረጋግጡልን ይህንኑ ሁነት ነው። በመሆኑም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት አደራጅቶ የማቅረቡ ሂደት ተስፋፍቶና ተጠናክሮ መቀጠሉን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ሥልት ተጠቅሞ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የማቅረቡ ሂደት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በሥፋት እየተተገበረ ይገኛል።

4.3.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ

ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎቹ በቋንቋው ይበልጥ እንዲገለገሉ፣ በአውድ ውስጥ ትርጉም ሠጪ የሃሣብ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማድረግ የቋንቋውን ቅርጾች በአግባቡ እንዲጠቀሟቸው የሚያስችል አቀራረብ መሆኑን በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ተመልክተናል። ስልቱ በቋንቋው ቅርጽ ላይ የሚያተኩር ሳይሆን ለተግባቦት ቅድሚያ የሚሠጥ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ በተጠቀሱት ዘመናት የተዘጋጁትን መማሪያ መፃህፍት ከዚህ የአቀራረብ ሥልት አንፃር ምን መልክ እንዳላቸው ቀጥሎ ይቀርባል።

4.3.4.1. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1968 ዓ.ም

የ1968ቱ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተከትሎ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ረገድ የበለፀገ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ይዘቶች የቀረቡት በዚህ የአቀራረብ ሥልት መሠረት ነውና። ከዚህ ቀጥለን ማሣያ የሚሆኑ ምሳሌዎች የሚገኙበትን ገጽ በተወሰነ መልኩ ለማየት እንሞክራለን።

- በሚከተሉት ቃላት ሀረጋት ሥራባቸው (መስርት) (ገጽ 25፣53፣116)፣
- በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገር ሥራባቸው (ገጽ 13፣25፣38፣53፣60፣68፣97፣121)፣
- አያያዥ ቃላት በመጠቀም የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች አያያዝ (ገጽ 53)፣
- በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠጡ ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃል ሙላ (ገጽ 59፣68፣97)፣

እነዚህ እና መሠል አቀራረቦች በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ ይገኛሉ።

ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በዚሁ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ መርህ መሠረት ከማቅረብ አንፃር እንደ 9ኛ ክፍሉ ሁሉ ጠንካራ አቀራረብ ታይቶበታል። ይህንንም በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ የቀረቡ ትዕዛዞችን መነሻ በማድረግ ለመቃኘት እንሞክራለን።

- በተሠጡ ቃላት ሀረጋትን መመስረት (ገጽ 33፣ 58፣ 89)፣
- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ማያያዝ (ገጽ 58)፣
- በተሠጡ ቃላት አረፍተ ነገር መመስረት (ገጽ 33፣ 39፣ 43፣ 58፣ 70፣ 79፣ 83፣ 103፣ 116፣ 121፣ 132)፣
- በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠጡ ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃል መሙላት (ገጽ 70፣ 115)፣
- በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላት በሌላ ቃል መተካት (ገጽ 63)፣እና
- አንድን አረፍተ ነገር በሌላ መልኩ እንደገና መጻፍ (ገጽ 99)

ላይ ተዘርዝረው የሚገኙ ሲሆኑ የመልመጃዎቹ ትዕዛዞች የሚነግሩን መጽሐፉ ይዘቶቹን ለማቅረብ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን የተከተለ መሆኑን ነው።

በድምሩ በዚህ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ረገድ፣ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተግብረዋል። በመጻሕፍቱ አቋም ክፍል እንዳየነውም ሆነ ከቀረቡት የመልመጃ ትዕዛዛት እንደምንረዳው፣ ሁሉም ይዘቶች የቀረቡት በዚህ ስልት ነው።

ይህ የአቀራረብ ስልት በቋንቋው አገባብና አጠቃቀም ላይ የሚያተኩር ሲሆን ቅርፃዊ ለሆኑ ጉዳዮች እንደማይጨነቅ ገልፀን ነበር። ከቀረቡት የመልመጃ ትዕዛዞች እና የይዘት አቀራረቦች የምረዳውም ይህንኑ ነው።

ይሁን እንጂ እነዚህኑ መፃህፍት ከውጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ አንፃር በገመገምንበት ወቅት ምንም አይነት ይዘት ያላካተቱ መሆናቸውን ገልፀን ነበር።

በዚያም ምክንያት ለቅርፃዊ ሰዋስው ተገቢውን ቦታ ባለመስጠታቸው ተችተናቸው ነበር። አሁንም ያረጋገጥነው ያንኑ ሃቅ ነው። ምክንያቱም ሁሉንም ይዘቶች በሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት ያቀረቡ ሆነው ተገኝተዋልና። ነገር ግን በክለሳ ድርሳናችን ክፍል ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የራሳቸው የሆነ ደካማ ጎን እንዳላቸውና የአንዱ ድክመት በሌላው ጥንካሬ ሊሞላ እንደሚችል በመጠቆም በመማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ወቅት ሁለቱንም የአቀራረብ ስልቶች አመጣጥኖ ማቅረብ ተገቢ እንደሆነ አንስተን ነበር።

ይሁን እንጂ በእነዚህ መፃህፍት ውስጥ ይህ ሁነት ተተግብሮ አልታየም። በመሆኑም መማሪያ መፃህፍቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በሂደት ተኮር ስልት ብቻ ማቅረባቸውና ውጤት ተኮር ስልትን ፈጽሞ መዘንጋታቸው እንደ ትልቅ ክፍተት ሊታይባቸው ችሏል።

4.3.4.2. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በርካታ ይዘቶችን ያቀረበው በዚህ የአቀራረብ መርህ መሠረት ነው።

- *ሁለት ቃላት አንድነት ሁነው እንደ አንድቃል እንደሚያገለግሉ ቀጥሎ ያሉት ከምንባቡ የወጡ ምሣሌዎችን ተመልክተህ ሌሎች የምታውቃቸውን አስር ቃላት ፃፍና አረፍተ ነገር ሥራባቸው (ገጽ 38)*

  ምሳሌ፡- አባለ-ዘር

- *በተሠጠህ ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት የሚያሳዩ አረፍተ ነገር ሠርተህ አሳይ (ገጽ 44) ።*
- *የሚከተሉትን አባባሎች አንድ በአንድ ወስደህ ፍቺያቸውን በሦስት ሦስት አረፍተ ነገሮች ለማሣየት ሞክር (ገጽ 57)*

እና መሰል መመሪያዎች መኖራቸው መማሪያ መጽሐፉ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ለማቅረቡ ማረጋገጫዎች ናቸው። በተመሣሳይ መልኩ፡-

- በተሠጡ ቃላት ሀረግ መመስረት (ገጽ 4)፣
- በተሠጡ ቃላት አረፍተ ነገር መመስረት (ገጽ 4፣ 23፣ 27፣ 33፣ 44፣ 60፣ 69፣ 73፣ 88፣ 94፣ 118)፣
- በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሠጡ ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃል መሙላት (ገጽ 11)፣ እና
- በጥምር ቃላት አረፍተ ነገር መመስረት (ገጽ 38)

በዚህ ሥልት መሠረት ተቃኝተው የቀረቡ ናቸው።

በ1972 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበው የ10ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍም ከዚህ የአቀራረብ መርህ አንፃር ከ9ኛ ክፍሉ የተለየ አይደለም። በዚህም መሠረት፡-

- በተሠጡ ቃላት አረፍተ ነገር መገንባት (ገጽ 2፣ 9፣ 12፣ 16፣ 24፣ 27፣ 33፣ 38፣ 43፣ 46፣ 56፣ 60፣ 69፣ 73፣ 81)፣
- የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን በአጣማሪ ማያያዝ(ገጽ 27፣ 27፣ 33)፣

- በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተሠመረበትን ቃል የሚተካ ሌላ ቃል መፈለግ (ገጽ 30)፣
- አንድን አረፍተ ነገር በሌላ መንገድ እንደገና ማዋቀር (ገጽ 58)፣እና
- በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ክፍት ቦታዎችን በተስማሚ ቃል መተካት (ገጽ 69) እና

የሚሉት ትዕዛዞች እና በዚህ መሠረት የሚተገበሩት መልመጃዎች የሚያስረዱት መጽሐፉ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን የተከተለ መሆኑን ነው።

ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በውጤት ተኮር አቀራረብ መርህ መሰረት መቅረብ አለመቅረባቸውን ባየንበት ክፍል ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ከፍተኛ ክፍተት ታይቶባቸው እንደነበር ገልፀን ነበር። በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከትነውም ያንኑ ሁነት ነው። ምክንያቱም በተጠቀሰው ዘመን አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት የተተኳሪዎቹ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ የቀረቡት በሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ነውና።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ሁሉንም ይዘቶች ሊባል በሚችል መልኩ ያቀረቡዋቸው በዚህ ስልት መሆናቸውን ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

4.3.4.3. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1984 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በውስጡ አካትቶ ከያዛቸው በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል ይህን ያቀራረብ ሥልት ተጠቅሞ ያቀረባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን ከሚከተሉት ማስረጃዎች መገንዘብ ተችሏል።

- *በሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ቅርፃቸውን ሳትለውጥ የባለቤት ገለጮች በማድረግ ዐ.ነገር ስራ። (ገጽ 24)*
- *የሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነገሩ የሚኖራቸውን የትርጉም ልዩነት በዐ.ነገር አስገብተህ አሳይ።(ገጽ 25 እና 73)*
- *በሚከተሉት ቃላት ፍቺያቸውን የሚያሳዩ አረፍተ ነገር ሥራ። (ገጽ 24፣32፣ 41፣ 54፣ 58 77 እና 83)*
- *ቀጥሎ የተሠጡትን ቃላት እንደ ሥም ገላጭ በመጠቀም ዐ.ነገር ሥራባቸው።(ገጽ 54)*
- *እነዚህን የግስ ገላጮች ሆነው እንዲሠሩ አድርገህ በአረፍተ ነገር አገባባቸውን አሳይ። (ገጽ 84)*

❖ *እነዚህን የስም ገላጮች አገባባቸውን በአረፍተ ነገር አሳይ።(ገጽ 84)*

ከላይ የዘረዘርናቸው ትዕዛዛት ሁሉም ምሳሌዎች አሏቸው። ምሳሌዎቹ የሚነግሩን ሰዋስዋዊ ቅርጹ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ገብቶ አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ወይም ለተግባቦት የሚበቃበትን አውዳዊ ሁነት ነው።

በመሆኑም ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ትዕዛዛት የሚነግሩን በዚህ ወቅት እንደ አዲስ ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ያቀረበ መሆኑን ነው

የቀረቡት ትዕዛዛትም ሆኑ በትዕዛዛቱ ሥር የቀረቡት ተግባራዊ ምሣሌዎች የሚነግሩን ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ሰዋስዋዊ ቅርጾች እንዲተነትኑ የሚያደርጉ ሳይሆን ይልቁንም ቅርጾቹን በተግባራዊ ግልጋሎት ላይ እንዲያውሏቸው፣ በማህበራዊ ተግባቦት ወቅትም እንዲጠቀሙባቸውና በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ልምምድ ለውጪም አለም እውናዊ የቋንቋ አጠቃቀም መሠረት እንዲሆናቸው የሚያደርግ የአቀራረብ ስልትን የተከተለ መሆኑን ነው።

በተመሳሳይ ጊዜ ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍም ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ያቀረበ መሆኑን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። ለዚህ ድምዳሜያቸው መሠረት ከሆኑን በርካታ ማስረጃዎች መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እናያለን።

❖ *የሚከለተው ምሳሌ የማሠሪያ አንቀጽን ገላጭ የሚያሳይ ነው።(ገጽ 5)*

ምሳሌ፦ ወፍራሙ ልጅ <u>በመኪና</u> መጣ። የተሠመረበት ቃል የማሠሪያ አንቀጽ ገላጭ ነው።

ምሳሌውን መሠረት በማድረግ የአረፍተ ነገር ማሠሪያ አንቀጽ ያላቸው አምስት አረፍተ ነገሮችን ፃፍ።

የመጀመሪያው ምሳሌ ሥለ ተውሳከ ግስ አገባብ የሚያወራ ነው። በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ቅርፃዊ ትንታኔና መግለጫ አልተሠጠበትም። ይዘቱ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ያለውን ቦታና ከተዋቃሪ አካላቱ ጋር ያለውን አውዳዊ ገምድና በምሳሌ የሚያስረዳ ነው። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውም ምሣሌውን መሠረት በማድረግ በቀረበላቸው ትዕዛዝ መሰረት የተሰጣቸውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ አገባብ ማሣየት ነው። ከዚህም በመነሳት አቀራረቡ ሂደት ተኮር መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በተመሳሳይ መልኩ፦

- *የሚከተሉት ቃላት ከአንድ የበለጠ ትርጉም የሚሠጡ መሆናቸውን በአረፍተ ነገር አሳይ።(ገጽ 9፣)*
- *ቀጥሎ ከተሠጡት ቃላት ብቻ መርጠህ ቅርፃቸውን እየለዋወጥህ ባለቤት፣ ተሣቢና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸው አምሥት አረፍተ ነገሮች ሥራ።(ገጽ 15)*
- *በምንባቡ ውስጥ "... እምቡር እምቡር፣ እንቅልፍ እንቅልፍ" የሚሉና ራሳቸውን የሚደግሙ ቃላት አይተናል። እንደዚህ ያሉ ሌሎች አምስት ቃላት መርጠህ አረፍተ ነገር ስራባቸው።(ገጽ 16)*
- *በተሠጡት ቃላት ዐ.ነገር ሥራባቸው። (ገጽ 36፣ 52 ና 88)*
- *ገጽ 47 በሚከተሉት ጥንድ ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት አረፍተ ነገር በመስራት ለይተህ አሳይ።(ገጽ 36፣ 52 ና 88)*

የሚሉ ትዕዛዛት እና በትዕዛዛቱ ሥር የቀረቡ ምሳሌዎች የሚነግሩን፣ በወቅቱ ቀርቦ የነበረው መማሪያ መጽሐፍ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ሥልትን ተጠቅሞ ይዘቶችን ያቀረበ መሆኑን ነው። ምክንያቱም ከላይ ያየናቸው ትዕዛዛት የሚነግሩን ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ቋንቋዊ ቅርጽ ላይ እንዲያተኩሩ ሳይሆን ሰዋስዋዊ ቅርጾቹን እንዴት በአረፍተ ነገር ውስጥ እንደሚጠቀሙባቸውና በተግባቦት ሂደትም እንደሚገለገሉባቸው ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን ተከትለው የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በተለያዩ ገጾቻቸው ላይ ማቅረባቸውን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። ከቀረቡት መረጃዎች በመነሳት በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩትን የመማሪያ መፃህፍት ከቀድሞዎቹ የ1968 እና የ1972/3 ጋር በማነፃፀር ስለታየው ለውጥ የሚከተለውን ማለት ይቻላል።

የቀድሞዎቹ መማሪያ መፃህፍት አብይ ትኩረታቸው አገባባብና ፍቺ እንጂ ቅርፃዊ ሰዋስው አልነበረም። መፃህፍቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ መርህ መሠረት አቅርበዋል ስንልም በዋናነት የትኩትረ አቅጣጫቸው በተሠጡ ቃላትና ሀረጋት አረፍተ ነገር መመስረትን እና ሥነ ፍችን ታሳቢ ያደረገ ነበር።

አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው ደግሞ በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ከፍተኛ ሊባል በሚችል መልኩ ቅርፃዊ ሰዋስውን አካትተው ነበር። ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን በ1984 ዓ.ም ቀርበው በነበሩት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተመለከትነውም ከአገባብና ፍቺ በተጨማሪ በቀረቡት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችም ላይ ነው። በመሆኑም በዚህ ወቅት በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ከቋንቋው

ሥነ ፍቺና አገባብ በተጨማሪ በቋንቋው ቅርፃዊ ሰዋስው ላይም የተንፀባረቀበት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል።

4.3.4.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም

በዚህ ወቅት እንደ አዲስ ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት ማቅረቡን ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ውጤት ማረጋገጥ ችለናል።

- *ክፍ ሲል በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ ባሰፈራችኋቸው ቃሎች ከ10-15 የሚደርሱ የተለያዩ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መሥርቱ። (ገጽ 29)*

የቀረበው ሠንጠረዥ ስለ ውልድ ግሶችና ቅጽሎች የሚያወራ ነው ።

ምሳሌ፦

ሀ. ጠረጴዛው ላይ የተደረደሩት ብርጭቆዎች ተሰባበሩ።

ለ. የጠርሙሱን ስባሪ ወረወረው።

ሐ. ወንድሜ ለማገዶ የሚሆን እንጨት አሳበረች።

መ. በሰባራ ብርጭቆ ሻይ አትጠጡ።

ከላይ ከቀረቡት ምሣሌዎች ጋር ተመሳሳይ የአቀራረብ ስልት ያላቸው መልመጃዎች በተለያዩ የመማሪያ መጽሐፉ ገጾች ላይ ይገኛሉ።

- ሀረጋቱና አረፍተ ነገራቱ የያዙትን ሃሣብ በራሳችሁ አገላለጽ እንደገና ዓፉ (ገጽ 72)፣
- ሀረጋቱንና አረፍተ ነገራቱን እንደገና አዋቅራችሁ ዓፉ (ገጽ 89)፣
- ተራ አረፍተ ነገሮችን ወደ ውስብስብ ቀይሩ (ገጽ 24)፣
- በተሠጡ ቃላትና ሀረጋት አረፍተ ነገር መስርቱ (ገጽ 4፣ 14፣ 15፣ 25፣ 26፣ 41፣ 49 51፣ 58 71 72፣ 79፣ 85 ፣91፣ 96፣ 106፣ 108፣ 109፣ 111).

የሚሉት ሊጠቀሱ የሚችሉ ይዘቶች ናቸው።

በመሆኑም እነዚህ ከላይ ያቀረብናቸው ምሳሌዎች የሚነግሩን በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው መማሪያ መጽሐፍ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማቅረቡን ነው። ምክንያቱም ከመጀመሪያው ምሳሌ መረዳት እንደሚቻለው በሠንጠረዡ ውስጥ የቀረበው፤ ውልድ ግሶች፣ ቅጽሎችና አርዕስታዊ ሥሞች እንዴት እንደሚመሠረቱ ነው። ይህ

የምስረታ ሥርዓት ግን በዚህ ብቻ አላበቃም። ምስርቶቹን ቃላት በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ቀርበው እናገኛለን። ቀጥሎም ተማሪዎቹ እነዚህን ውልድ ግሶች፣ ቅጽሎችና አርዕስታዊ ስሞች በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ እያስገቡ እንዲጠቀሙባቸው ያዝዛል። ይህ ማለት ደግሞ መዋቅራዊ የቋንቋ ቅርጾችን አገባብና አጠቃቀም የሚያሳይ፣ ለተግባቦት የሚያበቃ፣ የቃላቱን ግልጋሎታዊ ገጽታ የሚያንፀባርቅ የአቀራረብ ስልት ተከትሎ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት ያቀረቧቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው። ቀሪዎቹም ምሣሌዎችና ይዘቶች በዚሁ ሥልት የቀረቡ ናቸው።

በተመሳሳይ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም በተመሳሳይ የአቀራረብ ስልት ያቀረቧቸው በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ የተለያዩ ገጾች ላይ ይገኛሉ። ቀጥለን ጥቂቶቹን ለማስረጃ ያህል እናቀርባለን።

- *የሚከተሉትን ስሞች በባለቤትና በተሣቢ ቦታ ላይ በማስቀመጥ የተለያዩ ዐ.ነገሮችን መስርቱ።(ገጽ 21.)*

ምሳሌ፡ በሬ

ባለቤት- በሬው ገደል ገባ።

ተሳቢ= ገበሬው በሬውን ሸጠ።

በዚህ ምሳሌ መሰረት የሚሠሩ 10 ሥሞች ቀርበዋል።

እና መሠል ይዘቶች ከላይ ምሳሌዎቹ በቀረቡበት ሥልት የተዋቀሩ ናቸው።

በምሳሌ አንድ ውስጥ የምንመለከተው "ስም" በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የባለቤትና የተሳቢነት ሙያ ያለው መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ ጉዳዩ የቀረበው በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጠ ገብቶ ነው። ሰዋስዋዊ ቅርጾች ለተግባቦታ ተግባር እንደሔትና በምን መልኩ እንደሚውሉ ለማስረዳት በተጨባጭ ምሣሌ ይዘቱን በአውድ አስገብቶ የማቅረቡ ስትል ደግሞ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት መሆኑን አስቀድመን ገልፀናል።

በአጠቃላይ በ1991/2 ዓ.ም ቀርበው የነበሩት የ9ኛ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአቀራረብ ስልቱ ተተግብሮ እናገኘዋለን።

ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልትን በቃኘንበት ክፍል በ1984 ዓ.ም በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመበራከታቸውና የአቀራረብ ስልታቸውም በቅርጽ ላይ

ያተኩር ስለነበረ መፃህፍቱን የመዋቅራዊነት ባህሪ ታይቶባቸዋል ብለን ነበር። በዚህኛው ክፍል ደግሞ መፃህፍቱ ሂደት ተኮር አቀራረብንም ተግባራዊ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ችለናል።

ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መፃህፍት ከሁለቱ አቀራረቦች ወደ ውጤት ተኮር ያመዘኑ በመሆናቸው አሁንም ከዚያ ባህሪያቸው ተላቅቀዋል ማለት አያስደፍርም። ነገር ግን በ1984 ዓም ቀርበው ከነበሩት አንፃር በተሻለ ደረጃ ሂደት ተኮር አቀራረብን ተግብረዋል ማለት ተችሏል።

4.3.4.5. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ1997 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዚህ የአቀራረብ ስልት መሠረት፣ አደራጅቶ ያቀረባቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

- *የሚከተሉትን ምዕላዶች በተገቢ ቦታቸው እያስገባችሁ የአረፍተ ነገሮቹን ሠንጠ አሟሉ።(ገጽ 12)*

  በዚህ ትዕዛዝ ስር 15 ምዕላዶች የቀረቡ ሲሆኑ ምዕላዶቹ የሚገቡባቸው 10 ያህል አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል።

በዚህ መልኩ የቀረቡ የተለያዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች (በገጽ 13፣ 21፣ 30፣ 31፣ 38፣ 44፣ 58፣ 77፣78. 79 92 110 እና 115) ላይ ይገኛሉ።

ከላይ ከቀረቡት ምሣሌዎች መረዳት የሚቻለው መማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ መርህ አዋቅሮ ማቅረቡን ነው። ምክንያቱም ምሣሌው የሚያስረዳን የምዕላዶችን አገባብ ነው። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውም ምሣሌውን ሞዴል በማድረግ የቀረበላቸውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ በአረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ከቅርጽ ባሻገር ያለውን የአገባብ ሥርዓት መረዳት ነው።

በተመሳሳይ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍም ስልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር በበርካታ ገጾቹ ላይ መተግበሩን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

ለማስረጃ ያህል የተወሰኑትን ብቻ ለማየት እንሞክራለን።

- *ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃሎች ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሠጡትን የተለያየ ፍቺ የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች መሥርቱ።(ገጽ 111)*

  ምሳሌ፡ ሀ. ከጥቂት ጊዜ በኋላ የደፈረሠው ውሃ ይጠራል።

  ለ. ነጋዴው ግብር እንዲከፍል በሬዲዮ ይጠራል።

  በዚህ ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 6 ቃላትን ቀርበዋል።

ከላይ በቀረቡት ምሣሌዎች ስልት የቀረቡ የተለያዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች (በገጽ 19፣20፣ 26፣ 28፣ 39፣ 53፣ 54፣ 55፣ 62፣ 80፣ 89፣ 90፣ 93፣ 102፣ 111፣115፣116፣ 130 እና 158) ላይ ይገኛሉ።

ማለያ አድርገን ያቀረብናቸው ምሳሌዎች የሚነግሩን በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከቅርጽ አንጻር ብቻ ሳይሆን አገባባቸውም ጭምር ምን እንደሚመስል በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ እያስገባ ያቀረበ መሆኑን ነው። ከዚህ የምንረዳው ደግሞ መማሪያ መጽሐፉ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያቀረበ መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት በሰዋስው ትምህርት ረገድ ብዙዎቹ ይዘቶች ከ1991/2 እንዳሉ የተቀዱ ሲሆኑ እንደ አዲስ ከተካተቱትም ይዘቶች መካከል በዚህ የአቀራረብ ስልት የቀረቡ መኖራቸውን በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

የአቀራረብ ስልቱ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ ቀጣይነት ባለው መልኩ እየተተገበረ ያለ መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ቢሆንም፣ በዚህ ወቅት የቀረቡት መፃህፍት በ1991/2 ቀርበው ከነበሩት ጋር ሲነፃፀሩ ሥልቱን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የጎላ ልዩነት አልታየባቸውም።

4.3.4.6. ሂደት ተኮር አቀራረብ በ2004 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ለየት ባለ መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከያዛቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች መካከል በዚህ የአቀራረብ መርህ ያቀረባቸው መኖራቸውን ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። ቀጥለን የተወሰኑትን ለማሳያ ያህል እናቀርባለን።

❖ *በሚከተሉት ቃላት ባለቤትነትን፣ ተሣቢነትን፣ አገናዘቢነትን (ባለንብረትነትን) እንዲያመለክቱ በማድረግ አረፍተ ነገር ሰሩባቸው።(ገጽ 156)*

ምሳሌ፦ ሀ. የተሠበረው <u>ቀንድዋ</u> ነው። (ባለንብረትነትን)

ለ. <u>ቀንድ</u> ለጫማ መስሪያነት ያገልግላል። (ባለቤትነትን)

ሐ. ገበያ ወጥቼ <u>ቀንድ</u> ገዛሁ። (ተሣቢነትን)

በቀረበው ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ 6 ስሞች ቀርበዋል።

በዚህ ስልት የቀረቡ በርካታ ይዘቶች በመጽሐፉ (ገጽ 7፣ 26፣ 39፣ 65፣ 68፣ 69፣ 72፣ 86፣ 105፣ 106፣ 109፣125፣ 128፣ 129፣ 137፣ 155፣ 171፣ 172፣ 175) ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ ከላይ በማሳያነት ያቀረብናቸው ምሳሌዎችና ትዕዛዞች የሚነግሩን መማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹን ቅርፃዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አውዳዊ የአገባብ ስርዓታቸውን ጭምር የሚያሳዩ የአቀራረብ ስልትን የተከተለ መሆኑን ነው። ቀደም ብለን በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው ደግሞ ይህ በአገባብ ወይም በአጠቃቀም ላይ ያተኮረ የአቀራረብ መርህ ሂደት ተኮር ይባላል።

ከዚህም በመነሳት በዚህ ወቅት ቀርቦ በነበረው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የአቀራረብ ስልቱን ተግብሮታል ማለት ይቻላል። ሁኔታው የሚነግረንም በዚህ የአቀራረብ መርህ መሠረት ይዘቶችን የማቅረቡ ስልት በሥፋት እየተሠራበት መሆኑን ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ወቅት ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ይህንኑ የአቀራረብ መርህ ተከትለው የቀረቡ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ ይገኛሉ።

ለምሳሌ፦

❖ *ለሚከተሉት በ "ሀ" ውስጥ እማሬያዊ ፍቺያቸውን በ "ለ" ደግሞ ፍካሬያዊ ፍቺያቸውን የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች ፃፉ። (ገጽ 127)*

ምሳሌ፦ ጨለሌ

ሀ. ጣሪያው ላይ ያረፈውን ጨለሌ በድንጋይ አባረርኩት። (እማሬያዊ ፍቺው። የወፍ ዘር)

ለ. ደላላው ጨለሌ ነው። (ፍካሬያዊ ፍቺ= ብልጥ ነው)

እነዚህን ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎችና ትዕዛዛት የሚመስሉ፣ በመጽሐፉ የተለያዩ ክፍሎች (በገጽ 7፣ 27፣ 31፣ 62፣ 63፣ 73፣ 86፣ 91፣ 96፣ 97፣127፣ 138፣ 134፣ እና 124) ላይ ቀርበው ይገኛሉ።

ከዚህ የምንረዳው ደግሞ መማሪያ መፅሐፉ በሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ማቅረቡን ነው። ይህንንም እንድንል ያስቻለን የቀረቡት ምሳሌዎችና ትዕዛዛት በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ስለአቀራረብ ስልቱ ባቀረብነው ገለፃ መሠረት የቀረቡ በመሆናቸው ነው።

በመሆኑም በዚህ ወቅት በቀረቡት የ9ኛና 10ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቡ ሂደት ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

4.3.5. ጥምረታዊ አቀራረብ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት የ9ኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ

ይህ ንዑስ ክፍል ጥምረታዊ አቀራረብ የሚቀርብበት ነው። ይህ የአቀራረብ ስልት በቋንቋ መዋቅራዊ ቅርጽና ተግባቦት መካከል ያለውን ክፍተት መሙላት የሚያስችል መሆኑንና ተማሪዎቹም በውጤት ተኮር አቀራረብ መርህ መሠረት የሚማሩትን የቋንቋ ቅርጽ የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ ተግባራዊ ልምምዶችን እያደረጉ ቅርጹን በአገልግሎት ላይ እንዲያውሉት ማድረግን መሠረት ያደረገ የአቀራረብ ስልት መሆኑን በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ገልፀን ነበር። የአቀራረቡም ዋንኛ ዓላማ ተማሪዎቹ ጥንቃቄና ቁጥጥር ከተሞላበት የቋንቋ ቅርፃዊ ወይም መዋቅራዊ ትምህርት ወደ ውጤታማና ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም የሚያርጉትን እድገትና ሽግግር ማገዝ ነው።

በመሆኑም በዚህ ክፍል ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ቀርበው በነበሩትና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአቀራረብ ስልቱ ምን ገጽታ እንደ ነበረውና እንዳለው ወይም ሰዋስዋዊ የትምህረት ይዘቶችን በዚህ መርህ መሠረት ከማቅረብ አንፃር መማሪያ መፃህፍቱ ምን ለውጥና መሻሻል እንደታየባቸው ለማየት ጥረት ተደርጓል።

4.3.5.1. ጥምረታዊ አቀራረብ በ1968 ዓ.ም

በ1968 ዓ.ም ቀርቦ በነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቅርፃዊ ለዋስው አለ ለማለት እንደማያስደፍር ባለፈው ክፍል ገልፀን ነበር። በዚህ ረገድ ልንጠቅሰው የምንችለው (ገጽ 101) ላይ "ድርብ ቃላት ሁለት ቃላት በንዑስ ጭረት ተገናኝው የሚፈጥሩት አንድ ቃል መሆኑን በመግለጽ ተማሪዎቹ "- ሰብ" በሚለው ቃል ሊያልቁ የሚችሉ ቃላትን በሙሉ ጽፈው ምን ማለት እንደሆነ ትርጉማቸውን እንዲገልጹ የሚያገዘውን ብቻ ነው።

ይህም ቢሆን ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው ከቀረበላቸው መድረሻ ተጣማሪ ጋር በመቀናጀት ድርብ ቃል መመስረት የሚችል ሌላ ቃል መፈለግና ከተሠጣቸው ቃል ጋር በማጣመር የሚፈጠረውን ምስርት ቃል ፍቺ መግለጽ እንጂ የተመሠረተውን ድርብ ቃል በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ በተለያዩ አገባባዊ አውድ እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ባለመሆኑ መጽሐፉ የአቀራረብ ስልቱን ተግብሮታል ለማለት አያስደፍርም።

በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ወቅት ታትሞ የነበረው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም በዚህ የአቀራረብ መርህ መሠረት ያቀረበው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት የለም። በቀደሙት ክፍሎች ለመግለጽ እንደሞከርነው በ(ገጽ 133)ላይ "ቅንጫቢ ብሎ ቅንጭብጫቢ የሚል አነጋገር አለ። በዚህ አይነት የሚመሠረቱ አስር ያህል ቃላት ጽፈህ አቅርብና በመጀመሪያዎቹና በተመስራቾቹ መካከል ያለውን የሃሣብ ልዩነት ተናገር።" የሚለውን ይዘት አንስተነው ነበር።

ይሁን እንጂ አቀራረቡ ምስርቶቹም ሆኑ ዋናዎቹ ቃላት በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ገብተው ለተግባቦት በሚውሉበት መልኩ ሳይሆን "የፍቺያቸውን ልዩነት ብቻ ተናገሩ" የሚል በመሆኑ መጽሐፉ ስልቱን ተግብሮታል ለማለት አያስችለንም። በመሆኑም በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት የመጀመሪያዎቹ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የአቀራረብ ስልቱን ከመተግበር አንፃር ከፍተኛ ክፍተት ታይቶባቸዋል። ምናልባት መፃህፍቱ መጀመሪያውኑ ቅርፃዊ ሰዋስውን ያላካተቱ በመሆናቸው ስልቱን የመተግበር ግዴታ አለባቸው ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ነገር ግን ከላይ ያቀረብነው መደምደሚያ መሠረት ያደረገው መፃህፍቱ አካትተዋቸዋል የተባሉትን አንድ አንድ ይዘቶች እንኳን በዚህ ስልት ያላቀረቡ መሆናቸውን በማየት ነው።

4.3.5.2. ጥምረታዊ አቀራረብ በ1972/3 ዓ.ም

በ1973 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ቃላት ምስረታ (ገጽ 39) እና ስለስም ገላጭ (ገጽ 45) ያቀረባቸው ሁለት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ይገኛሉ። ይሁን እንጂ የሁለቱም ይዘቶች የአቀራረብ ስልት ይህንን የአቀራረብ መርህ የተከተለ አይደለም። ምክንያቱም የቃላት ምስረታው፣ ከአንድ ግስ የሚመሠረቱ 4 የተለያዩ ቃላትን ከዘረዘረ በኃላ በምሳሌው መሠረት የሚተገበሩ ግሶችን አቅርቧል። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውም በቀረበላቸው ምሣሌ መሠረት ከተሠጡ ግሶች አራት አራት ምስርት ቃላትን ማውጣት ነው።

በተመሳሳይ መልኩ ሥለ ሥም ገላጭ የቀረበውም ሁለተኛው ይዘት "... በዝረዘር የቀረቡ ስሞችን ሊገልጹ የሚችሉ ገላጮችን በሙሉ ስጥ" የሚልነው። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውም የተዘረዘሩትን ስሞች ሊገልጹ የሚችሉ ገላጭ ቃላትን መፈለግ ነው።

በመሆኑም የመማሪያ መጽሐፉ ቅርፃዊ ሰዋስውን በተገቢው መጠን ካለመያዙም ባሻገር የያዛቸውንም ቢሆን በዚህ ስልት መሠረት አላቀረባቸውም። ምክንያቱም የቀረቡት ሁለቱም ይዘቶች በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ገብተው ትርጉም ሠጪ የሆነ ተግባቦታዊ ተግባር ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ እንዴት እንደሚዋቀሩ የሚሳይ አቀራረብ አልታየበትምና።

በተመሳሳይ መልኩ በ1972ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍም በዚህ የአቀራረብ መርህ ረገድ የታየበት አዲስ ነገር የለም።

በመሆኑም በ1968ዓ.ም ሆነ በ1972/3 ዓ.ም ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የማቅረቡ ጉዳይ ክፍተት ታይቶበታል።

በአጠቃላይ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ቅርፃዊ ሰዋስውን በተገቢው መጠን ካለመያዛቸው በተጨማሪ የያዟቸውንም ጥቂት ሰዋስዋዊ የትምህረት ይዘቶች በዚህ ስልት መሠረት ያለማቅረባቸውን በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ችለናል።

4.3.5.3. ጥምረታዊ አቀራረብ በ1984 ዓ.ም

በዚህ ወቅት የታተመዉ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከቀድሞዎቹ ጋር ሲነፃፀር በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህረት ይዘቶች የተካተቱበት መሆኑን ደጋግመን ገለፀነዋል። መጽሐፍ በውስጡ ካካተታቸውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት መካከል በውጤት ተኮርም ሆነ በሒደት ተኮር የአቀራረብ መርህ ያቀረባቸው መኖራቸውንም ጭምር በቦታው ተመልክተናል። የጥምረታዊ አቀራረብ መርህ መሠረታዊ አላማ ደግሞ በሁለቱ አቀራረቦች መካከል ያለውን ክፍተት መመላት ነው።

በዚህም መሠረት በወቅቱ ቀርቦ በነበረው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ መርህ መሠረት መቅረብ አለመቅረባቸውን ለማወቅ ባደረግነው አሰሳ ያረጋገጥነው፤ የተወሰኑት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በውጤት ተኮር ስልት ብቻ ሲቀርቡ ቀሪዎቹ ደግሞ በሂደት ተኮር ሥልት ብቻ መቅረባቸውን ነው። በመሆኑም በሁለቱ አቀራረቦች መካከል ያለውን ክፍተት ሊሸፍን በሚችል መልኩ የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አላገኘንም። ይህም ማለት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹ ቅርጽን ወይም አገባብን በተናጠል በማሳይት ላይ ያተኮሩ እንጂ የቋንቋው መዋቅራዊ ቅርጽ፣ አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ወይም ቅርጽንና ተግባቦትን ባጣመረ መልኩ የቀረቡ አልነበሩም።

በዚህ ወቅት ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ይህንን ያቀራረብ ሥልት መሠረት በማድረግ የቀረበ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አልተገኘም። በመሆኑም ከዚህ መርህ አንፃር በሁለቱ መፃህፍት መካከለ የታየ ልዩነት የለም።

በመሆኑም ይህ የአቀራረብ ሥልት፣ በዚህ ወቅት ተዘጋጅተው በቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ባለመተግበሩ በ1968 እና በ1972/3 ቀርበው በነበሩት መፃህፍት ውስጥ የነበረው ክፍተት እስከ 1991/92 ድረስ የቀጠለ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

ይሁን እንጂ በ1984 በቀረቡትና ከ1984 በፊት ቀርበው በነበሩት መካከል የሚታየው ልዩነት፤ በ1984ቱ ውስጥ በርካታ ሰዋስዋዊ ቅርጾች የሚገኙ ሲሆኑ ከ1984ቱ በፊት ባሉት ውስጥ ያለመገኘታቸው ነው።

ይህም ሁኔት በ1984 ዓ.ም የቀረቡትን መፃህፍት የበለጠ ደካማ ሊያለኛቸው ችሏል። ምክንያቱም በርካታ ሰዋስዋዊ ቅርጾችን ያቀፉ ቢሆኑም የአቀራረብ ስልቱን አልተገበሩምና ነው።

4.3.5.4. ጥምረታዊ አቀራረብ በ1991/2 ዓ.ም

በዚህ ወቅት ቀርቦ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይህንን የአቀራረብ ሥልት በመጠኑም ቢሆን የተገበረው ይመስላል። ለዚህ አባባላችን ማስረጃ የሚሆኑን በ(ገጽ 29 እና 57) ላይ የሚገኙት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ናቸው።

(ገጽ 29) ጥያቄ ቁጥር 1. "የመጀመሪያውን ምሣሌ መሠረት በማድረግ ባዶ ቦታዎቹን በተስማሚ ቃላት ሙሉ።" ከሚለው ትዕዛዝ ቀጥሎ የሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

1	ሰበረ	ሰባበረ	ተሰባበረ	አሳበረ	ሰበራ	ሰባራ	ስባሪ	መሰበር

በዚህ መሠረት ከቀረቡት ግሶች፣ ውልድ ግሶችን፣ ቅጽሎቸንና ስሞችን እንዲመሠርቱ 14 ያህል ቃላትን አቅርቧል። ይህ የሚያመለክተው ምስረታን ነው። ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው ግሶች የተለያዩ ውልድ ቃላትን የሚመሠርቱት በቀረበላቸው ምሣሌ መሠረት በቃላቱ ቅርጽ ላይ በማተኮር ነው።

ይሁን እንጂ መማሪያ መጽሐፉ ይህንን ብቻ አቅርቦ ዘወር አላለም። "በአንዳንዶቹ ሳጥኖች ውስጥ የሚቀመጥ ቃል ላይኖር እንደሚችል" ከገለፀ በኃላ በጥያቄ 2 ስር "ከፍ ሲል በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ ባሰፈራችኋቸው ቃሎች ከ10-15 የሚደርሱ የተለያዩ አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መስርቱ" የሚል ትዕዛዝ በማቅረብ ተማሪዎቹ እንዴት አድርገው በምስርቶቹ ቃላት አረፍተ ነገር መገንባት እንደሚገባቸው የሚከተለውን ምሳሌ አቅርቧል።

ምሣሌ፦ ሀ. ጠረጴዛው ላይ የተደረደሩት ብርጭቆዎች <u>ተሰባበሩ</u>።

ለ. የጠርሙሱን <u>ስባሪ</u> ወረወረው።

ሐ. ወንድሜ ለማገዶ የሚሆን እንጨት <u>አሳበረኝ</u> ።

መ. <u>በሰባራ</u> ብርጭቆ ሻይ አትጠጡ።

እነዚህ ምሳሌዎች የሚነግሩን የተመሠረቱት ውልድ ግሶችና ቅጽሎች በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ገብተው ለተግባራዊ ግልጋሎት እንዴት ሊውሉ እንደቻሉ ነው።

በመሆኑም ከላይ የቀረበው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቀርቦ የምናየው ጥምረታዊ በሚለው የአቀራረብ መርህ እሳቤ መሠረት ነው። ምክንያቱም፦ የመጀመሪያው ጥያቄ በቋንቋው ቅርጽ ላይ ያተኮረ ሲሆን ሁለተኛው ግን በአገባብ ላይ ያነጣጠረ ነውና ነው። ይህም ማለት ከቀረበው ምሣሌ የምንረዳው በመጀመሪያ ደረጃ የቃላትን የምስረታ ስርዓት ሂደት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በምስረታ ሂደቱ የተገኙትን የምስርት ቃላቱን አውዳዊ አገባብ ወይም በተግባራዊ ግልጋሎት ወቅት እንዴት ለተግባቦት ማዋል እንደሚቻል ነው። ይሁንና የመጀመሪያው በቃላቱ ቅርጽ ላይ፣ ቀጥሎ ያለው ደግሞ በአገባብ ላይ በተናጠል ቀርበው ቢሆን ኖሮ በውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ሥልት ቀርበዋል እንላቸው ነበር። አቀራረባቸው ግን እንደዚያ አይደለም። ይልቁንም የቋንቋውን ቅርጽ የበለጠ ተጨባጭ በማድረግ ሰዋስዋዊ ቅርጹ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግን መሠረት ያደረገ የአቀራረብ ስልትን የተከተለ ነው። ይህ ደግሞ ጥምረታዊ አቀራረብ ያልነው ነው። በ(ገጽ 57) ላይም በተመሳሳይ ስልት የቀረበ ይዘት ይገኛል።

በመሆኑም በዚህ ወቅት አገልግሎት ላይ ውሎ የነበረው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ረገድ ፍንጭ ታይቶበታል። ከዚህም በመነሳት ስልቱ በተተካሪዎቹ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ መተግበር የጀመረው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነበር ማለት ይቻላል።

በ1992 ዓ.ም ቀርቦ በነበረው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥም የአቀራረብ ስልቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ተተግብሮ እናገኘዋለን።

(ገጽ 31) ጥያቄ ቁጥር 3፣ ስር እንዲህ የሚል ትዕዛዝ እናገኛለን።

"ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ቃላት የሚስማሙ መስራች ምዕላዶችን እየመረጣችሁ ከቃላቱ በስተመድረሻ በማከል የተለያዩ ቃላትን መስርቱ።"

ካለ በኋላ ቃላቱንና መስራች ምዕላዶቹን በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል።

-አሽ	- ነት	-ኢያ	-ኣት	-ኛና	
-ኣማ	- ኣዊ	-ኣም	-እና		
ሀ. መጥረግ	መ. ሞኝ	ሰ. ወጣት	በ. ቅብብል	ኀ. ሕዝብ	ኣ. ድብብቅ
ለ. ልም	ሠ. ልብ	ሸ. ጥብቅ	ተ. መክተፍ	ነ. አመል	ከ. ድንጋይ
ሐ. ድርቅ	ረ. ሰማይ	ቀ. ሜዳ	ቸ. ቀንድ	ኘ. ግብ	ኸ. ነገር

ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው የቀረቡን መስራች ምዕላዶች ከተሠጧቸው ቃላት ጋር በማቀናጀት ቃላት መመስረት ነው።

ይሁን እንጂ መማሪያ መጽሐፉ በዚህ ብቻ አላበቃም። ወረድ ይልና በጥያቄ አራት ሥር የሚከተለውን መመሪያ አስፍሮ እናገኘዋለን።

"በጥያቄ ሦስት ስር ከመሠረታችኋቸው ቃላት መካከል በአምስቱ የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን ስሩ።" በማለት ምስርቶቹን ቃላት በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ አስገብተው እንዲገለገሉባቸው ያዛል። ከዚህ የምንረዳው በጥያቄ 3 ላይ የቀረበው መልመጃ በቅርጽ ላይ ያተኮረ ሲሆን በጥያቄ 4 ስር የቀረበው ደግሞ ያው ቅርጽ በተግባራዊ ተግባቦት ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ገጽታ የሚያሳይ ነው። ይህንንም ሁነት ለተማሪዎቹ በሚከተለው ምሳሌ አቅርቦላቸዋል።

ምሳሌ፦ ታሪክ -ኣዊ= ታሪካዊ

ታሪክ= የሐገራችንን ታሪክ የሚገልጹ መፃህፍት ታተሙ።

ታሪካዊ= ቱሪስቶቹ ታሪካዊ ቦታዎችን በመጎብኘት ላይ ናቸው።

ከዚህ በኋላ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው ምሳሌውን መሠረት በማድረግ ቀሪዎቹን መልመጃዎች መስራት ነው። ይህንን በማድረግ ሂደት ውስጥ ግን ሁለት ነገሮች ይጠብቋቸዋል። የመጀመሪያው ነፃና ጥገኛ ምዕላዶቹን በማገናኘት ዉልድ ቃል መመስረት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመሠረቷቸው ውልድ ቃላት ዓረፍተ ነገር መሥራት ነው። ይህ ሁነት የሚነግረን ደግሞ የመጀመሪያው መልመጃ ውጤት ተኮር አቀራረብን መሠረት ያደረገ ሲሆን ሁለተኛው ግን ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን መሠረት ያደረገ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ የቀረቡት ለየብቻቸው አይደለም። ይልቁንም ተከታትለውና አንድን ሰዋስዋዊ ይዘት መሠረት አድርገው ነው። ይህ አይነቱ የአቀራረብ ስልት ደግሞ በክለሳ ድርሳኑ ክፍላችን ለመግለጽ እንደሞከርነው ጥምረታዊ አቀራረብ ይሰኛል።

በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ከላይ በምሳሌነት ያቀረብነው አይነት የአቀራረብ ስልት ያላቸው ሰዋስዋዊ ይዘት ይገኛሉ።

ለምሳሌ፦

- *ከግስ ስም መመስረትና በምስርቱ ስም አረፍተ ነገር መስራት፤(ገጽ 48)*

- *የቀረቡትን ጥምር ቃላት ስም ወይም ቅጽል ብሎ መለየትና ቅጽል የተባሉትን ቃላት በአረፍተ ነገር መዋቅር ማስገባት፣(ገጽ 115)*
- *እንደ "ወጣ ገባ" እና "ደፋ ቀና" አይነት ቅርጽ ያላቸውን ቃላት መመስረትና በመሠረታቸውም ቃላት አረፍተ ነገር መገንባት፣ (ገጽ 135)*
- *እንደ "እምቢታ፣ እይታና እሩምታ" ከሚሉ ቃላት ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን ቃላት መመስረትና በመሠረታቸው ቃላት አረፍተ ነገር መስራት፣ (ገጽ 76)እና*
- *ግሶችን ወደ ስም በመለወጥ፣ በተመሠቱት ስሞች ሀረግ መመስረት(ገጽ 85) የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው።*

ከዚህም በመነሳት በዚህ ወቅት የተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ መርህ መሠረት ከማቅረብ አንፃር መልካም የሚባል ጅምር የታየበት ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም በተመሳሳይ ወቅት ከታተመው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በተሻለ መልኩ ተግብሮታልና።

በአጠቃላይ በ1991/2 ቀርበው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅመው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ረገድ የመጀመሪያዎቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ከመቻሉም በላይ በተለይ የ10ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ በርከት ያሉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ሥልት ማቅረብ መቻሉን መገንዘብ ተችሏል

4.3.5.5. ጥምረታዊ አቀራረብ በ1997 ዓ.ም

በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ በቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ የአቀራረብ ስልት የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን እናገኛለን። ከእነዚህም መካከል የተወሰኑት ብቻ ለማሳያነት እናቀርባቸዋለን።

(ገጽ 77) "ከግስ ስም መመስረት" በሚለው ክፍል ጥያቄ 1 ላይ የሚከተለውን ትዕዛዝ እናገኛለን።

"ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግሶች ወደ ስም ከለወጣችሁ በኋላ በተገቢ ስፍራቸው ላይ እያስገባችሁ የአረፍተ ነገሮቹን መልዕክት አሟሉ።"

ምሳሌ፦ ጨለጠ= ጭላጭ

ብርጭቆው ውስጥ ያለውን ጭላጭ ወተት ዝንብ ወሮታል።

የሚል ምሳሌ ካቀረበ በኋላ በዚህ መልኩ የሚሠሩ አስር ግሶች ተዘርዝረው ቀርበዋል። ከእነዚህ ግሶች የሚመሠረቱት "ሥሞች" የሚገቡባቸው 10 ያህል አረፍተ ነገሮችም ቀርበዋል።

ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡላቸውን ግሶች ወደ "ስም" መለወጥ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ምስርቶቹን ስሞች በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ባለው ተስማሚ ክፍት ቦታ በማስገባት የአረፍተ ነገሩን ሃሣብ የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ነው።

በመሆኑም ይህ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት በመጽሐፍ ውስጥ ቀርቦ የምናገኘው በውጤት ተኮር የአቀራረብ ህግጋት መሠረት ብቻ ሳይሆን ወደ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ሽግግር በታየበት መልኩም ጭምር ነው። ይህም ማለት የይዘቱ አቀራረብ ከሰዋስዋዊ ቅርጹ ተነስቶ ቅርጹ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ተግባር ላይ ወደሚውልበት የአገባብ ስርዓት ሽግግር የታየበት በመሆኑ አቀራረቡን "ጥምረታዊ አቀራረብ" በሚለው ስር ልናካትተው እንችላለን።

ይህንን አይነት የአቀራረብ ስልት ተከትለው የቀረቡ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ በተለያዩ ገጾች ላይ ሠፍረው ይገኛሉ። ለምሳሌ፦ ስለ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገር (ገጽ 29)፣ ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን አረፍተ ነገሮች ማስተካከል (ገጽ 58 እና 79)፣ ስለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ (ገጽ 85)፣ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አንቀጽ ስለመገንባት (ገጽ 110)፣ ውልድ ግሶችን በመመስረት የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን መስራት (ገጽ 92) የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህ በመነሳት በዚህ ወቅት ተሻሽሎ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ ስልት ያቀረበ መሆኑን ከላይ ካቀረብነው ማስረጃ መገንዘብ ይቻላል። በ1991 ዓ.ም ቀርቦ ከነበረው መጽሐፍ አንፃር ሲታይም የአቀራረብ ስልቱን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ለውጥና መሻሻል መኖሩን መረዳት ተችሏል። ምክንያቱም በ1991ቱ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ ሥልት ቀርበው የምናገኛቸው ይዘቶች ሁለት ብቻ ሲሆኑ በዚህ ወቅት ግን ሰባት ያህል ይዘቶች ተካትተው ይገኛሉና።

በሌላ መልኩ በተመሳሳይ ወቅት በተሻሻለው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም የተለያዩ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ ሥልት መርህ መሠረት ቀርበው እናገኛዋለን። ቀጥሎ ማሣያ የሚሆኑ የተወሰኑ ይዘቶች በምሳሌነት ቀርበዋል።

(ገጽ 92) ጥያቄ ቁጥር 1. የሚከተሉትን ቃላት ወደ መስተዋድዳዊ ሐረግ አሳድጉና ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

ምሳሌ ሀ. ሠው = ቃል (ስም)

እንደ ሠው= መስተዋድዳዊ ሀረግ

እንደ ሠው የዳበረ አዕምሮ ያለው የለም= (ዓረፍተ ነገር)

ለ. ሀገር= ቃል (ስም)

ስለሀገር= መስተዋድዳዊ ሀረግ

ስለ ሀገር ልማትና ደህንነት ማሰብ የዜጎች ሁሉ ኃላፊነት ነው። (ዓ.ነገር)

በዚህ ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ ሦስት ስሞችና ሁለት ግሶች ቀርበዋል።

መማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ለተማሪዎቹ በማቅረብ ሂደት የአቀራረብ ስልቱን ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። ምክንያቱም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶቹን በውጤት ወይም በሂደት ተኮር ስልት ብቻ ያቀረበ ሳይሆን ሁለቱንም ባጣመረ መልኩ፣ ለሰዋስዋዊ ቅርጽም ሆነ አገባብ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ቅርጹን እንዴት ባለ አውድ ውስጥ አስገብተው መጠቀም እንደሚገባቸው ጭምር በሚያሳይ መልኩ የቀረቡ በመሆናቸው ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ገጾች በርከት ያሉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ ሥልት የቀረቡ መሆናቸው በተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።ከእነዚህም መካከል፦

- ራሳቸውን በመድገም ጥምር ቃል በሚመሠርቱ ቃላት አረፍተ ነገር መመስረት (ገጽ 28)፣
- መስተዋድዶችን በመጠቀም ተራ አረፍተ ነገሮችን ወደ ውስብስብ መለወጥ (ገጽ 28)፣
- ሰዋስዋዊ ስህተቶችን አቃንቶ አረፍተ ነገሩን እንደገና መፃፍ (ገጽ 39.)፣
- አጣማሪ ቃላትና ሐረጋት በመጠቀም የተጣመሩ አረፍተ ነገሮችን መመስረት (ገጽ 55)፣
- የቃላትንና ሐረጋትን የፍቺ ገጽታ በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ማሣየት (ገጽ 62)፣
- በተሰጡ ቃላት ሀረግና ዓረፍተ ነገር በመመስረት (ገጽ 157)፣ እና
- ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ወደ ተራ ዐ.ነገሮች መከፋፈል (ገጽ 158)

የሚሉት ይገኙበታል። ከዚህ የምንረዳው መጽሐፉ ስልቱን በመተግበር ረገድ ከባለፈው የ1992ቱ መጽሐፍ ጋር ሲነፃፀር መሻሻል ማሳየቱን ነው። በአጠቃላይ በዚህ ወቅት ተሻሽለው የቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በ1991/2 ቀርበው ከነበሩት ጋር ሲነፃፀሩ በተሻለ መልኩ ስልቱን ተግባራዊ ያደረጉ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል። በመሆኑም ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቡ ሂደት ለውጥና መሻሻል እያሳየ መምጣቱን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

4.3.5.6. ጥምረታዊ አቀራረብ በ2004 ዓ.ም

በዚህ ወቅት የቀረበውና በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት እየሠጠ የሚገኘው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል ያሳየ መሆኑን በዚህ ስልት ካቀረባቸው በርካታ ይዘቶች መረዳት ተችሏል። ይህንን የአቀራረብ መርህ መሠረት አድርጎ ያቀረባቸው ይዘቶች በመጽሐፉ የተለያዩ ገጾች ላይ ሠፍረው እናገኛቸዋለን። ሁሉንም ይዘቶች ማቅረቡ አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ተገቢም ባለመሆኑ ለማስረጃ ያህል ብቻ የሚከተሉትን እናነሳለን።

- *የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ሥህተት በምሣሌው መሠረት የቁጥር፣ የፆታ፣ የመደብ በማለት ከለያችሁ በኋላ አረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ እንደገና ፃፉ ((ገጽ 26))።*

ምሳሌ፦ ልጆች ታላቆቻችንን ማክበራቸው ያስመሰግናል።

ስህተቱ የመደብ አለመስማማት

አረፍተ ነገሩ ሲስተካከል፦

1. *ልጆች ታላቆቻቸውን ማክበራቸው ያስመሠግናቸዋል።*

   ወይም

2. *ልጆች ታላቆቻችንን ማክበር ያስመሰግነናል።*

በዚህ መሠረት የሚሠሩ 5 ያህል አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል።

እነዚህን የሚመስል የአቀራረብ ስልት ያላቸው ተጨማሪ አቀራረቦች በመማሪያ መጽሐፉ

- *የቃላት አገባባዊ ፍቺ (ገጽ 7.)፣*
- *አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ማጣመር (ገጽ 65፣)፣*
- *የቃላት አማራጭያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ (ገጽ 68.)፣*
- *በቀረቡት ቃላት አረፍተ ነገር መመስረትና የቃላቱን ሰዋስዋዊ ሙያ መግለጽ (ገጽ 109)፣*
- *ስለ ቃላት መጥበቅና መላላት (ገጽ 125.)፣*
- *የቃል ክፍሎችን በተገቢው የአረፍተ ነገር ክፍላቸው ማስገባት (ገጽ 128)፣*
- *ከግስ ውልድ ግስ መመስረትና በምስርቶቹ ግሶች አረፍተ ነገር መገንባት (ገጽ 128)፣*
- *በተሠጡ ቃላት መጀመሪያ ስማዊ ሀረግ ቀጥሎ አረፍተ ነገር መገንባት (ገጽ 141)፣*
- *በተሠጡ ቃላት መጀመሪያ ቅጽላዊ ሀረግ ቀጥሎ አረፍተ ነገር መገንባት (ገጽ 141)፣*
- *ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገር (ገጽ 143)፣*
- *የተሠጡትን ቃላት ባለቤት፣ ተሳቢና ዘርፍ በማድረግ አረፍተ ነገር መስራት (ገጽ 156)*

የሚሉ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን እናገኛለን።

በመሆኑም ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚነግሩን በዚህ ወቅት ተዘጋጅቶ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይህንን የአቀራረብ ስልት ከበፊቶቹ መፃህፍት በተሻለ ሁኔታ የተገበረው መሆኑን ነው። ምክንያቱም መጽሐፉ ለሰዋስዋዊ ቅርጾችም ሆነ ለቅርጾቹ አገባብ ትኩረት በመስጠት አቅርቧቸዋልና።

አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው መጽሐፉ በውስጡ አካትቶ የያዛቸውን በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በማቅረብ ሂደት ቅርጽንና አገባብን ለየብቻ ነጣጥሎ ያቀረበበት ክፍል ቢኖርም፣ እስከ አሁን ቀርበው ከነበሩት መፃህፍት ሁሉ በተሻለ መልኩ ሁለቱንም አቀራረቦች ማለትም ውጤትና ሂደት ተኮርን አዋህዶ ወይም ለሰዋስዋዊ ቅርጽም ሆነ አገባብ ትኩረት ሰጥቶ የተዘጋጀ መሆኑን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። ይህ ድምዳሜ በዚህ ወቅት ተዘጋጅቶ ለቀረበው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም ይሠራል።

በዚህ ወቅት ቀርቦ አሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ያቀረባቸው በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በበርካታ ገጾቹ ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል የተወሰኑት፦

- *ገጽ 86፣ ጥያቄ " ለ" ከቀረቡ ግሶች ቅጽሎችን መሥርቱ*

1. ምሳሌ ፦ <u>ግስ</u>	*<u>ወልድ ቅጽል</u>*
1. አጠረ	*አጭር*
2. ወፈረ	*ወፍራም*
3. ከበረ	*ክቡር*

በዚህ ምሣሌ መሠረት የሚሠሩ አራት ግሶች ቀርበዋል።

ከተማሪዎቹ የሚጠቀው በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከቀረቡላቸው ግሶች ቅጽል መመስረት ነው። ይህ በቅርጽ ላይ ብቻ ያተኮረ አቀራረብ ነው ማለት እንችላለን። ነገር ግን አቀራረቡ በዚህ ብቻ አያበቃም። ከአምድ የተመሠረተው ቅጽል በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ በተገቢው ቦታ ገብቶ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል። ይህ ደግሞ ሂደት ተኮር አቀራረብ ነው። ይህንን ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር የሚደረገውን ሽግግሮሽ የሚያቀላጥፈውን የአቀራረብ ስልት ጥምረታዊ አቀራረብ እንለዋለን።

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ስልት የቀረቡ በርካታ ይዘቶች መጽሐፉ፦

- *ከቃል ክፍሎች ሀረጋትን መመስረት (ገጽ 26)፣*
- *የአረፍተ ነገር አይነቶች (ገጽ 44፣ 72 እና 133)፣*
- *የቃላት አማራያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ (ገጽ 45 እና 127)፣*
- *የአረፍተ ነገር ስልቶች (ገጽ 61.)፣.*
- *የድምጾች ጠብቀውና ላልተው መነበብ (ገጽ 83)፣ እና*
- *የድምፅ መርዘምና ማጠር (ገጽ 84-85)*
- *የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች(ገጽ 96)*

ላይ ቀርበው እናገኛቸዋለን። ከዚህ የምረዳው መማሪያ መጽሐፉ የአቀራረብ ስልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ያቀረበ መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ ይህንን የአቀራረብ ስልት ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቡ ሂደት ከ1991/2 ዓ.ም ጀምሮ በቀረቡት መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ በሥፋት እየተተገበረ የመጣ መሆኑን ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ መረዳት ተችሏል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሣው ዓላማ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩትና ባሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከመቼ ጀምሮ በየትኛው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካትተው እንደቀረቡ በመመርመር ይዘቶቹ ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አንጻር በጊዜ ሂደት ያሳዩትን ለውጥና መሻሻል ወይም አለመሻሻል መፈተሽ ነበር።

ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚገባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎችም በሰዋስው ትምህርት ረገድ ምንምን ይዘቶች ቀረቡ?፣ እነዚህ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ አቀራረባቸው ምን ይመስላል? በተጠቀሰው ዘመን፣ ታላሚ በሆኑት የተተኳሪዎቹ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የትምህርት ይዘቶቹ ከአቀራረብ አንፃር ያሳዩት ለውጥና መሻሻል ምን ገጽታ አለው? የሚሉት ነበሩ።

አጥኚው ይህንን ጥናት ዳር ለማድረስ የሚያስችሉትን ትውረታዊ የመነሻ ሃሣቦች ከጥናቱ ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው ቀደምት ጥናቶች፣ መፃህፍት፣ የጥናት መጽሔቶችና የመረጃ መረቦች የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ የክለሳ ድርሳኑን ክፍል አጠናክሯል። በክለሳ ድርሳኑ ክፍልም ምሁራኑ ያቀረቧቸውን ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች በመንተራስ መፃህፍቱን ለመገምገም የሚያስችሉ መስፈርቶችን አዘጋጅቷል። በእነዚህም መስፈርቶች መሠረት ተተኳሪዎቹ የመማሪያ መፃህፍት እንደየህትመት ዘመናቸው ቅደም ተከተል ተፈትሸዋል።

ትንተናው የተካሄደውም አንድን የማቅረቢያ መስፈርት በመውሰድ በተለያዩ ስድስት ጊዜያት በታተሙት አስራ ሁለት የተተኳሪዎቹ ክፍሎች የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ምን ገጽታ እንዳለው በቅደም ተከተል በመፈተሽ ነው። ይህንን ፍተሻ በማድረግ ሂደትም ሁለት መልክ ያላቸዉ ተግባራት ተከናዉነዋል። የመጀመሪያው ተግባር በተከታታይ ጊዜያት ታትመው በቀረቡት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአቀራረብ መርሁ ያሳየውን ለውጥና መሻሻል ወይም አለመሻሻል የሚያሳይ ገጽታ ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በተመሳሳይ ወቅት ታትመው በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለውን ሁኔት የሚያመለክት ነው።

ይህንን ተግባር ለማከናወን ያስችል ዘንድም በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በሥነ ድምጽ፣ ሥነ ምዕላድ፣ ሥነ-ሐረግ፣ አረፍተ ነገርና ሥነ ፍቺ በሚል ዘርፍ ተለይተው ተለቅመዋል። ቀጥሎም በእነዚህ የሰዋስው ንዑስ ዘርፎች ውስጥ ተካትተው የቀረቡት ይዘቶች በየወቅቱ እየተለወጡና እየተሻሻሉ በመጡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተሠጣቸው ትኩረትና የተከሰቱበት ጊዜ የተዳሰሰ ሲሆን፣ በመጨረሻም በዚህ መልኩ የተሠበሠቡት መረጃዎች ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል።

በትንተናው ውጤትም ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩትና ያሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከስነ ትምህርታዊ መርሆዎች አንጻር እንደሚከተለው ሆነው ተገኝተዋል።

ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች፣ ሥነ ድምፅ፣ ሥነ ምዕላድ፣ ሥነ ሐረግ፣ አረፍተ ነገርና ሥነ ፍቺ በሚል በንዑሳን ክፍሎች በመመደብ ከመቼ ጊዜ አንስቶ መቅረብ እንደጀመሩ ለማወቅ በተደረገው ቅኝት፣ አጠቃላይ በሆነ መልኩ መማሪያ መፃህፍቱ ሁለት መልክ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

የመጀመሪያው ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የነበራቸው ገጽታ ነው። ወቅቱ ቅርፃዊ ሰዋስው በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ያልተካተተበትና መፃህፍቱም በሥነ-ፍቺና አገባብ በተለይም በአረፍተ ነገር ምስረታ ላይ ያተኮሩ ስለነበሩ ለቅርፃዊ ሰዋስው ቦታ ያለመስጠት ክፍተት ታይቶባቸዋል። በዚህም መሠረት ስነ ድምጽን በተመለከተ ምንም የቀረበ ይዘት ያልታዬ ሲሆን በስነ-ምዕላድ ዘርፍም የ"ጥምር ቃል አመሰራረት፣ ውልድ ግሶች አመሰራረት እና የስም ገላጮችን መለየት" ከሚል የዘለለ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘት አልታየባቸውም። በሥነ ሐረግ ዘርፉም እንዲሁ "ከተሠጡ ቃላት ሐረግ መመስረት" ከሚለው በስተቀር ሌላ ይዘት አይገኝም። አረፍተ ነገርንና ሥነ ፍቺን በተመለከተ ግን በቅርጽ ላይ አያተኩሩ እንጂ ሠፊ ትኩረትና ሽፋን ተሰጥቷቸው በተደጋጋሚ ቀርበዋል።

ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚታየው ሲሆን በተጠቀሰው ዘመን ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሁሉም ንዑሳን የሰዋስው ትምህርት ዘርፎች ተካትተው ቀርበዋል።

የንዑሳኑን ሰዋስዋዊ የትምህርት ዘርፎች ተናጠላዊ ገጽታ ስንመለከት ደግሞ፡-

ነ-ድምጽ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያልተካተተ
ን ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን
ትቶ ከመገኘቱም በላይ የተሠጠው ትኩረትና የቀረበበትም መንገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስፋትና
ለቀት እያገኘ መምጣቱን ማረጋገጥ ተችሏል።

ኖ ምዕላድ ዘርፍም እንዲሁ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት
ስጥ እጅግ ጥቂት ሊባሉ የሚችሉ ይዘቶች ብቻ የቀረቡ ሲሆኑ ከ 1984 እስከ 2004 ድረስ
ት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን እንደ ስነ ድምጽ ሁሉ ሠፊ ሽፋን አግኝቶ ቀርቧል።

ነ ሐረግ ከ1968 እስከ 1983 ፣ ከ1984 እስከ 1996 እና ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ
በሩት ጊዜያት ያለው ገጽታ ልዩነት ታይቶበታል።

968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ "ከምስረታ" የዘለለ ይዘት
ልቀረበም ነበር። ያውም ቢሆን ውስን በሆነ መልኩ ነው። ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ
በሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን "ከምስረታ" በተጨማሪ "አይነትና አመሠራረትን"
ተመለከተ በውስን የሐረግ አይነቶች ደረጃም ቢሆን ተካትቶ መቅረብ የጀመረበት ጊዜ ሲሆን፣
1997 እስከ 2004 ዓ.ም ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ሁሉንም የሐረግ አይነቶች
ካተተ መልኩ የ"አመሠራረት፣ አይነት፣ ቅርፃዊና መዋቅራዊ ጉዳዮች" በስፋት መቅረባቸውን
ማረጋገጥ ተችሏል።

ረፍተ ነገርን በተመለከተ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩት
መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በስፋት ቀርቦ የነበረው " በተሠጡ ቃላትና ሐረጋት አረፍተ ነገር
መመስረት" ነበር። ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን
ምስረታ በተጨማሪ ስለ "አይነቶቹ፣ ሥልቶቹ፣ ቅርፃዊ እና ተግባራዊ ገጽታው" ከጊዜ ወደ
ጊዜ በሥፋትና በጥልቀት እየቀረበ መምጣቱን ማወቅ ተችሏል።

የቃላት፣ የቅጥያዎች፣ የሐረጋትና የአረፍተ ነገራት ፍቺዎችን በተመለከተ ከ1968 እስከ 2004
ዓ.ም ድረስ ባሉት ሁሉም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ሲሆኑ የስርጭታቸውም መጠን
እየጨመረ መምጣቱን ማወቅ ተችሏል። በተለይም የቃላት፣ የሐረጋትና አረፍተ ነገራት
"አውዳዊ፣ ተመሳሳይና ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍቺዎች" ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም
ድረስ ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሥፋት የቀረቡ ሲሆኑ ከ1984 እስከ

04 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥም፣ ከስርጭታቸው በተጨማሪ
ቀርቡበት ስልትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበላ መምጣቱ ታውቋል።

ስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ስልት አደረጅቶ
ቅረብን በተመለከተ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ቀርበው የነበሩት የ9ኛና 10ኛ ክፍል
ማሪያ መፃህፍት በሚከተሉት ሦስት ዘመናት ተመሳሳይ ባህሪያት ታይቶባቸዋል።

ጀመሪያው ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ያለው ሲሆን በዚህ ወቅት ሁለት ጊዜ ቀርበው
በሩት *መማሪያ መፃህፍት* ውስጥ እጅግ ጥቂት ሊባል በሚችል ደረጃም ቢሆን መፃህፍቱ
ቱን ተጠቅመው ያቀረቧቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ታይተዋል። ይሁን እንጂ በዚህ
ት የቀረቡት ይዘቶች ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ የአቀራረብ ስልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ
ምህርት ይዘቶች የማቅረቡ ተግባር ሠፊ ክፍተት የታየበት መሆኑ ተረጋግጧል።

ለተኛው ዘመን የሚባለው ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ያለው ሲሆን፣ *መማሪያ*
ፃህፍቱ ከስነ ፍቺ እና ዓረፍተ ነገር ምስረታ በተጨማሪ በርካታ ቅርጻዊ የሰዋስው ትምህርት
ዘቶችን ያካተቱ ቢሆኑም፣ በዚህ የአቀራረብ ስልት የቀረበ አንድም ሰዋስዋዊ የትምህርት
ዘት አልተገኘም። በመሆኑም የነበረው ክፍተት እጅግ ጎልቶ የወጣበት ጊዜ መሆኑን መገንዘብ
ችሏል።

መጨረሻው ዘመን ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ያለው ነው። በተጠቀሰው ዘመን የአቀራረብ
ልቱን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቡ ተግባር ዳግም ያንሰራራበትና
መማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ተገቢ የሆነ ሽፋንና ትኩረት እያገኘ የመጣበት ዘመን መሆኑን
ተደረገው የሠነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም በ1997 ዓ.ም በተዘጋጁት *መማሪያ*
መፃህፍት ውስጥ በተወሰነ መልኩ መተግበር የጀመረው ይህ የአቀራረብ ስልት በ2004 ዓ.ም
ዘጋጅተው በቀረቡት መፃህፍት ውስጥ በሥፋት ቀርቦ መገኘቱ ታውቋል።

ዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብን በመተለከተ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ያለው ጉዞ ሦስት
ጽታዎች ያሉት ሆኖ አግኝተነዋል።

መጀመሪያው ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩት *መማሪያ* መፃህፍት
ውስጥ የነበረው ገጽታ ነው። በዚህ ወቅት *መማሪያ* መፃህፍቱ ዝቅተኛ ሊባል በሚችል መልኩ

ገበሩት በመሆናቸው ከዚህ የአቀራረብ መርህ አንጻር መጻህፍቱ ክፍተት የታየባቸው
ያናቸውን መገንዘብ ተችሏል።

ኒተኛው ገጽታ ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የነበረው
ያን መፃህፍቱ የያዟቸውን ሁሉንም ሰዋሰዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ ስልት የማቅረብ
ት ያሳዩበት ጊዜ ነበር። በመሆኑም የወቅቱ መማሪያ መፃህፍት ይዘቶችን በዚህ ስልት
ማቅረብ አንፃር የበለፀጉ ሆነው ተገኝተዋል። ይሁን እንጂ በዚህ የአቀራረብ መርህ ብቻ
ሉንም ይዘቶች የማቅረቡ ሂደት ስነ ትምህርታዊ ተቀባይነቱ አነስተኛ ነው።

ስተኛውና የመጨረሻው ገጽታ ደግሞ ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ቀርበው በነበሩትና
ት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለው ሁኔት ነው። በወቅቱ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ
አቀራረብ ስልቱ ትግበራ መቀዛቀዝ ያሣየበት ወቅት ነበር። ምክንያቱ ደግሞ መማሪያ
ፃህፍቱ ከፊል ሰዋሰዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መርህ
ያቀርቡ ቀሪዎቹን ደግሞ ከአጠቃለይ ወደ ዝርዝር በሆነ ስልት ማቅረብ የጀመሩበት ጊዜ
መሆኑ ነው። ይህ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይን እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የማቅረቢያ
ቀርሆዎችን አመጣጥኖ የማቅረቡ ሂደት ስነ ትምህርታዊ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ
ቀባይነት ያለው አሰራር ሆኖ ተገኝቷል።

ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋሰዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቡን ሂደት
ተመለከተ ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የታየውን ለውጥ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ ሁለት
ጽታ ያለው ነው።

መጀመሪያው በ1968 ዓ.ም በታተሙትና በኋላም በ1972/3 ዓ.ም ተሻሽለዉ ቀርበው እስከ
983 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለው ነው ።
ተጠቀሰው ዘመን የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ቅርፃዊ ሰዋስው በሥፋት ያልታየባቸውና
ትኩረታቸውም ሥነ አገባብን በተለይም የአረፍተ ነገር ምስረታንና ሥነ ፍቺን መሠረት ያደረገ
ነበር። በዚህም መሠረት መማሪያ መፃህፍቱ የተጠቀሱትን የትምህርት ይዘቶች በሙሉ
የቀረቡት በሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ነበር። በመሆኑም በተጠቀሰው ዘመን አገልግሎት ላይ
ውለው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት የአቀራረብ ስልቱን በሚገባ ተግብረውታል። ይሁን እንጂ
ሰዋሰዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በዚህ የአቀራረብ ስልት ብቻ ማቅረቡ ተገቢ አልነበረም።
ምክንያቱም ከውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ጋር መጣጣም ነበረበትና።

የአቀራረቡ ሁለተኛ ገጽታ ግን ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልገሎት ሲሰጡ በነበሩትና ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለው ነው። በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ቅርፃዊ ሰዋስው በስፋት የታየባቸው ናቸው። በመሆኑም መፃህፍቱ የአቀራረብ ስልቱን ተጠቅመው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር በተለይም ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ መዳከም ያሳየበት ዘመን ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የሆነው በተጠቀሰው ዘመን የነበሩት መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በብዛት በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት በማቅረባቸው ምክንያት ነው። ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን የአቀራረብ ስልቱ እንደገና ማንሰራራት የጀመረበትና ከጊዜ ወደ ጊዜ በስፋት እየተተገበረ የመጣበት ዘመን መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። ይህም ማለት መጀመሪያ በ1984 እና በኋላም በ1991/2 ዓ.ም ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በተወሰነ መጠን ብቻ ተተግብሮ የምናገኘው ይህ የአቀራረብ ስልት በ1997 እና በ2004 ዓ.ም በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን በስፋት እየተተገበረ መምጣቱን ማረጋገጥ ተችሏል።

ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት *ውጤት ተኮር የአቀራረብ* ስልትን ተጠቅመው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር ሦስት መልክ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

የመጀመሪያው ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ሁለት ጊዜ ታትመው አገልግሎት ሲሰጡ በነበሩት መፃህፍት ውስጥ ያለው ነው። አስቀድመን እንደገለጽነው በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት በርካታ ቅርፃዊ ሰዋስው ያልነበረባቸው ነበሩ ። በመሆኑም በ1973 ዓ.ም ቀርቦ በነበረው የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካትተው ከተገኙት ሁለት ቅርጻዊ የሰዋስው የትምህርት ይዘቶች ውጪ በዚህ ስልት የቀረበ ይዘት አልተገኘም። በመሆኑም በተጠቀሰው ዘመን ተግባር ላይ ውለው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት የአቀራረብ ስልቱን ተግብረውታል ለማለት አያስደፍርም። የመጻህፍቱ ትልቁ ድክመትም ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህን አመጣጥኖ ያለመተግበር ክፍተት ነዉ።

ሁለተኛው ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የታየው ገጽታ ነው። በተጠቀሰው ዘመን አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የሚገኙባቸው ሲሆኑ ከያዟቸው

ይዘቶች መካከል አብዛኛዎቹን ያቀረቧቸው በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት አማካኝነት ነበር። በመሆኑም ወቅቱ የአቀራረብ ስልቱ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ በስፋት የተተገበረበትና መፃህፍቱም የመዋቅራዊነት ባህሪ የታየባቸው ዘመን ነበር። ይሁን እንጂ ስነ ትምህርታዊ ተቀባይነት ያለው ሂደት እና ውጤት ተኮር አቀራረብን አመጣጥኖ መተግበር በመሆኑ በዚህ ረገድ መጻህፍቱ ክፍተት የታየባቸው መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል።

የአቀራረብ ስልቱ ሦስተኛው ገጽታ የሚባለው ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ባሉትና በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለው ነው። በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ረገድ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልትን የተገበሩ ቢሆኑም ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ከነበሩት ጋር ሲነፃፀሩ ለዘብ የማለት አዝማሚያ ያሳዩ ይመስላሉ። ምክንያቱ ደግሞ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት የማቅረቡ ተግባር እየገነነ በመምጣቱ ነው። በመሆኑም የአቀራረብ ስልቱ በተጠቀሠው ዘመን የመቀዝቀዝ አዝማሚያ የታየበት ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ውጤት እና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን አመጣጥኖ የማቅረቡ ጉዳይ ስነ ትምህርታዊ ፋይዳው የጎላ በመሆኑ መጻህፍቱ ከዚህ መርህ አንጻር ከነሱ በፊት ከነበሩት የተሸሉ ሆነው ተገኝተዋል።

ጥምረታዊ አቀራረብን ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን የማቅረቡ ሂደት ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፃህፍት ውስጥ የነበረው ሁነት በሚከተሉት ሶስት ዘመኖች ተመሳሳይ ገጽታ የታየበት ሆኖ ተገኝቷል።

የመጀመሪያው ክፍል ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የነበረው ነው። በዚህ ወቅት ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ቅርፃዊ ሰዋስውን በተፈለገው መጠን ያላካተቱ ከመሆናቸውም በላይ የያዟቸውን ውስን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችንም ቢሆን በዚህ ስልት ያላቀረቡበት ወቅት ነበር።

ሁለተኛው ክፍል የሚባለው ደግሞ በ1984 ዓ.ም ተዘጋጅቶ እስከ 1990/91 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ላይ ውለው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለው ገጽታ ነው። በዚህ ወቅት ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ከበፊቶቹ ይልቅ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አካትተው የያዙ ቢሆኑም የተወሰኑትን በውጤት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት ብቻ ያቀረቧቸው ሲሆኑ ቀሪዎቹን ደግሞ በሂደት ተኮር ስልት ብቻ ማቅረባቸውን ማወቅ ተችሏል።

ይህም ማለት እነዚህ ሁለት የአቀራብ ስልቶች በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የተተገበሩ ቢሆኑም የቀረቡት ግን በተናጠል ነው። በመሆኑም የወቅቱ መማሪያ መፃህፍት የአቀራረብ ስልቱን ተግባራዊ አላደረጉትም ነበር። ይህም የመማሪያ መጻህፍቱ መሰረታዊ ክፍተት ሆኖ ታይቷል።

ሦስተኛው ክፍል ከ1991/2 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበረው ዘመን ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የታየው ለውጥ ነው። ወቅቱ የአቀራረብ ስልቱ የተከሠተበትና በሂደትም በሥፋት አገልግሎት ላይ እየዋለ የመጣበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የአቀራረብ ስልቱ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የተከሠተው በ1991/2 ዓ.ም በቀረቡት ውስጥ ሲሆን፣ በ1997 ዓ.ም ተሻሽለው በቀረቡት ውስጥ በተሻለ ሁኔታ ተስፋፍቶ እናገኘዋለን። በመጨረሻም በ2004 ዓ.ም እንደ አዲስ በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ደግሞ የበለጠ ዳብሮና በልጽጎ በመቅረቡ የአቀራረብ ስልቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻለ ትኩረት እያገኘና ተገቢ የሆነ ሽፋን እየተሠጠው መምጣቱን ማወቅ ተችሏል።

5.2 አስተያየት

ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ አካትቶ የማቅረቡ ዓላማ ተማሪዎች ከሚኖራቸው ክህሎት ጎን ለጎን የሥርዓትም እውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ ከቋንቋ ትምህርቱ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። ከቋንቋ ተማሪውም የሚጠበቀው የክሂልና የሥርዓት እውቀትን አጣምሮ መያዝ እና በተግባቦት ወቅት በአግባቡ አገልግሎት ላይ ማዋል ነው።

ከ1968 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩት እና ባሉት መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ቀርበው የነበሩትን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በተመለከተ በ1968 እና 1972/3 ዓ.ም የታተሙት በዓረፍተ ነገር ምስረታና በስነ ፍቺ ላይ በማተኮር ለቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጽ፣ አገባብና አጠቃቀም ቦታ የነፈጉ ነበሩ። ይሁን እንጂ ከ1984 እስከ 2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት ግን ከአረፍተ ነገር ምስረታና ሥነ ፍቺ በተጨማሪ ከሥነ ድምጽ እስከ አረፍተ ነገር መዋቅር ድረስ በርካታ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን አካትተው የያዙ በመሆናቸው የነበረውን ክፍተት የሞሉ ሆነው ተገኝተዋል። ይኸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከቋንቋው የክሂልና የሥነ ጽሁፍ ዘርፎች ጋር በማጣመር በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የማቅረቡ ተግባር ተጠናክሮ ቢቀጥል

ሰዋስዋው የትምህርት ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ የአቀራረብ ስልት የማቅረቡ ተግባር ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እጅግ ጥቂት ሊባል በሚችል መልኩ የተከሰተ ሲሆን፣ ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ባሉት ውስጥ ደግሞ ጭራሹኑ አልተተገበረም ነበር። ይሁን እንጂ ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩትና ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ተገቢውን ቦታና ትኩረት እያገኘ የመጣ በመሆኑ፣ ይህ ጅምርና እድገት ተጠናክሮ ቢቀጥል። ይህ ማለት ግን ሁሉም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በዚህ የአቀራረብ ስልት ብቻ ወደሚቀርቡበት ደረጃ ይድረሱ ማለት ሳይሆን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ጋር ይመጣጠን ማለት ነው።

ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በሆነ የአቀራረብ ስልት የማቅረብ ሂደት ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ውስን በሆነ መልኩ ብቻ የተተገበረ ሲሆን፣ ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ሁሉንም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የቀረቡት በዚህ ስልት ብቻ ነበር። ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉትና በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን ከፊል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ አቀራረብ እየቀረቡ በመምጣታቸው ይኸው ተግባር ተጠናክሮ ቢቀጥል፣ ምክንያቱም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከሁለቱ በአንዱ የአቀራረብ መርህ ብቻ አደራጅቶ ማቅረቡ ተገቢ አይደለምና። ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው ደካማ ጎን ያላቸው በመሆናቸውና የአንዱ አቀራረብ ክፍተት በሌላው አቀራረብ ጠንካራ ጎን ስለሚሞላ ሁለቱንም አቀራረቦች አመጣጥኖ ማቅረቡ ስነ ትምህርታዊ ተቀባይነት ያለው ነው።

ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ቀርበው የነበሩት መማሪያ መፃህፍት የያዟቸውን ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ሁሉንም ሊባል በሚችል መልኩ ያቀረቧቸው በሂደት ተኮር የአቀራረብ መርህ መሠረት ሲሆን ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን በውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት የገነነበት ዘመን በመሆኑ የአቀራረብ ስልቱ ትግበራ መቀዛቀዝ አሳይቷል። ይሁንና በዚህ ጊዜ ውስን በሆነ መልኩ ሲተገበር የነበረው ይህ የአቀራረብ ስልት ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በድጋሚ ማንሠራራት አሳይቶ በሂደት እየዳበረ መምጣቱን ማረጋገጥ ተችሏል። በተለይም በ2004 ዓ.ም በቀረቡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተሻለ አተገባበር የታየበት በመሆኑ ይኸው ሁኔታ የበለጠ ተጠናክሮ ቢቀጥል

ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ውጤት ተኮር በሆነ የአቀራረብ ስልት የማቅረቡ ተግባር ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እጅግ ዝቅተኛ ሊባል በሚችል መልኩ ብቻ የተተገበረ ሲሆን ከ1984 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን በግልባጩ አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች የቀረቡት በዚህ ስልት መሠረት ነው። ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በቀረቡት መፃህፍት ውስጥ ደግሞ የአቀራረብ ስልቱ የመቀዝቀዝ አዝማሚያ አሳይቷል። ምክንያቱ ደግሞ መማሪያ መፃህፍቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በሂደት ተኮር ስልትም ማቅረብ በመጀመራቸው ነው። በተለይም በ2004 ዓ.ም የተዘጋጀዉ የመማሪያ መጽሐፍ ውጤት ተኮርንም ሆነ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልትን ተመጣጣኝ ሊባል በሚችል ደረጃ ያቀረበ በመሆኑ ይኸው የሂደትና ውጤት ተኮር ምጥጥናሻዊ አቀራረብ ይበልጥ ተጠናክሮ ቢቀጥል። ምክንያቱም ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን ከሁለቱ በአንዱ የአቀራረብ መርህ መሠረት ብቻ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም። ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራቸው ደካማ ጎን ያላቸው በመሆናቸውና የአንዱ አቀራረብ ክፍተት በሌላው ጠንካራ ጎን ስለሚሸፈን ሁለቱንም አቀራረቦች አመጣጥኖ ማቅረቡ ተቀባይነት ያለው አመለካከት በመሆኑ ነዉ።

ጥምረታዊ አቀራረብን በተመለከተ ከ1968 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ቅርፃዊ ሰዋስው ተገቢ የሆነ ቦታ ያልተሠጠው ሲሆን በተወሰነ ደረጃ አሉ የተባሉትንም ቢሆን በዚህ ስልት የማቅረቡ ጉዳይ ትኩረት ተነፍጎት ነበር።ከ 1984 እስከ 1996 ዓ.ም ቀርበው በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ደግሞ የተወሰኑትን ይዘቶች በውጤት ተኮር ቀሪዎቹን ደግሞ በሂደት ተኮር ስልት ብቻ አቅርበው ስለነበር ሥልቱን ተጠቅሞ ይዘቶችን የማቅረቡ ክፍተት እንደቀጠለ ነበር። ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በነበሩት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ግን የአቀራረብ ስልቱ በሂደት እያደገና እየጎለበት የመጣበት ወቅት ሲሆን በተለይም በ2004ቱ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሥፋት ተተግብሮ የቀረበ በመሆኑ ይኸው ተግባር የበለጠ ተጠናክሮ ቢቀጥል

በተጠቀሰው ጊዜ ቀርበው የነበሩት መማሪያ መጻህፍት ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይን፣ ውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አመጣጥኖ በማቅረብ እና ጥምረታዊ አቀራረብን በተገቢው ሁኔታ በመተግበርም ረገድ በጊዜ ሂደት እየተሻሻሉ የመጡ ቢሆኑም ከችግር የጸዱ ናቸው ማለት ግን አይደለም። ስለዚህ ከእነዚህ አቀራረብ ክፍተቶች በመነሳት የተሻሉ መጻህፍት ይዘጋጁ ዘንድ ለአዘጋጆቹ አካላት የአቀራረብ መርሆዎቹን ታሪካዊ እድገት እና ነባራዊ ሁኔታን ከግንዛቤ ያስገባ ስልጠና ቢሰጥ።

ዋቢ ጽሁፎች

ሁሉባንተ አደመ (1994)። "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተዘጋጁት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አደረጃጀት ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ሐዋዝ ወልደየስ (2000)። "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛና ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጠ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት"። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)።

ሰለሞን ዮሐንስ (1987)። "በ1984 የተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት የሰዋስው ይዘት አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ስሜ ውቤ (1996)። "በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል የ "Afaan Oromoo" መማሪያ መጽሐፍት ላይ የተደረገ የሰዋስው ትምህርት ግምገማ"። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽኑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አበበ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ባየ ይማም (1987)። *የአማርኛ ሰዋስው*። አዲስ አበባ፣ ተ.መ.ማ.ማድ።

_____(2000)። *የአማርኛ ሰዋስው*። የተሻሻለ ሁለተኛ እትም ፣ አዲስ አበባ፣እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማኅበር።

ተስፋዬ ሽዋዬ (1981)። "የቋንቋና ሥነ-ልሣን መግቢያ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)።

ተስፋዬ በቀለ (1993)። "በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል ኢ-አፍ-ፊት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ኤም.ኤ.ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴር (1968)። *አማርኛ መማሪያ 10ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፣
ት.መ.ማ.ማ.ድ።

_____ (1968*)። አማርኛ መማሪያ 9ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ።

_____ (1972*)። አማርኛ መማሪያ 10ኛ ክፍል።* እንደገና ተሻሽሎ የታተመ፣
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

_____(1973*)። አማርኛ መማሪያ 9ኛ ክፍል።* እንደገና ተሻሽሎ የታተመ።
ሴንትራል ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

_____ (1984*)። የአማርኛ መማሪያ 10ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ። ት.መ.ማ.ማድ።

_____ (1984*)። የአማርኛ መማሪያ 9ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ። ት.መ.ማ.ማድ።

_____ (1991)። *የአማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 9ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ። ሜጋ
አሳታሚ ድርጅት።

_____ (1992*)። የአማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 10ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ። ሜጋ
አሳታሚ ድርጅት።

_____ (1997)። *የአማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 10ኛ ክፍል*።ተሻሽሎ የወጣ፣ አዲስ አበባ።
ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

_____ (1997)። *የአማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 9ኛ ክፍል*።ተሻሽሎ የወጣ፣ አዲስ አበባ።
ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

_____ (2004)። *አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 9ኛ ክፍል* ።ዱባይ፣አል-ጉሬር
አሳታሚ አታሚ ድርጅት።

_____ (2004)። *አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 10ኛ ክፍል* ።ዱባይ፣አል-ጉሬር
አሳታሚ አታሚ ድርጅት።

አስካለ በዛብህ (1992)። "በ1991 የተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃህፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አቀራረብ ትንተና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ኢያሱ መሰለ (2003)። "በ(1999) ዓ.ም በተሻሻሉት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘት አመራረጥ አቀራረብ አደረጃጀት ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ኤም.ኤ.ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)።

እስሌማን (2003)። "በ12 ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ት/ት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር"። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ኤም.ኤ.ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)

እንደገና ፈንታው (1994)። "በድሬደዋ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ላይ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ" ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ኪዳን ገብረእግዚያብሔር (1993)። "በደቡብ ህዝቦች ክልል በመጀመሪያ ሳይክል ለኢ- አፍ ፊት በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ካሳሁን ገነቱ (1995)። "በአፋር ክልላዊ መንግስት ለሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁ የአማርኛ መማርያ መፃህፍት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ"።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ውድአዲስ ምህረቴ (1994)። "በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ለሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ያለዉ እንዳወቀ (1998)። የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። ባህርዳር፣ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ጌታሁን አማረ (1989)። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

_____ (1993)። "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ5ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ።" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ መጽሔት፣ ቁጥር 11፣ ገጽ 53-67።

ይግለጡ አለነ(1988)። "የአማርኛ መማሪያ ሰዋስው ትምህርት ድረጃ ከ9-11 ክፍል"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ዮሐንስ ኃይለማሪያም (1993)። "በ1992 የተዘጋጀው አዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃህፍ የሰዋስው ይዘትና አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ደምሴ ስንሻው (1999)። "የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት (1966 — 1983)"። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ቋንቋ ማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

Allen, J. P. B. (1974). "Pedagogical Grammar." In Allen, J. P.B. and S.P it Corder, Techniques.*In Applied Linguistics.* Oxford: Oxford University Press.

Batstone, R. (1994). *Grammar.* Oxford: Oxfrod University Press.

Brown, D. (1994). *Principle of Language Learning and Teaching.* USA: Prentice Hall.

Bygate, M. et.al. (1994). *Grammar and Language Teacher.* Hemel Hempstead: Prentice Hall.

Chalker, S. (1991). Current English Grammar. London: Macmillan Education Ltd.

_____ (1994). "Pedagogical Grammar" in bygate.M., Allan Tonkya and Eddle Williams (ed.) (1994). Grammar and Language Teachers. Englewood cliffs,N.J: Prentice Hall International Hu Ltd.

Cook, V. (2001). Second Language Learning and Language Teaching (3rd ed.). New York: Oxford University Press.

Cunningsworth, A. (1984). *Evaluating and Selecting EFL.* Teaching Materials (5th print). Oxford: Heinman.

_____ (1995). *Choosing your Course Book.* Oxford: Henimann.

Dawson, C. (1984). *Teaching English as a Foreign Language.* Edinburgh: Nelson Harp.

Dubin and Olshtain, E. (1986). *Course Design.* Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. (2000). "*The Place of Grammar Instruction in the Second/Foreign Language Curriculum.*" In Brown, K. (ed.). language and linguistics. Encyclopedia, Vol.9, Oxford: Elsevier Ltd. (pp28-54).

Grant, N. (1987). *Making the most of your Text Book.* London: Longman.

GreenBaum, S. (1986). "*English and a Grammarian's.*" in Bygate, M. et.al.(eds.). Grammar and Language Teacher. New York: Prentice Hall. Pp32-33.

_____ (1988). Good English and the Grammarian. London: Longman.

Harmer, J. (1987). *Teaching and learning grammar.* London. Longman.

_____ (1991). *The Principle of English Language Teaching.* London: Longman.

_____ (1995). *The Principle of English Language Teaching.* London: Longman.

Hutchinson, T. and Torres, E. (1994). *The Text Book as Agent of Change.* Hongkong: Longman Group LTd.

Larson-Freeman, D. (1991). *Teaching Grammar.* In Celce-Murcia, M. (ed.). Teaching English as Second or Foreign Language. Boston: Heinman Publisher. Pp 246-295

Little, D. (1994). "Words and their Properties: Arguments for a lexical Approach to Pedagogical Grammar". In odlin, J. (ed.), *perspectives on Pedagogical Grammar.* (pp. 99-122). Cambridge: Cambridge University Press.

Donough. J. and Christopher, S. (1995). *Ma terial and Methods in ELT.* A Teachers Guides Oxford: Blanck Well.

Mitchell, R. (1994) *"Foreign Language Teachers and Teaching of Grammar."* In Bygate. M., Tonkyn, A. and Williams, E. (eds.). Grammar and Language Teacher. (pp 215-236). Cambridge: Cambridge University Press.

Newby, D. (2000). "*Pedagogical Grammar.*" http://knol.google.com/k/7/8/2010.

Nunan, D. (1991). *Language Teaching methodology: A Text Book for Teachers.* Oxford: international Book Distribution Ltd.

Odlin, T. (1994). "Introduction." In Odlin, T. (ed.). *Perspective on pedagogical Grammar. (pp.1-21).* Cambridge: Cambridge University Press.

Palmer, F. (1984). *Grammar (2nd ed.).* New York: Penguin Book.

Richards, J. and Rodgers, T. (1986). *Approaches and Methods in Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Rutherford, W. C. (1987). *Second Language Grammar.* London: Longman.

Sheldon, L. (1987). "*Evaluating ELT Text Book and Materials.*" *ELT Journal.* Vol. 42 No 237-246.

Stern, H. H. (1983). Fundamental Concepts Of Language Teaching. Cambridge: CUP.

_____ (1992*). Issues and Optioins in Language Teaching.* Oxford: Oxford University Press.

Tonkyn, A. (1994). "*Introduction: Grammar and Language Teacher.*" In Bygate, M., Tonkyn, A. and Williams, E. (eds). Grammar and Language Teacher. (pp1-13) Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P. (1996). *A Course in Language Teaching: Practice and Theory.* Cambridge: Cambridge University Press.

_____ (2008). *Grammar Practice Activities: A Practical Guide for Teachers.* Cambridge: Cambridge University Press.

Woods. E. (1995). *Introduction Grammar.* London: P

ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ ሥራ መሆኑን በፊርማ አረጋግጣለሁ።

ስም እምሸው ማሞ በለጠ

ፊርማ .....

ቀን ሰኔ 2005 ዓ.ም